# አማርኛ
# እንደሁለተኛ ቋንቋ
# የተማሪ መፅሐፍ
# አራተኛ ክፍል


**አዘጋጆችና አርታኢዎች**

ብርቱካን ጃቢር (BA)

ገነት ፈለቀ (MA in TeAm)

ዮሀንስ ጋሪሞ (MA in TeAm)

**አማካሪዎች**

ሂሩት አምሃ (MA in TeAm)

ሰለሞን ዮሀንስ (MA in TeAm)

**ያስገመገመና ያጠናቀቀ**

ገነት ፈለቀ (MA in TeAm)

**የቡድን(ፓናል) መሪ**

መኩሪያ ላንቃሞ

**ሰዓሊና ዲዛይነር**

ሽመልስ አመያ (BA)



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ትምህርት ቢሮ

## ምስጋና

ይህ መጽሐፍ በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታ ምክረ ሐሳብ መሰረት በኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅተው የቀረቡትን የሥርዓተ ትምህርት መጽሐፍት ማዘጋጃ ሰነዶችን መነሻ በማድረግ በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀ ሲሆን የዝግጅትና የሕትመት ወጪው በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስትና በኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ማረጋገጫ ፕሮግራም-ኢ/GEQIP-E/ ተሸፍኖአል፡፡

በመሆኑም የመጽሐፉን ዝግጅት በገንዘብ፣ በሰው ሃይልና በማቴሪያል፣ ተፈላጊውን መረጃ በመስጠት፣ ተቋማቸውን በመፍቀድ፣ ልምዳቸውንና ዕውቀታቸውን በማጋራት እንዲሁም ሌሎችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለደገፉ አካላት፣ተቋማትና ግለሰቦች ሁሉ ትምህርት ቢሮው ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

## የቅጂ መብት

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት የአዲስ አበባ አስተዳደርና የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ትምህርት ቢሮዎች ናቸው፡፡

© 2014፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ድሞክራሳዊ ሪፓብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር፤ የቅጂ መብት ሙሉ የተከበረ ነው፡፡ ያለፈቃድ ማተም፣ ማባዛት፣ ባልተገባ መንገድ ማከማቸትና በሃርድ ኮፒም ሆነ በሶፍት ኮፒ ማሰረጨት እንዲሁም ላልተገባ ዓላማ መጠቀም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ድሞክራሳዊ ሪፓብሊክ፤ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 410/2004 ቅጂ መብት እና ጥበቃ ደንብ መሰረት ያስቀጣል፡፡

የመጀምሪያ እትም 2016 ዓ.ም

ሲዳማ/ ሃዋሳ

# ማውጫ


| ይዘት | ገጽ |
|---|---|
| ምዕራፍ ፩ የአየር ንብረት ለውጥ---------------------------- | 1 |
| ምዕራፍ ፪ ስነ ቃል---------------------------------------- | 15 |
| ምዕራፍ ፫ ባህል------------------------------------------ | 29 |
| ምዕራፍ ፬ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት---------------------- | 41 |
| ምዕራፍ ፭ ግብርና---------------------------------------- | 53 |
| ምዕራፍ ፮ ስርዓተ ጾታ------------------------------------ | 64 |
| ምዕራፍ ፯ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ------------------------ | 75 |
| ምዕራፍ ፰ ገበያና ግብር----------------------------------- | 85 |
| ምዕራፍ ፱ አካባቢያችን----------------------------------- | 97 |
| ምዕራፍ ፲ አህጉራት ባህሮችና ሐይቆች-------------------- | 109 |

# መግቢያ

ይህ የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪ መማሪያ መጽሀፍ የተዘጋጀው አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ታስቦ ነው፡፡ በመጽሀፉ የተካተቱ ይዘቶች አራቱን የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብና መጻፍን ) እንዲሁም የቃላትና የሰዋስው እውቀቶችን ያመጣጠኑ ናቸው፡፡

መጽሀፉ ቀደም ብሎ ለክፍሉ የተሰናዳውን መርሀ ትምህርት መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሆኖ አስር ምዕራፎችን አካቶ የያዘ ነው፡፡ የየምዕራፉ ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ በሰፈረው ክፍለ ጊዜ ተደራጅተዋል፡፡ የእያንዳንዱ ምዕራፍ ርዕስ ምንባቦችን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ከዚህ የሚመነጩ ተግባራትና መልመጃዎች ቋንቋን ለማስተማር ጥሩ ከመሆናቸው ባሻገር ተማሪዎቹን ከአካባቢያቸው ጋር ለማስተዋወቅ መንገዱን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ተማሪዎች በየደረጃቸው የተለያዩ ባህላዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ፣ እንዲሁም አለም አቀፋዊ ይዘቶችን በአማርኛ ቋንቋ እንዲገልጹ ስለሚጠበቅ፣ የመጽሀፉ ይዘቶችን እንደ መሳሪያ ይጠቀማሉ፡፡ አዘገጃጀቱ ከህይወት ተሞክሮ ጋር የቀረበ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ አዳዲስ ጉዳዮችን ለመማር ግላዊ ገጠመኞቻቸውንና ልምዶቻቸውን እንዲጠቀሙ ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሰረት ችግር ፈቺና አሳታፊ ተግባራትና መልመጃዎች በየምዕራፉ ተካተዋል፡፡ ይህም ተማሪዎች ቋንቋን በተለያየ መንገድ እንዲጠቀሙ ማስቻል ነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## የአየር ንብረት ለውጥ

- የሚጠበቁ ውጤቶች

### ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ምንባብ አዳምጠህ/ሽ ጥያቄዎችን ትመልሳለህ/ሺያለሽ፤
- በማጥበቅ እና በማላላት ሲነበብ አዳምጠህ/ሽ የፍቺ ልዩነት ያላቸውን ቃላት ትለያለህ/ሽ፤
- የዓረፍተ ነገሮችን ተግባራትን ትናገራለህ/ሪያለሽ፤
- የተለያዩ ተረቶችን አንብበህ/ሽ ቁም ነገሮችን ትረዳለህ/ጂያለሽ፤
- የዘመዶችህን/ሽን ስም አንብበህ/ሽ ትረዳለህ/ጂያለሽ፤
- ስዕሎችን በመመልከት የድርጊት ቃላትን ገምተህ/ሽ ትፅፋለህ/ፊያለሽ፤
- ቃላትን በተገቢው ቦታ እያስገባህ/ሽ አንቀፁን ታሟላለህ/ያለሽ፤
- ዘመናዊ ልብሶችን ተመልክተህ/ሽ ወካይ ቃላትን ትፅፋለህ/ፊያለሽ፡፡

## ክፍል አንድ፤ ማዳመጥ

- ምንባቡን አዳምጦ የመረዳት ጥያቄዎችን መስራት

በማጥበቅና በማላላት ሲነበብ አዳምጦ የፍቺ ልዩነት ያላቸውን ቃላት መለየት

### ተግባር አንድ

### የማነቃቂያ ተግባር


የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን ከማዳመጥህ/ሽ በፊት በቃል መልስ/ሽ፡ ፡

- የመሬት መራቆት ምንድነው?
- ደን መትከል ለምን ያስፈልጋል?
- የሁለቱ ስዕሎች ልዩነት ምንድነው?

ሀ



ለ



## 2 አቅርቦት

መምህርህ/ሽ የሚያነቡልህ/ሽን ምንባብ በጥሞና አዳምጥ/ጪ፡፡

### መልመጃዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት በቃል መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ለአየር ንብረት ለውጥ መከሰት አንዱ ምክንያት የደን መጨፍጨፍ ነው፡፡

ለ. በሰደድ እሳት ደኖች ሊጠፉ አይችሉም፡፡

ሐ. ሰዎች ለማገዶ እንጨት ሲቆርጡ በምትኩ አለመትከላቸው አካባቢው እንዲራቆት ያደርጋል፡፡

መ. የመሬት መራቆት የሚያደርሰው ዋነኛው ጉዳት የንፁህ አየር እጥረት ነው፡፡

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጥከው/ሽው ፅሁፍ መሰረት በፅሁፍ መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ሰዎች ደንን በእሳት ለምን ያጋያሉ?

ለ. ደኖች የመሬትን መራቆት እንዴት ይከላከላሉ?

ሐ. ደኖች የሚወድሙባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

መ. በረሃማነት ሲከሰት የሚያመጣቸውን ችግሮች ፃፍ/ፊ፡፡

፫. በሚከተሉት ቃላት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ዓረፍተ ነገር ሰርተህ/ሽ ለመምህርህ/ሽ አሳይ/ዪ፡፡

ምሳሌ፡- ተከሰተ ፤ በደን መጨፍጨፍ ምክንያት የአየር ንብረት ለውጥ ተከሰተ፡፡

ሀ. ማጋየት

ለ. ጨዋማ

ሐ. ጠራርጎ

መ. በረሃ

፬. የደን መጨፍጨፍ በአየር ንብረት ላይ የሚያስከትለውን ችግር በቡድን ተነጋግራችሁ ለመምህራችሁ በፅሁፍ አቅርቡ፡፡

## ተግባር ሁለት

### የማነቃቂያ ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን ከማዳመጥህ/ሽ በፊት በቃል መልስ/ሺ፡፡

- ደን ምንድነው?
- ደኖች ችግር የሚገጥማቸው በምን ምክንያት ነው?

### 2 አቅርቦት

መምህርህ/ሽ የሚያነቡትን ፅሑፍ በጥሞና አዳምጥ/ጪ፡፡

### መልመጃዎች

፩. ባዳመጥከ/ሽው ፅሁፍ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. በአለም ላይ ያሉ ዛፎች ስለችግራቸው ለመወያየት ምን አደረጉ?

ለ. በዛፎች ላይ እየደረሰ ያለው ትልቁ ችግር ምንድነው?

ሐ. የአየር ንብረት ለውጥ ከተከሰተ ምን ምን ችግር ይፈጠራል?

መ. ትልቁ ዛፍ ዋነኛ ጠላታችን ብሎ ያቀረበው ማንን ነው?

ሠ. ሁሉም ዛፎች ቀጭኑ ዛፍ ላይ ያጉረመረሙት ለምንድነው?

ረ. ቀጭኑ ዛፍ እንዴት ሆነን እንደግ አለ?

፪. ከምንባቡ የወጡ ቃላትን መምህርህ/ሽ በማጥበቅ እና በማላላት ሲጠሩ በማዳመጥ የሚሰጡትን ፍቺ ተናገር/ሪ፡፡

ሀ. አለ

ለ. ያሉት

ሐ. ይራባሉ

መ. ጠላት

ሠ. ቀና

፫. ቀጥሎ በዓረፍተ ነገር የገቡትን ቃላት በምሳሌው መሰረት ሲጠብቁ የሚሰጡትን ፍቺ በቡድን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

ምሳሌ፡- አለ = ዮናስ መፅሐፉን ስጠኝ አለ/ተናገረ፡፡ (ሲላላ)

መልስ፤ ዮናሰ ቤት ውስጥ አለ/ መኖሩን፡፡ (ሲጠብቅ)

ሀ. ያሉት = እነከበደ ስብሰባ ላይ ያሉት ሀሳብ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

ለ. ይራባሉ = ገበሬው በርትቶ ካልሰራ ቤተሰቦቹ ይራባሉ፡፡

ሐ. መመንጠር = ደንን መመንጠር ለአየር ንብረት ለውጥ ያጋልጣል፡፡

መ. ጠላት = የኢትዮጵያ ዋና ጠላት ድህነት ነው፡፡

፬.ቀጥሎ የተሰጠህ/ሽን ቃላት ሲጠብቁ የሚሰጡትን ፍቺ በዓረፍተ ነገር አሳይ/ዪ፡፡

ምሳሌ፡- አያት = ዘነበ ትምህርት ቤት ሄዶ ልጁን አያት/ ተመለከታት፡፡

ሀ. ጠላ

ለ. ዋና

ሐ. ገና

መ. ለጋ



## ክፍል ሁለት፤ መናገር

- የዓረፍተ ነገር ተግባራትን መናገር

### የማነቃቂያ ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን ከማዳመጥህ/ሽ በፊት በቃል መልስ/ሺ፡፡

- የዛፎች መመንጠር የሚያስከትለው ጉዳት ምንድነው?

## 2 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበልህ/ሽን ጭውውት በጥሞና ተመልከት/ቺ፡፡

ለምለም እና ግርማ የአንድ መንደር ልጆች ናቸው፡፡ ትምህርት ቤታቸው ከሚኖሩበት መንደር ራቅ ያለ ቦታ ስለሆነ ዘወትር ከትምህርት ቤት ሲመለሱ ትልቅ የዋርካ ዛፍ ዛሬ አላገኙችትም ተቆርጣለች፡፡

ለምለም፤ ወይኔ! ግርማ ተመልከት!

ግርማ፤ ምኑን?

ለምለም፤ አይታይህም እንዴ? የምናርፍባት ዛፍ የለችም፡፡

ግርማ፤ አሀ! አሀ! እውነት ነው ዛፏ የለችም፡፡

ለምለም፤ በቃ የመንደራችን ሰዎች በየጊዜው እየቆረጡ ነው፡፡ ትናንትናም ወንድሜ ገንዘብ ያስፈልገኛል ብሎ ታች ያለውን ዛፍ መንጥሮ ሸጠው፡፡

ግርማ፤ እውነት? ሁሉንም?

ለምለም፤ አዎ! እኔ ግን ደኖችን መመንጠር የአየር ንብረት መለወጥ ይፈጥራል ብሎ መምህራችን ነግረውናል ብዬ ብነግረውም አልሰማኝም፡፡

ግርማ፤ በቃ ይህን ጉዳይ በሰፈራችን ላለው የግብርና ባለሙያ እንንገረውና ዛፎችን መቁረጥ እንደሌለባቸው እና ይልቁን መትከል እንዳለባቸው በትኩረት እንዲሰራ ልናማክረው ይገባል፡፡ በተጨማሪም ህብረተሰቡ ባዮጋዝ እንዲጠቀም ስለ ባዮጋዝ ግንዛቤ እንዲሰጥ ልንነግረው ይገባል፡፡

ለምለም፤ ባዮ ጋዝ ምንድነው? ለአየር ንብረት ለውጥስ ምን አስተዋፅኦ አለው?

ግርማ፤ ባዮጋዝ ማለት ከ2-4 ሜትር የሚሆን ጉድጓድ ተቆፍሮ ከተዘጋጀ በኋላ የከብት እበት በውሃ ተበጥብጦ ለተወሰነ ጊዜ ያለ አየር ታምቆ በሚቆይበት ወቅት የሚፈጠር ኃይል ሰጪ ጋዝ ነው፡፡ ይህንን ጋዝ በቱቦ በማስተላለፍ ለምግብ መስሪያና መብራት ለማብራት ያገለግላል፡፡

ለምለም፤ ስለዚህ ባዮጋዝ ካለ ለምግብ ማብሰያ ዛፍ አይቆረጥም ማለት ነው፡፡

ግርማ፤ በትክክል፡፡

## መልመጃዎች

፩.. ከላይ ጥንድ ጥንድ በመሆን የቀረበውን ጭውውት በመለማመድ ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በቀረበልህ/ሽ ጭውውት መሰረት በቃል መልስ/ሽ፡፡

ሀ. ለምለም“ወይኔ!ግርማ ተመልከት!” ያለችው ምን አይነት ስሜት ተሰምቷት ነው?

ለ. በመልሱ ውስጥ ለምለም ግርማን ምን ምን ጥያቄዎችን ጠየቀችው?

ሐ. “በጣም ጥሩ ሀሳብ ነው!” የሚለውን እና “አይታይህም እንዴ?” የሚለው ሀሳብ የአቀራረብ ልዩነት አለው ?እንዴት?

መ. ለምለም የሚያርፉበት ዛፍ አለመኖሩን ስትነግረው ግርማ ምን አለ?

፫. መምህርህ/ሽ በሰጡት ገለፃ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ጥያቄያዊ፣ ሀተታዊ እና አጋኗዊ በማለት ለይተህ/ሽ ተናገር/ሪ፡፡

ሀ. ኦ! ዛሬ ቀኑ ደስ ሲል!

ለ. ዛሬ ችግኞችህን ውሃ አጠጥተሃል?

ሐ. ተክሎችን መንከባከብ ያስደስተኛል፡፡

መ. ከዛፎች ምን ምን ጥቅም ይገኛል?

ሠ. የት ነበርክ?

ረ. ዛሬ በጊዜ ደረስኩ፡፡

ሰ. ለምለም ስፍራ ማየት አእምሮን ያድሳል፡፡

ሽ. እሰይ! እሰይ! ችግኜ አደገች፡፡

ቀ. አፉ! ተወኝ በቃ!

፬. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን በየተራ እየተጠያየቃችሁ ምላሽ ስጡ፡፡

ምሳሌ፣ 1. ሀ = ዛፍ ቆርጠህ ታውቃለህ?

ለ = ኧረ አላውቅም! በፍፁም ዛፍ ቆርጬ አላውቅም!

ሀ = ተክሎችን ትወዳለህ?

ለ = ______________________________ ፡፡

ሀ = ምን ያህል ችግኝ ተክለህ ታውቃለህ?

ለ = ______________________________ ፡፡

ሀ = ኦ! በጣም ጎበዝ! የተከልካቸውን ችግኞች ውሀ የምታጠጣው መቼ ነው?

ለ = ______________________________ ፡፡

ሀ = በጣም ጎበዝ! አመሰግናለሁ፡፡

ለ = እኔም በጣም አመሰግናለሁ፡፡

## ክፍል ሶስት፤ ማንበብ

- የግል ምንባብ አንብቦ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን መስራት

### የማነቃቂያ ተግባር

የቀረበልህን/ሽን ምንባብ ከማንበብህ/ሽ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

- ውሃ የሚሰጠው ጥቅም ምንድነው?
- ውሃ ባይኖር ኖሮ ህይወት ያለው ፍጡር ምን ይሆን ነበር?

### 2 አቅርቦት

የቀረበልህ/ሽን ምንባብ በጥሞና አንብብ/ቢ፡፡

**የምንጭ ውሃ ፍለጋ**

በአንድ አካባቢ የነበረው ውሃ በሙሉ በማለቁ ፍጥረታት በውሃ ጥም ማለቅ ጀመሩ፡፡ አንዳንድ ፍጥረታት ደግሞ በየቦታው ወድቀው ሲያጣጥሩ ይታዩ ጀመር፡፡ በፊት ምድርን አስጊጠዋት የነበሩት ተክሎች እያደር ደረቁ፡፡ ዛፎች፣ ሳሮች፣ ፍራፍሬዎች፣ አትክልቶች እና ቅጠላ ቅጠሎች፣ ጫካዎች፣ ደኖች ቀስ በቀስ በውሃ ማጣት የተነሳ ከምድር መጥፋት ጀመሩ፡፡ ምድር ለዐይን ደስ የማትል ስፍራ ሆነች፡፡ ከእለታት አንድ ቀን በመንደሯ የሚኖሩ ሦስት ልጆች በውሃ ጥም ከምናልቅ ውሃ ወዳለበት አካባቢ ለምን አንሄድም? በማለት ለጉዞ ተዘጋጁ፡፡ የመንደሩ ነዋሪዎች ጉዟቸው የተሳካ እንዲሆን መርቀው ሸኗቸው፡፡ ልጆቹም በቀን በማታ እየተጓዙ ውሃ ፍለጋቸውን ቀጠሉ፤ ነገር ግን ምንም ውሃ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡

አንድ ቀን ከረጅም አድካሚ ጉዞ በኋላ ሦስቱም ጓደኞቾ እረፍት ለማድረግ አንድ ስፊ ዋሻ ውስጥ ገቡ፡፡ እሳት አንድደው ስለ ቤተሰባቸው፣ስለጉዟቸው ይጫወቱ ነበር፡፡ "ጓደኞቼ ምንም ውሃ ማግኘት አልቻልንም፡፡ ለዚህ ሁሉ ድርቅ እና የአየር ንብረት ለውጥ ተጠያቂው እኛው ራሳችን ነን" ሲል ሁለቱም ጓደኞቹ "እንዴት?"በማለት በአንድነት ጮኸው ጠየቁት፡፡ አያችሁ ይኽ ድርቅ ለምን የተከሰተ መሰላችሁ? በፊት አካባቢያችን በዛፎች እና በደን የተሞላ ነበር፡፡ የነበሩትን ደኖች ማን አቃጠላቸው? በዙሪያችን የነበሩትን ዛፎች ማን ጨፈጨፋቸው? ከብቶችን በደኖች አካባቢ ስናሰማራ ለጋ ተክሎችን አይሰባብሩምን የዛፎችን ቅጠሎችን አያራግፉም፡፡

ደን ከሌለ ዝናብ የለም፤ ዝናብ ከሌለ ሰብል የለም፡፡ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ንፁህ አየር የለም! እነዚህ ከሌሉ ህይወት የለም! ስለዚህ አካባቢያችንን እንደ ድሮው ለመመለስ ጥለን መሰደድ ሳይሆን ተመልሰን አካባቢያችንን ወደ ቀድሞዋ ይዞታዋ መመለስ አለብን በማለት ጓደኞቹን አሳምኖ ወደ አካባቢያቸው ተመለሱ፡፡

(ጥበበ ፍቃዱ(አቅሎስ)፣ ባለታክሲው ጥንቸል፣ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ ኀ/የተ/ማ 2012፣ ገጽ 111-112)

## መልመጃዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት በቃል መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ህይወት ያለው ፍጡር ውሃ ካላገኘ ይሞታል፡፡

ለ. ለአየር ንብረት ለውጥ ተጠያቂ የሚሆነው የሰው ልጅ ነው፡፡

ሐ. ደኖች ሲቃጠሉ የአየር ንብረት ለውጥ ሊከሰት ይችላል፡፡

መ. ከብቶች በደን ውስጥ ሲሰማሩ በተክሎች ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡

ሠ. ደን በሌለበት አካባቢ ዝናብ ሁል ጊዜ ይጥላል፡፡

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በፅሁፍ መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ተክሎች፣ ሳሮችና ዛፎች የሚደርቁት ለምንድነው?

ለ. በመንደሩ የነበሩ ሶስት ልጆች የወሰኑት ውሳኔ ምንድነው?

ሐ. ከሶስቱ ጓደኞች አንደኛው ያመጣው ሀሳብ ምንድነው?

መ. ዝናብ ከሌለ ሰብል የለም፤ ህይወትም የለም የተባለው ለምንድነው? በምሳሌ አስደግፈህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡

ሠ. ምድር ለዐይን ደስ የማትል ስፍራ የሆነችው በምን ምክንያት ነው?

፫. በአካባቢህ/ሽ ድርቅ ቢከሰት ምን ታደርጋለህ/ታደርጊያለሽ? በቡድን ተወያዩና በምሳሌ አስደግፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

## ተግባር ሁለት

## የዘመዶቻቸውን ስም አንብቦ መናገር

### የማነቃቂያ ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ከማንበብህ/ሽ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎችን በቃል መልስ/ሺ፡፡

- ልጆች ወፎች የት እንደሚኖሩ ታውቃላችሁ?
- ከማን ከማን ጋር ነው የምትኖረው/ሪው?

### 2 አቅርቦት

የቀረበውን ምንባብ በጥሞና አንብብ/ቢ፡፡

### የአዕዋፍ ቤተሰብ ስሞች እና ስራዎቻቸው

በአንድ እጅግ በጣም ትልቅ በሆነ ዛፍ ላይ ከቤተሰቦቿ ጋር የምትኖር ትንሽ ወፍ ነበረች፡፡ የወፏ ቤተሰብ ቁጥር ብዙ ነበር፡፡ አባት ወፍ፣ እናት ወፍ፣ እህት ወፍ፣ ወንድም ወፍ፣ አጎት ወፍ፣ አክስት ወፍ፣ የወንድ አያት፣ የሴት አያት፣ አማች ወፍ፣ ምራት ወፍ እና ሌሎች የቅርብ ዘመድ ወፎች ሁሉ በአንድ መንደር ይኖራሉ፡፡ ከእነዚህ ሁሉ የመጨረሻ ልጅ እሷ ናት፡፡ በዚህ የተነሳ ትንሿ ወፍ ትባላለች፡፡

የእነዚህ ወፎች አኗኗር ወደ ልዩ ልዩ ዛፎች በመብረር ጥራጥሬ ማምጣት እና መብላት ሲሆን ሁሉም ወፎች የየራሳቸው የሆነ ስራ ድርሻ አላቸው፡፡ የወፎቹን ማደሪያ ጎጆዎች በሳር እየሰራ በየጊዜው ጥገና የሚያደርገው አባት ወፍ ነው፡፡

ወንድም ወፍ ደግሞ ወደ ልዩ ልዩ ቦታዎች፣ ጫካዎች እና ሜዳዎች እየሄደ ለቤተሰቡ የሚበቃውን ጥራጥሬ ሰብስቦ ያመጣል፡፡ እናት ወፍ ደግሞ ትናንሽ ወፎችን በመንከባከብ እና በማሳደግ ሀላፊነቷን ትወጣለች፡፡ ሰሞኑን ግን በአቅራቢያቸው የሚገኘው ጫካ በሰደድ እሳት በመቃጠሉ ተቸግረዋል፡፡

ስለዚህ ለብዙ ጊዜ የሚሆን ምግብ ለማምጣት ሁሉም ወፎች ወደ ሩቅ ቦታ ለመሄድ ሲነሱ መብረር የማትችለው ትንሿ ወፍ ጎጆቸውን እንድትጠብቅ ታዘዘች፡፡ ትንሿ ወፍ ጎጆቸውን እየጠበቀች ሳለ ድንገት ወደ ውጭ ስትመለከት አቶ ንፋስን አየችው፡፡ “አቶ ንፋስ ጎጆ መጠበቅ ስለሰለቸኝ እንድበር እርዳኝ?” ስትለው “ነይ ምን ቸገረኝ” ብሎ ይዟት እያበረረ ከቤቷ አርቆ ወሰዳት፡፡ ብዙ ርቀት ካበረራት በኋላ አቶ ንፋስ ድንገት ጥሏት ሲጠፋ ያለ ንፋስ መብረር ስላልቻለች ወደ ምድር ወድቃ፣ እግሯ ተሰበረ፡፡

ጥበቡ ፍቃዱ (አቅሎስ)፣ዳንሰኞች ዋልያዎች፣ 2012፣ ገፅ-25

## መልመጃዎች

፩. የሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልሺ/ስ፡፡

ሀ. ትንሿ ወፍ የምትኖረው ከእናት እና ከወንድሟ ጋር ብቻ ነው ፡፡

ለ. የትንሿ ወፍ አባት የስራ ድርሻ ምግባቸውን ማምጣት ነው፡፡

ሐ. የትንሿ ወፍ እናት ቤተሰቡን የመንከባከብ ሀላፊነት አለባት፡፡

መ. በአካባቢያቸው በተፈጠረው ሰደድ እሳት የወፏ ቤተሰብ ተቸግረዋል፡፡

ሠ. አቶ ንፋስ ትንሿን ወፍ ወደ ቤቷ መልሷታል፡፡

፪ . የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በፅሁፍ መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ባለታሪኳ ወፍ ትንሿ ተብላ የተጠራችበትን ምክንያት ከምንባቡ ተመልክተህ/ሽ በንባብ አቅርብ/ቢ፡፡

ለ. ወፎቹ ወደ ተለያዩ ቦታ የሚበሩት ምን ለማምጣት ነው?

ሐ. ከትንሿ ወፍ ጋር አብረው የሚኖሩት እነማን ናቸው?

መ. ትንሿን ወፍ ከቤቷ አርቆ የወሰዳት ማነው?

ሠ. በትንሿ ወፍ ላይ ጉዳት የደረሰባት ለምንድነው?

፫. በ "ሀ" ስር የተዘረዘሩት ሀረጋትን በ "ለ" ስር ከቀረበው ፍቺያቸው ጋር አዛምድ/ጂ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ___1. የአባት/ የእናት እህት | ሀ. አክስት |
| ___2. የእናት/ የአባት እናት | ለ. አጎት |
| ___3. የአባት/ የእናት ወንድም | ሐ. ሴት አያት |
| ___4. የአባት/ የእናት አባት | መ. ወንድ አያት |

፬. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. የቤተሰቦችህን/ሽን ስም እና የስራ ድርሻ ፃፍ/ፊ እና ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ አንብብ/ቢ፡፡

ለ. በቤተሰብህ/ሽ ውስጥ ትልቁን የስራ ድርሻ የሚወጣው ማን ነው? በማስረጃ አስደግፊህ/ሽ አንብብ/ቢ፡፡

ሐ. ከቤተሰቦችህ/ሽ መካከል ትንሹ የስራ ድርሻ ያለው ማን ነው?

## ክፍል አራት፤ መፃፍ

- ስዕሎችን መሰረት አድርጎ መፃፍ

### አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበው ስዕል በአትኩሮት ተመልከት/ቺ፡፡



ስዕል 1



ስዕል 2



ስዕል 3



ስዕል 4

## ② መልመጃዎች

፩. ከላይ የቀረበውን ሥዕል በማየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ስዕል አንድ የሚያሳየን ምንድነው?

ለ. ስዕል ሁለት የሚያሳየን ስለምንድነው?

ሐ. ስዕል ሦስት የሚያሳየን ምንድነው?

መ. ስዕል አራት የሚያሳየን ስለምንድነው?

፪. የሚከተሉትን ቃላት በተገቢው ቦታ በማስገባት ከስር የቀረበውን አንቀፅ አሟላ/ዪ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ፀሐይዋ | ፈረስ | ዛፍ |
| ለምለም | አውሬ | የሚቆፍሩት |

አንድ ቀን ጠዋት አንድ ሽማግሌ ገበሬ___1___ለመትከል ይቆፍሩ ነበር፡፡ ___2___ለማደን የሚሄድ አንድ ወጣት ሹም በ ___3___ እየጋለበ መጣ እና አጠገባቸው ሲደርስ ቆሞ ይመለከት ጀመር፡፡ ቀጥሎም አባቴ በዚህ ዕድሜዎት ምን ሊተክሉ ነው ___4___ አላቸው፡፡ ሽማግሌውም ዛፍ ልተክል አሉት፡፡ እርሱም አሁን አርጅተዋል ዛፍ እስኪያድግ ብዙ ጊዜ ይወስዳል ለምን ይደክማሉ? አላቸው፡፡ ሽማግሌውም ልጄ አይታይህም ___5___ ስታቃጥል፤ የአየር ንብረት ለውጥ___6___ የነበረው መሬት ተራቁቶ ዝናቡ የሸሸን ለምን ይመስልሃል? በአካባቢያችን ያሉት ዛፎች እና ደኖች ስለጠፉ ነው፡፡ እኔ ባልደርስበትም ለልጅ ልጄ ይሆናል አሉት፡፡

(ኢትዮጲስ፣የልጆች ተረት፣ ቁጥር 2፣ ገፅ-30)

፫. ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ስለ ዛፍ ጥቅም ፃፉ፡፡

## ክፍል አምስት፤ ቃላት

• ስዕልን መሰረት አድርጎ ወካይ ቃላት መጻፍ

### የማነቃቂያ ተግባር

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጪ፡፡

- በጣም ቅዝቃዜ በሆነ ሰዓት ምን አይነት ልብስ ይለበሳል?
- ዘመናዊ ልብስ የሚባለው ምን አይነት ልብስ ነው?

## 2 አቅርቦት

የሚከተሉትን ሥዕሎች በአትኩሮት ተመልከት/ቺ፡፡

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

መ. 

### መልመጃዎች

፩ . የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሥዕሉን እያየሽ/ህ መልሺ/ስ፡፡

ሀ. በሥዕል “ሀ” ላይ የተመለከትከው/ሽው የልብስ ዓይነት ምን ይባላል?

ለ. በሥዕል “ለ” ላይ የተመለከትከው/ሽው የልብስ ዓይነት ምን ተብሎ ይጠራል?

ሐ. በሥዕል “ሐ” ላይ የተመለከትከው/ሽው የልብስ ዓይነት ምን ይባላል?

መ. በሥዕል “መ” የተመለከትከው/ሽው የልብስ ዓይነት ምን ይባላል?

፪. ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ በመጠያየቅ በሥዕሉ ከተመለከታችሁት ሌላ የዘመናዊ ልብስ ስሞችን ዘርዝሩ፡፡

1. ______________________ 3. ______________________

2. ______________________

# ምዕራፍ ሁለት

## ስነ ቃል

● የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ያዳመጥሽ/ከውን ስነ-ቃል ወይም ተረቶችን ትተርኪያለሽ/ካለህ፤
- የደስታ ስሜቶችን በተገቢው ቋንቋ ትናገሪያለሽ/ራለህ፤
- መመሪያዎች ተከትለሽ/ህ ማንበብን ትለማመጃለሽ/ዳለህ፤
- ተራ ዓረፍተ ነገሮችን አንብበሽ/ህ ትረጂያለሽ/ዳለህ፤
- ሀረጎችን ከፍቺያቸው ጋር አዛምደሽ/ህ ዓረፍተ ነገር ትፅፊያለሽ/ፋለህ፤
- የባህላዊ መሳሪያዎች ጥቅም በቃላት ትገልጪያለሽ/ጣለህ፤
- ስዕሎችን ተመልክተሽ/ህ ወካይ ቃላትን ትጠሪያለሽ/ራለህ፡፡

## ክፍል አንድ፤ ማዳመጥ

- ያዳመጡትን ታሪክ መልሶ መተረክ

### የማነቃቂያ ተግባር

"ዶሮዎች መሬት ለምን ይጭራሉ?" የሚለውን ተረት ከማዳመጥሽ/ህ በፊት ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጪ/ጥ፡፡

ሀ. ስለ አፈታሪክ የምታውቂው/ቀውን ተናገሪ/ር/፡፡

ለ. ተረት ሲተረት አዳምጠሽ/ህ ታውቂያለሽ/ህ?

ሐ. የምታዪ/የው ስዕል ምን ያሳያል?



## 2 አቅርቦት

ቀጥሎ መምህርሽ/ህ "ዶሮዎች መሬት ለምን ይጭራሉ?" የሚለውን ምንባብ ሲያነቡልሽ/ህ በጥሞና አዳምጪ/ጥ፡፡

### መልመጃዎች

፩. ባዳመጥ ሽው/ከው ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልሺ/ስ፡፡

ሀ. በጥንት ጊዜ ዶሮዎች እንደ ጭልፊቶች ይበሩ ነበር፡፡
ለ. ክንፍ መስፊያውን መርፌ የተዋሱት ዶሮዎቹ ናቸው፡፡
ሐ. በዶሮዎችና በጭልፊቶች መካከል ጥል ተነስቷል፡፡
መ. ዶሮዎች ጭልፊቶችን ሲያዩ ይደበቃሉ፡፡

፪. ባዳመጥሽ/ከው ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ስጪ/ጥ፡፡

ሀ. ጭልፊቶች መብረር የቻሉት በምንድነው?

ለ. ዶሮዎች መርፌን የተዋሱት ለምንድነው?

ሐ. ዶሮዎች ለምን መሬት ይጭራሉ?

መ. ዶሮዎች ጭልፊቶችን ሲያዩ የሚደበቁት ለምንድነው?

፫. ያዳመጥሽ/ከው ተረት ለክፍል ጓደኞችሽ/ህ በቃል ተርኪ/ክ፡፡

፬. አንድ የምታውቂው/ቀውን ተረት ለክፍል ጓደኞችሽ/ህ ተናገሪ/ር፤ ሌሎቹም ሲናገሩ በጥሞና አዳምጪ/ጥ፡፡

## ተግባር ሁለት

### የማነቃቂያ ተግባር

አንበሳ እና ደቦሉ የሚለውን ተረት ከማዳመጥሽ/ህ በፊት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጪ/ጥ፡፡

- የምታውቂው/ቀውን ስለ ዱር አራዊት የተነገረ ተረት ተናገሪ/ር፡፡
- የራሳችን ያልሆነን ነገር የኛ ነው ማለት ተገቢ ነውን?

## 2 አቅርቦት

መምህርሽ/ህ “አንበሳና ደቦሉ” የሚለውን ምንባብ ሲያነቡልሽ በጥሞና አዳምጪ/ጥ፡፡

### መልመጃዎች

፩. በምንባቡ መሰረት የሚከተሉት ጥያቄዎች የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልሺ/ስ፡፡

ሀ. የአንበሳው ደቦል የሚውለው ከአህዮች ጋር ነው፡፡

ለ. የአንበሳውን ደቦል የሚያደንቁት አንበሶች ናቸው፡፡

ሐ. አህያው የአንበሶችን ድምፅ ይለማመዳል፡፡

መ. የአንበሳው ደቦል የራሱ ያልሆነ ባህርይን ከአህዮቹ ኮርጇል፡፡

፪. የሚከተሉትን ቃላት ካነበብህ/ሽ በኋላ በተገቢ ቦታቸው በማስገባት አንቀጹን አሟላ/ዪ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ደቦል | እንሰሳት | በመኮረጅ |
| መደነቅ | ያደንቁታል | ከአህያዎች |
| ባህርይ | ማናፋታቸው | |

መሞገስና__1__የሚወድ አንድ ትንሽ የአንበሳ __2__ከቢጤዎቹ አንበሶች በመራቅ ሌሎች የተናቁ __3__ጋር ጓደኝነት ይመሰርታል፡፡ይህ ደቦል የአህዮችን__4__መቅዳት ይጀምራል፡፡ አነጋገራቸውን፤ __5__እና አረማመዳቸውን ሁሉንም ነገር__6__ልክ እንደ አህዮች መሆን ይጀምራል፡፡

፫. ያዳመጥሽው/ከውን ታሪክ ለክፍል ጓደኞችህ መልሰሽ/ህ ተናገር/ሪ፡፡



## ክፍል ሁለት፤ መናገር

- የደስታ ስሜቶችን በተገቢው ቋንቋ መግለፅ

### ተግባር አንድ

**የማነቃቂያ ተግባር**

ቀጥሎ የቀረበውን እንኪያ ሰላንቲያ ጥንድ ጥንድ በመሆን ለክፍሉ አቅርቡ፡፡

አበዛሽ፤ እንኪያ ሰላንቲያ
ብሩክ፤ በምንቲያ
አበዛሽ፤ በጋሪ
ብሩክ፤ ምን አለ በጋሪ?
አበዛሽ፤ ምን ጊዜም ደስ ይላል ጎበዝ ተማሪ፡፡

### 2 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበውን ጭውውት ጥንድ ጥንድ በመሆን አቅርቡ፡፡

ሙሉጌታ ከስራ ወደ ቤቱ ሲመለስ ከሩቅ የተመለከታትን ልጅ በፈገግታ እያየት እጁን ዘርግቶ በፍጥነት ወደ እሷ ተራመደ፡፡

ሙሉጌታ ፤ሰብልዬ በጣም ትልቅ ልጅ ሆነሻል! ድሮ እናንተ ቤት እያለሁ

ህፃን ልጅ ነበርሽ! ይገርማል! እንዴት ነሽ?

ሰብለ፤ ደህና ነኝ አንተ እንዴት ነህ?

ሙሉጌታ፤ ደህና ነኝ! ትምህርት እንዴት ነው?

ሰብለ፤ ውይ! ተመረቅኩኝ እኮ!

ሙሉጌታ፤ ኧረ! እንኳን ደስ አለሽ!

ሰብለ፤ እንኳን አብሮ ደስ አለን!

## 3 መልመጃ

፩. የቀረበውን ጭውውት መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ ስጪ/ጥ፡፡

ሀ. ሙሉጌታ የሰብለን መመረቅ ሲያውቅ ደስታውን ለመግለፅ ምን አላት?

ለ. ሰብለ ምን አይነት ምላሽ ሰጠችው?

ሐ. ጥንድ ጥንድ በመሆን ከላይ ያለውን ጭውውት ተለማምዳችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

## ተግባር ሁለት

- **የተለያዩ አውዶችን ተጠቅሞ መናገር**

### የማነቃቂያ ተግባር

ለበዓላት ጊዜ የምትለዋወጪ/ጠው የመልካም ምኞት መግለጫ ተለዋወጡ፡፡

## 2 አቅርቦት

የቀረበልሽ/ህን ጭውውት በአትኩሮት ተመልከቺ/ት፡፡

ፍቅሬ የሶስተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ዛሬ ከወትሮው በጣም ደስ ብሎታል፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ ከቤት ሲወጣ መምህሩን በር ላይ አገኛት፡፡

ፍቅሬ፤ መምህርት መምህርት!

መምህርት፤ አቤት! ፍቅሬ ደህና አደርክ?

ፍቅሬ፤ ደህና! መምህርት ደህና!

መምህርት፤ ዛሬ በጣም ደስ ብሎሀል?

ፍቅሬ፤ አዎ መምህር እናቴ በጣም ትንሽ ልጅ ወለደችልን!

መምህርት፤ ውይ! እንኳን ደስ አለህ!

**ፍቅሬ፤** እንኳን አብሮ ደስ አለን!

**መምህርት፤** በጣም ደስ ይላል ልግባና ልጠይቃታ?

**ፍቅሬ፤** እሺ እንግባ፡፡ ይህችት እማማ

**መምህርት፤** እንኳን ፈጣሪ ረዳሽ!

**የፍቅሬ እናት፤** ፈጣሪ ይመስገን! በሰላም ተገላገያለሁ፡፡

**መምህርት፤** እየረፈደ ስለሆነ ልንሄድ ነው፡፡ ፈጣሪ ያሳድግልሽ!

**የፍቅሬ እናት፤** አሜን!

## 3 መልመጃ

፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው ጭውውት መሰረት መልሺ/ስ፡፡

ሀ. ከላይ የቀረበውን ጭውውት ከመምህራችሁ ጋር በመሆን ሶስት ሆናችሁ አቅርቡ፡፡

ለ. መምህርቷ ፍቅሬን እንኳን ደስ አለህ! ስትለው ምን በማለት መለሰላት?

ሐ. መምህርቷ የፍቅሬን እናት ገና ስታያት ምን አለቻት?

መ. የፍቅሬ እናት ምን ብላ መለሰችላት?

ሠ. ከላይ ያለውን ጭውውት በቡድን ተከፋፍላችሁ ቤታችሁ ተለማምዳችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ::

፪. ለአዲስ ዓመት መግቢያ ሰዎች ሲገናኙ ምን ይባባላሉ? ከጓደኞችሽ/ህ ጋር ተነጋገሪ/ር፡፡

## ክፍል ሶስት፤ ማንበብ

- ተራ ዓረፍተ ነገርን ማንበብ

### ተግባር አንድ

### የማነቃቂያ ተግባር

"የፊቼ በዓል ታሪካዊ አመጣጥ" የሚለውን ምንባብ ከማንበብሽ/ህ በፊት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልሺ/ስ፡፡

- በሀገራችን ምን አይነት በዓላት ይከበራሉ?
- በጣም የምትወጂ/ደው በዓል የቱ ነው?

የቀረበውን ስዕል በአትኩሮት ተመልክተሽ/ህ ስዕሉ ስለምን እንደመሚገለልጽ ገምቺ/ት፡፡



## 2 አቅርቦት

፫. ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ መምህርሽ/ህ ሲያነብልሽ/ህ መልሰሽ/ህ አንብቢ/ብ፡፡

### የፊቼ በዓል ታሪካዊ አመጣጥ

ፊቼ የሲዳማ ብሄር የዘመን መለወጫ በዓል ሲሆን ሰፋ ያለ ባህላዊና ማህበራዊ ትርጉም ያለው ነው፡፡ የፊቼ በዓል የራሱ ታሪካዊ አመጣጥ፣ የአከባበር ሥነ ሥርዓት ፣ አብረውት የተቆራኙ ባህላዊ እሴቶችና እምነቶች እንዲሁም ጨዋታዎች ያሉት ነው፡፡

የፊቼ በዓል ታሪካዊ አመጣጥ አልፎ አልፎ የተለያየ መነሻ እንዳለው ቢነገርም አዛውንቶች በአመዛኙ የሚስማሙበት አቅጣጫ ግን አንድ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም የፊቼ ምንነቱ ወይም ትርጉሙ ከአንዲት የሲዳማ ሴት ስም እና ድርጊት ጋር ስለመያያዙ፣ የፊቼ በዓል ሃዌላ ስለ መጀመሩና ከዚያም ወደ ተቀሩት የሲዳማ ክፍሎች ስለመስፋፋቱ ነው፡፡ በአፈ-ታሪክ እንደሚወሳው ፊ ቼ የሚል ቃል መነሻው ፊቼ /አንዳንዴ ፊቾ/ ከምትባል ሴት ነው፡፡ ይህች ሴት ወላጆቿ እንደሞቱባትና በየአመቱ ለወንድሞቿ የባህል ምግብ “waasa” እያመጣችየቃዋዶ እለት ትጠይቃቸው እንደነበር ይነገራል፡፡ በቅቤ የተዘጋጀውን ቆጮ “buurisame” ጎረቤት ተሰብስቦ ይጋበዝ እንደነበር ይወሳል፡፡ በአፈ-ታሪክ መሰረት ምግቡ ይበላ የነበረው ማታ እንደነበር ሲነገር ይህንን በተደጋጋሚ ስትፈፅም ቆይታ ፊቼ ትሞታለች፡፡ ቀደም ሲል የግብዣው ታዳሚ የነበሩ ሰዎች እርሷ ከቀረች በኋላ የምትመጣበት ጊዜ ጠብቀው ሲያጡ በራሳቸው ለመደገስ ይስማማሉ፡፡ የግብዣውንም ስያሜ በስሟ ፊቼ አሉት፡፡ ዝግጅቱም ዓመት እየጠበቀ እየቀጠለ ሄደ የህዝቡ አመታዊ በዓል ሆነ፡፡ ይህም የፊቼ በዓል ታሪካዊ አመጣጥ መሰረት እንደሆነ ይነገራል፡፡

ፊቼ የተጀረው ሀዌላ እንደነበር ሲነገር ለዚህም ምክንያቱ ፊቼ የሀዌላ ጎሳ ስለነበረች ሳይሆን፣ ሀዌላዎች ለአዲስ ዓመት ዋዜማ የቃዋዶ እለት ተሰብስበው ጨረቃ ልትታይ አንድ ቀን ሲቀራት ማለትም በዲማ ወይም በጨለማ ዕለት የፊቼ በዓል ያከብሩ እንደነበረ ይነገራል፡፡ በማግስቱ ግን ጨረቃ ስለምትታይ የጫንባላላ በዓል ሆኖ ይከበር እንደነበር ይወሳል፡፡

(ምንጭ፤የሲዳማ ብሄራዊ ታሪክ፤ሀዋሳ፣የካቲት 2003 ዓ.ም፣ ገፅ 306)

## 3 መልመጃዎች

፩. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት በቃል መልሺ/ስ፡፡

ሀ. ፊቼ የሲዳማ ብሄር ዘመን መለወጫ ባህል ነው፡፡

ለ. የፊቼ ትርጉሙ ከአንዲት የሲዳማ ሴት ስምና ድርጊት ጋር የተያያዘ ነው፡

ሐ. ፊቼ የምትባለው ሴት ወላጆቿ “waasa” ታመጣላቸው ነበር፡፡

መ. በታሪኩ መሰረት ምግብ የሚበላው ማታ ነው፡፡

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በፅሁፍ መልሺ/ስ::

ሀ. ፊቼ የምትባለው ሴት በቅቤ የተዘጋጀውን ቆጮ የምታበላው ለምንድነው?

ለ. የፊቼ በዓል ታሪካዊ አመጣጥ አባቶች የሚስማሙበት አቅጣጫ ምንድነው?

ሐ. ፊቼ ስትሞት የግብገዋው ታዳሚዎች ምን ማድረግ ጀመሩ?

፫. በአካባቢሽ/ህ ምን አይነት በዓላት ይከበራሉ? ቤተሰብሽ/ህን ጠይቀሽ/ህ ለክፍል ጓደኞችሽ/ህ ተናገሪ/ር::

## ተግባር ሁለት

### የማነቃቂያ ተግባር

"እናትና ልጅ" የሚለውን ምንባብ ከማንበብሽ/ህ በፊት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጪ/ጥ፡፡

- ልጆች ጎበዝ ተማሪ እንዲሆኑ ምን ማድረግ አለባቸው?
- ወላጆቻችንን ምን አይነት ስራ ማገዝ አለብን?

## 2 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበልሽ/ህን ምንባብ በጥሞና አንብብ/ቢ፡፡

### እናትና ልጅ

እናትና ልጅ በአንድ ደሳሳ ጎጆ ቤት ውስጥ አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ልጁ በጣም ረባሽ ነበረ፡፡ በመሆኑም እናቲቱ በጣም ትማረር ነበር፡፡ ሁል ጊዜ ፊቷ አስቀምጣ ትመክረው ነበር፤ እርሱ ግን የእናቱን ምክር ስለማያዳምጥ ሁል ጊዜ እናቱን ከሰው ጋር ያጣላት ነበር፡፡ ከዚያም እናቱ ከብዙ ሃሳብ በኋላ ትምህርት ቤት አስገባችው፡፡ እርሱም ቀስ በቀስ ተለወጠ፡፡በትምህርት ቤት ባገኘው አስደናቂ ውጤትም መምህራን ሁሉ ተደሰቱ፡፡ እርሱም በጣም ደስ አለው፡፡ በአመቱ መጨረሻ ከክፍል ሁሉ አንደኛ ወጥቶ ተሸለመ፡፡ እናቱም ሽልማት ገዝታ ጠበቀችውና ከትምህርት ቤት ሲመለስ ሽልማቱን ሰጠችው፡፡ ይህ ሁሉ ውጤት የእናቴ ምክር ነው በማለት እናቱን አመሰገነ፤ ይቅርታም ጠየቃት፡፡

## 3 መልመጃዎች

፩. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሺ/ስ፡፡

ሀ. እናትየው በልጁ የተማረረችው ለምንድነው?

ለ. እናትየው ከብዙ ሃሳብ በኋላ ምን አደረገች?

ሐ. ልጁ ትምህርት ቤት ሲገባ ምን አደረገ?

መ. ትምህርት ቤቱ ለልጁ ምን ሰጠው?

፪. የሚከተሉትን ቃላት መሰረት በማድረግ ጅምር ተራ ዓረፍተ ነገር በመጨረስ ለክፍል ጓደኞችሽ/ህ አንብቢ/ብ፡፡

ምሳሌ፣ **መከረችው፤** አሸናፊን እናቱ መከረችው፡፡

ሀ. ትምህርት ቤት፤ ዮሴፍ ትምህርት ቤት ____________፡፡

ለ. ሽልማት፤ ለአብይ ሽልማት ____________ ፡፡

ሐ. መፅሀፍ፤ ወንድሜ መፅሀፍ ____________፡፡

መ. ምክር፤ ለእህቴ ምክር ____________ ፡፡

ሠ. ይቅርታ፤ ተማሪው መምህሩን ይቅርታ ____________ ፡፡

፫. በባህርያቸው አስቸጋሪ የሆኑ ልጆች ምን መደረግ አለባቸው? ወላጆችሽ/ን በመጠየቅ ፃፊ/ፍ እና ለክፍል ጓደኞችሽ/ህ አንብቢላቸው/ብላቸው፡፡

፬. ጥፋት አጥፍተሽ/ህ ወላጆችሽን/ህን ካስቀየምሽ/ክ ምን ማድረግ አለብሽ/ህ? በቡድን ተወያዩ እና ለክፍሉ በንባብ አቅርቡ፡፡



## ክፍል አራት፤ መፃፍ

- ጅምር ሀሳቦችን አሟልቶ መፃፍ

### የማነቃቂያ ተግባር

፩. ከዚህ በታች በቀረበው ፅሁፍ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልሺ/ስ፡፡

**አስቴር፤** በጠዋት ተነስተህ ምን አድርገህ መጣህ ?

**በየነ፤** ውሃ ከምንጭ ቀድቼ ነው የመጣሁት፤ አንቺስ ምን ሰራሽ ?

**አስቴር፤** እኔም ቡና አፍልቼ ነው የመጣሁት፡፡

**በየነ፤** በጠዋት ተነስተን ቤተሰቦቻችንን መርዳታችን ጥሩ ነው፡፡

**አስቴር፤** በትክክል!

## 2 መልመጃዎች

፩. ሀ. አስቴር በየነን የጠየቀችው ጥያቄ ምንድነው?

ለ. በየነ በጠዋት ተነስተን ምን ማድረግ አለብን አለ?

፪. ቀጥሎ የቀረቡትን ጅምር ሀረጎች አሟልተህ/ሽ ፃፍ/ፃፊ፡፡

ምሳሌ፣ ጠዋት ከመኝታዬ ስነሳ ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን እበላለሁ፡፡

ሀ. አልማዝ ጎበዝ ተማሪ ስለሆነች ______________________________፡፡

ለ. አስቴር በጠዋት ተነስታ______________________________፡፡

ሐ. እጅን አለመታጠብ ለኮቪድ ______________________________፡፡

መ. የእጅ እና የእግር ጥፍር ሁልጊዜ______________________________፡፡

ሠ. አለሚቱ ቡና ከገበያ ______________________________፡፡

ረ. እናቴ እንጀራ ______________________________፡፡

ሰ. አስተማሪያችን የቤት ስራ ______________________________፡፡

ሸ. ዛሬ በጠዋቱ ______________________________፡፡

፫. በ "ሀ" ስር ያሉትን ጅምር ሀረጋት በ "ለ" ስር ካሉት ሀሳቦች ጋር በማዛመድ ዓረፍተ ነገር መስርተህ/ሽ ፃፍ/ፃፊ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ________ 1. አስቴር ገበያ ሄዳ | ሀ. ወደ እርሻ ሄደ፡፡ |
| ________ 2. ከበደ በሳሙና | ለ. የቤት ስራ እያረመች ነው፡ |
| ________ 3. ገበሬው ሞፈርና ቀንበር | ሐ. ሽንኩርት ገዛች፡ |
| ________ 4. መምህርቷ የሰጠችውን | መ. ጊዜውን በትክክል ይጠቀማል፡፡ |
| ________ 5. ጎበዝ ተማሪ | ሠ. ልብሱን አጠበ፡፡ |

፬ . በአካባቢሽ/ህ የሚነገሩ ሶስት እንቆቅልሾችን ጠይቀሽ/ህ ፃፊ/ፍ እና ለክፍል ጓደኞችሽ/ህአቅርቢ/ብ፡፡

## ክፍል አምስት፣ ቃላት

- የባህላዊ መሳሪያዎች ስሞች እና አገልግሎታቸውን መለየት

## 1 አቅርቦት

፩. ቀጥሎ የቀረቡ የባህላዊ መሳሪያዎች ሥዕል በቡድን በመመልከት ስማቸውን ተናገሩ፡፡


ሀ


ለ


ሐ


መ


ሠ


ረ

ሰ


ሸ


## 2 መልመጃዎች

፩. ከሰንጠረዡ ባህላዊ መሳሪያዎችን ተመልክተሽ/ህ ስማቸውንና አገልግሎታቸውን በቃል ተናገር/ሪ፡፡

የቃላት እና የሀረጋት ሠንጠረዥ

| ወካይ | የባህላዊ መሳሪያዎች ስሞች | የሚሰጡት አገልግሎት |
|---|---|---|
| ሀ | ጦር | ለአደን |
| ለ | | |
| ሐ | | |

| | | |
|---|---|---|
| መ | | |
| ሠ | | |
| ረ | | |
| ሰ | | |
| ሸ | | |

፪. ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች መሰረት ሌሎች ሶስት ባህላዊ መገልገያ ቁሳቁሶችን ፃፊ/ፍ፡፡

## ክፍል ስድስት፤ ሰዋስው

### 1 አቅርቦት

- ቀጥሎ ያለውን ማስታወሻ ፃፊ/ፍ

ማስታወሻ፡- ዓረፍተ ነገር በውስጡ በሚይዘው ግስ ብዛት ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡ ነጠላ አረፍተ ነገር አንድ ማሰሪያ አንቀፅ (ግስ) ያለው ነው፡፡

ምሳሌ፡-1. አየለ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

2. ዳፉርሳ ትናንት ትምህርት ቤት አልመጣም፡፡

3. ዳራሮ ገበያ ሄደች ፡፡

4. ሹፌሩ መኪና ነዳ፡፡

### 2 መልመጃዎች

፩. የሚከተሉትን ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት አስተካክለሽ/ህ ነጠላ ዓረፍተ ነገር መስርቺ/ት፡፡

ምሳሌ፡- ኢያሱ ቀረጠ እንጨት፡፡

ኢያሱ እንጨት ቀረጠ፡፡

ሀ. ሰራች ወጋየሁ ቁርስ____________፡፡

ለ. አይሻ ሄደች በመኪና ወደ ይርጋለም____________፡፡

ሐ. ሰፋ የጨርቅ ኳስ አቡሽ____________፡፡

መ. አያንቱ ታጠበች እግሯን____________፡፡

ሠ. ፃፈች ደመቀች መፅሀፍ____________፡፡

ረ. ሰበረ ህፃኑ መነፅር____________፡፡

፪. ቀጥሎ የቀረቡ ጅምር ሃሳቦችን በማሟላት ተራ ዓረፍተ ነገር ፃፊ/ፍ፡፡

ምሳሌ፡- በቀለ ጫማውን አጠበ፡፡

ሀ. ደስታ ትምህርት ቤት ____________፡፡

ለ. ደጊቱ ገበያ ____________፡፡

ሐ. ገበሬው ምርቱን ____________፡፡

መ. ማሳንቱ ከምንጭ ውሃ ____________፡፡

ሠ. መምህሩ ረባሹን ተማሪ ____________፡፡

፫. ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት መነሻ እና መድረሻ ቅጥያዎችን አውጪ/ጣ፡፡

ምሳሌ፡- ቤቶች ቤት፣ (-ኦች)

በሬዎች በሬ፣ (-ዎች)

ሀ. ደጆች____________

ለ. ከብቶች ____________

ሐ. ፖሊሶች____________

መ. ተማሪዎች ____________

ሠ. ጫማዎች ____________

# ምዕራፍ ሦስት

## ባህል

- **የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ያዳመጥከው/ሽውን ታሪክ ትናገራለህ/ሪያለሽ፤
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በቃል ትመልሳለህ/ሻለሽ፤
- በቀረበልህ/ሽ ጭውውት መሰረት ንግግር ታቀርባለህ/ቢያለሽ፤
- የተለያዩ ባህላዊ ክንውኖችን ለጓደኞችህ/ሽ ትናገራለህ/ሪያለሽ፤
- ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክለህ/ሽ ታነባለህ/ቢያለሽ፤
- አያያዥ በመጠቀም አንቀፁን አሟልተህ/ሽ ትፅፋለህ/ፊያለሽ፤
- ጅምር ሃሳቦችን አሟልተህ/ሽ ዓረፍተ ነገር ትፅፋለህ/ፊያለሽ::

## ክፍል አንድ፤ ማዳመጥ

- የተደመጠውን ታሪክ መልሶ መናገር

አዳምጦ የመረዳት ጥያቄዎችን መመለስ

### የማነቃቂያ ተግባር

"አፌኖ" የሚለውን ምንባብ ከማዳመጥህ/ሽ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

- ስለ ባህል የምታውቀውን/ቂውን ተናገር/ሪ፡፡
- በአካባቢህ/ሽ ምን ዓይነት ባህላዊ ዳኝነት አለ?

### 2 አቅርቦት

መምህሩ የሚያነቡትን ምንባብ በጥሞና አዳምጥ/ጪ

### 2 መልመጃዎች

፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ሃሳቦች ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

ሀ. "አፊኒ" ማቅረብ በሸንጎ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

ለ . "የአፊኒ" ስርዓት የተጣሉ ሰዎች ከገደብ ሲያልፉ እንዲታረቁ ዕድል ይሰጣል፡፡

ሐ. "የአፊኒ"ን ሥርዓት ጥሶ የተገኘ ሰው በባህሉ መሰረት "በሴራ" ህግ ይቀጣል፡፡

መ. ሰዎች እውነተኛ ፍትህ እንዲያገኙ፤ "አፊኒ" ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

ሠ. "አፊኒ" የተጣሉትን ለማስታረቅ ብቻ ሳይሆን ተራን ጠብቆ መናገርንም ይመለከታል፡፡

፪. መምህሩ በድጋሚ ሲያነቡልህ/ሽ በማዳመጥ በ "ሀ"ስር ለቀረቡት ቃላት በ "ለ" ስር ካለው ፍቺያቸው ጋር አዛምድ/ጂ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አፊኒ | ሀ. የቅጣት አይነት |
| 2. ሴራ | ለ. ታላቅ ልዩ ስብሰባ |
| 3. ሶንጎ | ሐ. ሰማችሁ ወይ |
| 4. አልቀበልም | መ. መመርመር |
| 5. መፈተሽ | ሠ. እንቢተኝነት |

፫. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ከክፍል ጓደኞችህ/ሽ ጋር ተወያዩና መልስ/ሺ፡፡

ሀ. በሲዳማ ባህል አፊኒ የሚካሄደው በምን ጊዜ እንደሆነ ተወያዩ፡፡

ለ. አፊኒ ሲካሄድ የሚሳተፉት ግለሰቦች ምን ምን ርዕሰ ጉዳይ ያነሳሉ?

ሐ. አንድ ሰው "አፊኒ" ሳይል በስሜታዊነት እርምጃ ቢወስድ ምን ይሆናል?

መ. ካዳመጥሽው/ከው ታሪክ ምን አዲስ ሃሳብ አገኘሽ/ህ?

ሠ. የቀረበልሽን/ህን ባህላዊ ዳኝነት መሰረት አድርገሽ/ህ በአካባቢሽ/ህ ስለሚደረግ የእርቅ ስነ ስርአት ተወያይ/ዩ፡፡

## ተግባር ሁለት

### የማነቃቂያ ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን ከማዳመጥህ/ሽ በፊት መልስ/ሺ፡፡

- ለበዓላት የሚለበሱ ባህላዊ ልብሶችን ታውቂያለህ/ሽ?
- በአካባቢህ/ሽ በበዓላት ቀን ወጣት ሴቶችና ወንዶች ምን አይነት ልብስ እንደሚለብሱ ተናገር/ሪ፡፡

## 2 አቅርቦት

መምህሩ የሚያነቡትን ምንባብ በጥሞና አዳምጥ/ጪ፡፡

## 2 መልመጃዎች

**፩.. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆነ እውነት ፣ ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት በቃል መልስ/ሺ፡፡**

ሀ. የአሪ ብሔረሰብ የሚገኘው በሲዳማ ክልል ነው፡፡

ለ. “ጶኒ” ወይም “ጦኒ” ተብሎ የሚጠራ ባህላዊ ልብስ የሚለብሱት ወንዶች ናቸው፡፡

ሐ. ከጥጃ ቆዳ የሚዘጋጀው “ጎራ” የሚለብሱት ወጣቶች ናቸው፡፡

መ. የአሪ ብሔረሰብ ሴቶች አብዛኛውን ጊዜ የሚለብሱት ከእንሰት ቅጠል የሚሰራ ልብስ ነው፡፡

ሠ. የአሪ ብሔረሰብ ባህላዊ የሴቶች ልብስ ከቃጫና ከእንጨት ቅርፊት ተገምዶ የሚዘጋጅ ባለዘርፍ ቀሚስ ነው፡፡

ረ. በአሁን ወቅት ሁሉም የብሔረሰብ አባላት የፋብሪካና የሽመና ውጤት የሆኑ ዘመናዊ ልብስ ይለብሳሉ፡፡

**፪. መምህር የሚያነቡትን ታሪክ በጥሞና ካዳመጥህ/ሽ በኋላ መልስህ/ ሽን ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ ተናገር/ሪ፡፡**



### ክፍል ሁለት፤ መናገር

- በቀረበው ጭውውት መሰረት ንግግር ማድረግ

## 1 አቅርቦት

የቀረበልህ/ሽን ጭውውት በአትኩሮት ተመልከት/ቺ፡፡

አቡሽ ፤“ወእረም’’ የሚባለው ባህላዊ ምግብ ታውቃለህ/ሽ?

ታሪኩ፤ ኧረ አላውቅም የምን ብሔረሰብ ባህላዊ ምግብ ነው?

አቡሽ ፤ የጌዲዮ ማህበረሰብ ባህላዊ ምግብ ነው፡፡

ታሪኩ፤ የጌዲዮ ብሔረሰብ የት ነው የሚኖረው?

አቡሽ፤ በዲላ፡፡

ታሪኩ፤ ታዲያ ’’ወእረም’’ከምንድነው የሚሰራው?

አቡሽ፤ የገብስ (የከበቆሎ) ቆሎ ከኀመንና ከስጋ ጋር በመደባለቅ ይሰራል?

ታሪኩ፤ በጣም የሚጣፍጥ ይመስላል፡፡

(ምንጭ፡የብሔረሰቦች ምክር ቤት, ሀዋሳግንቦት 2001)

## 2 መልመጃዎች

፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. ከላይ የቀረበውን ጭውውት ከመምህርህ/ሽ ጋር ጥንድ ጥንድ በመሆን ድምፅህ/ሽን ከፍ በማድረግ በንግግር አቅርብ/ቢ፡፡

ለ. ባህል ለሀገራችን የሚሰጠውን ጥቅም በቡድን ተወያዩና በምሳሌ በማስደገፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ሐ. መምህርና ተማሪ በሚል ርዕስ ጭውውት አዘጋጁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

መ. በአካባቢያችሁ ስለምታውቀው/ቂው አንድ ባህላዊ ምግብ ቤተሰቦችህን/ሽን በመጠየቅ ያገኘኸውን/ሽውን ሃሳብ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ ተናገር/ሪ፡፡

፪. በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ ስለሚገኝ ባህላዊ ልብሶች ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ::

## ተግባር ሁለት

- በተሰጠ ርዕስ ጭውውት አዘጋጅቶ መናገር

### የማነቃቂያ ተግባር

- የምታውቂውን/ቀውን የሙያ ዓይነት ተናገሪ/ር፡፡

### 2 አቅርቦት

የሚከተለውን የማስታወሻ ሀሳብ ለጓደኞችሽ/ህ ተናገሪ/ር፡፡

**ማስታወሻ**

ጭውውት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚካሄድ በፈጠራ ወይም በገጠመኝ ላይ የተመሰረተ የሃሳብ ልውውጥ ነው፡፡

ሚና ነጠቃ (አንድን የሙያ ዘርፍ ባለቤቱን ተክቶ መጫወት)

ቀጥሎ የቀረበውን ጭውውት ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ ተለማመዱና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ ፡፡

ዶክተር ዳኢቴ፤ ለኮሮና ቫይረስ ፈዋሽ መድኃኒት እየፈለኩኝ ነው፡፡

ኢንጂነር ፉላሳ፤ መቼም አንቺ መድሃኒቱን ስታገኚ እኔን ታማክሪለች፡፡

ዶክተር ዳኢቴ፤ ለምን ብዬ ነው አንተን የማማክረው?

ኢንጂነር ፉላሳ፤እኔም በሙያዬ ላግዝሽ ስለምችል ነው፡፡

ዶክተር ዳኢቴ፤ አንተ ኢንጂነር ሆነህ መድኃኒት ትቀምማለህን?

ኢንጂነር ፉላሳ፤ አይ!እንደዛ ማለት አይደለም ነገር ግን በሙያዬ በምሰራበት ድርጅት የመድኃኒት ማሸጊያ ብልቃጦችን አቀርብልሻለሁ፡፡

ዶክተር ዳኢቴ፤ ትክክል ነህ ተጋግዘን ከሰራን ችግሩን እናቃልላለን፡፡

ኢንጂነር ፉላሳ፤ አዎን ትክክል ነሽ በተለያዩ ሙያዎች መሰማራት ለዚህ ለክፉ ቀን ተባብሮ ለመስራት ያግዛል፡፡

## 2 መልመጃዎች

፩. በቡድን በመሆን ስለኮሮና ቫይረስ መከላከያ መንገዶች ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሃሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርብ/ቢ ፡፡

፪. ከዚህ በታች በተሰጣችሁ የሙያ ዘርፎች መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን የተመቸህን/ሽን በመምረጥ ጭውውት አዘጋጅተህ/ሽ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ሀ. አስተማሪና ተማሪ

ለ. ሐኪምና በሽተኛ

ሐ. ሌባና ፖሊስ

መ. ርዕሰ መምህርና መምህር

ሠ. ገበሬና ነጋዴ

ረ. አሰሪና ሰራተኛ

## ክፍል ሦስት፤ ማንበብ

- የቀረበውን ምንባብ አንብቦ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን መመለስ
- የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮችን በድርጊት ቅደም ተከተል ማስተካከል

### የማነቃቂያ ተግባር

የቆጮ አዘገጃጀት የሚለውን ምንባብ ከማንበብህ/ሽ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

- ባህላዊ ምግብ ማለት ምን ማለት ነው?
- በአካባቢህ/ሽ ባህላዊ ምግብ ከምን ይዘጋጃል?

## 2 አቅርቦት

የቀረበልህን/ሽን ምንባብ በጥሞና አንብብ/ቢ፡፡

### የቆጮ አዘገጃጀት

ለምግብነት ከደረሰው እንሰት የሚዘጋጅ "waasa"የተባለውን ባህላዊ ምግብ ለማዘጋጀት ከ1 እስከ 2 ወር የሚፈጅ ሲሆን አዘገጃጀቱም እንደሚከተለው ይገለፃል፡፡ ለእንሰቱ መፋቂያና ለተፋቀው ቆጮ ማጠራቀሚያ የሚሆን ቦታ "hassa"ይዘጋጃል፡፡ "hassa" ክብ ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን ክብደት እንዲቋቋም ዙሪያው በእንጨት አጥር ይታጠራል፡፡ ውስጡም በቅጠልና ከእንሰቱ ውጫዊ ክፍል በሚቆረጠው "haticho" ተለብዶ አፈርና ቆሻሻ እንዳያስገባ ይደረጋል፡፡

እንሰቱ ተገንድሶ የቅጠሎቹ የታችኛው ንብብር ‹shafina› ንጽህናውን በጠበቀ መንገድ እየተሸለቀቀ ወደሚፋቅበት ቦታ ይጓጓዛል፡፡ shafina ተፍቆ የሚወጣው ፈሳሽ ‹wixa› የሚጠራቀምበትን አነስተኛ ጉድጓድ በአነስተኛ ከመፋቂያው ቦታ በስተግርጌ ይቆፈርና ቅጠል ተነጥፎበት ይዘጋጃል፡፡ በጉድጓድ ውስጥ የሚጠራቀመው ‹ዊጣ› ሲዘቅጥ ከላይ የሚቀረው ውሃ እየተደፋ ዝቃጩ እንዲጠራቀም በማድረግና ከእርሾ ‹gamaama› ጋር በመደባለቅ ‹bulʾa› የእንሰት ጮማ(ስብ) የተባለ ተወዳጅ የቆጮ ዓይነት ይዘጋጃል፡፡

የእንሰቱም ስር /hamicho/ በቆንጮራ ተቆርጦ በማጠራቀሚያ hassa ውስጥ በወርች አጥንት "quho" ይጨፈጨፋል፡፡ገሚሱ "hamicho" ውጫዊ ክፍሉ ሙሽራው ተጨፍጭፎ የተፋቀ ሻፊና ቅርፊት አንድ ቦታ ሲከማች በሚፈጠረው ባህሪ ባለው ቃጫ "shigido" በማሸትና በቅጠል በመጠቅለል እንዲብላላ ከጥሬ ቆጮ ጋር የሚደባለቅ ገማማ እንዲሆን ይተዋል፡፡ እስኪብላላ ድረስ ተጨማሪ እንሰት እየተቆረጠ ተፍቆ "hassa" ይከማቻል፡፡ ገማማው ሲብላላ እየተጨፈጨፈ ከተከማቸው አብቾ ጋር ይደባለቃል፡፡በቀጣይም በየጊዜው እየታሸ ከሁለት እስከ ሶስት ሳምንት ይቆያል፡፡ይህም ቆጮው ነጣ ያለ መልክና መልካም መዓዛ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ተዘጋጅቶ ለምግብነት ዝግጁ የሆነ ቆጮ "waasa"ተብሎ ይጠራል፡፡

የሲዳማ ብሔር ታሪክ

ገፅ 309

## 2 መልመጃዎች

፩. የሚከተሉትን ሃሳቦች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

ሀ. “waasa” (ዋሳ) የሚዘጋጀው ከሙዝ ተክል ነው፡፡

ለ. ከዝግጅቱ መጀመሪያ ቀን ጀምሮ ለምግብነት እስኪደርስ የሁለት ወራት ጊዜ ከፈጀ በኋላ “waasa” (ዋሳ) ይባላል፡፡

ሐ. የእንሰት ቆጮ “waasa” ከእንሰት ብቻ የሚዘጋጅ የምግብ ዓይነት ነው፡፡

መ. ለዳቦና ለእንጀራ መጋገሪያ ሊጥ እርሾ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ለ “waasa”ገማንቾ ያስፈልጋል፡፡

፪. በ”ሀ” ስር የቀረቡትን ቃላት በ”ለ“ ስር ካሉት ፍቺያቸው ጋር በምንባቡ መሰረት አዛምድ/ጂ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. መጠቅለል | ሀ.መላጥ |
| 2. መሸልቀቅ | ለ. መርጋት |
| 3. ማጠራቀም | ሐ. ጥሩ ሽታ |
| 4. መብላላት | መ. መሸፈን |
| 5. መዓዛ | ሠ. ማሰባሰብ |
| 6. መዝቀጥ | ረ.መዋሃድ |

፫. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ሃሳ “hassa” የሚዘጋጀው ለምንድን ነው?

ለ. ሻፊና ተፍቆ የሚወጣው ፈሳሽ የት ይደረጋል?

ሐ. ቡላ የተባለው ተወዳጅ ምግብ ከእንሰት እንዴት ይገኛል?

መ. ቆጮ ነጣ ያለ መልክ እና መልካም መዓዛ እንዲኖረው የሚያደረገው ምንድነው?

፬. ባነበብከው/ሽው ፅሁፍ መሰረት ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ዓረፍተ ነገሮች በድርጊት ቅደም ተከተል አስተካክለህ/ሽ አንብብላቸው/ቢላቸው፡፡

ሀ. የእንሰቱ ስር በቢላዋ ተፈቅፍቆ በማጠራቀሚያ ውስጥ በወርች አጥንት ይጨፈጨፋል፡፡

ለ. ሻፊና ተፍቆ የሚወጣው ፈሳሽ የሚጠራቀምበት አነስተኛ ጉድጓድ ይዘጋጃል፡፡

ሐ. በዚሁ ሁኔታ ተዘጋጅቶ ለምግብነት ዝግጁ የሆነ ቆጮ /wassa/ይባላል፡፡

መ. ገማማ እስኪብላላ ተጨማሪ እንሰት እየተቆረጠ /ሀሳ/ ይከማቻል፡፡

ሠ. የተሰራው ሀሳ ክብደት እንዲቋቋም ዙሪያው በእንጨት ባላ ይቸከላል፡፡

ረ. በውስጡም አፈርና ቆሻሻ እንዳያስገባ በእንሰቱ ቅጠል ውጫዊ ክፍል ይለበዳል፡፡

ሰ. ሃዕሚኖ ውጫዊ ክፍሉንና ሙሽራው ተጨፍጭፎ የተፋቀው ሻፊና ቅርፊት አንድ ጋር ይከማቻል፡፡

## ክፍል አራት፤ መፃፍ

## ተግባር አንድ

### 1 አቅርቦት

- ዓረፍተ ነገሮችን አያያዥ በመጠቀም አንቀፅን በትክክል መፃፍ

### መልመጃዎች

፩. ከዚህ በታች ያሉትን አያያዦች በመጠቀም ቀጥሎ ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች በማጣመር አንቀፅ መስርት/ቺ፡፡

| | |
|---|---|
| ስለዚህ | በተጨማሪ |
| በአጠቃላይ | ስለሆነም |

ሀ. ባህል ለአንድ ሀገር የማንነት መገለጫ ነው፡፡

ለ. የህዝቦችን የኑሮ መሰረት ለትውልድ ለማሻገር ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡

ሐ. አሁን መነሻ የሆነው ከቀደሙት አባቶች የሚወርሳቸው ልምዶች ናቸው፡፡

ሠ. የኢንዱስትሪ ውጤቶች የምንገለገልባቸው ቁሳቁሶች መነሻቸው ባህላዊ የሆነው ዕደ ጥበብ ነው፡፡

፪. በ "ሀ" ስር ያሉትን ሀረጋት በ "ለ"ስር ካሉት ተስማሚያቸው ጋር በማዛመድ ዓረፍተ ነገር ፃፍ/ፊ፡፡

| " ሀ | "" ለ" |
|---|---|
| 1. ታላላቆቻችንን ማክበር | ሀ. በሚገባ ማወቅ አለባቸው፡፡ |
| 2. አቅመ ደካማ አዛውንቶችን | ለ. ለይተን ማወቅ አለብን፡፡ |
| 3. ህፃናት ባህላቸውን | ሐ. አንዱ ባህላዊ ስርዓታችን ነው፡፡ |
| 4. ባህልና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊትን | መ. ማሳተፍ ውጤታማ ያደርጋል፡፡ |
| 5. ሴቶችን ከወንዶች እኩል | ሠ. መርዳት አለብን፡፡ |

፫. በአካባቢህ/ሽ ስለምታውቀው/ቂው ባህላዊ ጨዋታ ፃፍ/ፊ፡፡

## ተግባር ሁለት

### 1 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበውን አንቀፅ መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

**ምንባብ**

በጌዲዮ ብሔረሰብ ዘንድ የሚዘጋጅ ተወዳጅ ምግብ "ኮፌ" በመባል የሚታወቅ ሲሆን አዘገጃጀቱም በወንፊት በደንብ ተነፍቶ የተዘጋጀ ቆጮ ከገብስ ዱቄት ጋር በመደባለቅ ይነኮራል፡፡ በቅቤና በሌላ ቅባት ነክ ነገሮች እንዲለሰልስ ተደርጎ ይታሻል፡፡ አንዳንዴ ይህ ምግብ ከአደንጓሬ ጋር በመደባለቅ ተዘጋጅቶ ይቀርባል፡፡ይህ ምግብ የተለየ ክብር ለሚሰጠው እንግዳ (ትልቅ) ሰው የሚቀርብ ምግብ ነው፡፡

(ምንጭ-በብሔረሰብ ምክር ቤት በባህል ቋንቋና ታሪክ ቅርስ ጥናት ተቋም የተዘጋጀገጽ 379 ሀዋሳ)

### 2 መልመጃዎች

፩. ከአንቀፁ የወጡ ቃላትን ተጠቅመህ/ሽ ዓረፍተ ነገር ፃፍ/ፊ፡፡

ለምሳሌ ፡- <u>እንግዳ፤</u> እንግዳ የሚመጣ ቀን እናቴ ልዩ ምግብ ታዘጋጃለች፡፡

ሀ. ተወዳጅ

ለ. ማንኮር

ሐ. መለስለስ

መ. ክብር

ሠ. ማዘጋጀት

ረ. መደባለቅ

፪. ቀጥለው የቀረቡትን ጅምር ሀሳቦች በምሳሌው መሰረት አሟልተህ/ሽ ዓረፍተ ነገር ፃፍ/ፊ፡፡

ለምሳሌ፡- ጎበዝ ተማሪ የቤት ስራውን በሚገባ ይሰራል፡፡

ሀ. ወላጆች ለልጆቻቸው ______________________ ፡፡

ለ. ______________________ ህብረተሰቡን የሚጎዳ ድርጊት ነው ፡፡

ሐ. ሴት ልጅን ማስተማር ______________________ ፡፡

መ. የተለያዩ ባህሎችን ማወቅ ______________________ ፡፡

ሠ. ______________________ ባህላዊ ጭፈራ ነው ፡፡

ረ. ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት ______________________ ፡፡

፫. በቡድን በመሆን ስለምትወዱት የምግብ ዓይነት ፃፉ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመንገድ ትራፊክ ደህንነት

- ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የተለያዩ መመሪያዎችን አዳምጠሽ/ህ ትተገብሪያለሽ/ራለህ፤
- አዳምጦ የመረዳት መልመጃዎችን ትሰሪያለሽ/ራለህ፤
- ጭውውቶችን መነሻ አድርገሽ/ህ ትናገሪያለሽ/ራለህ፤
- የድርጊት ቃላትን በመጠቀም ንግግር ታደርጊያለሽ/ጋለህ፤
- የግል ንባብ ማንበብ ትለማመጃለሽ/ዳለህ፤
- ዓረፍተ ነገሮችን በማገጣጠም አንቀፅ ትመሰርቺያለሽ/ታለህ፤
- የድርጊት ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተ ነገርን ትመሰርቺያለሽ/ታለህ፡፡

## ክፍል አንድ፤ ማዳመጥ

### • አዳምጦ የመረዳት መልመጃዎችን መስራት

የተለያዩ መመሪያዎችን አዳምጦ መተግበር




## ተግባር አንድ

### 1 የማነቃቂያ ተግባር

ምንባቡ ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችው መልሱ፡፡

- የትራፊክ ፖሊሶች መንገድ ላይ የሚቆሙት ለምንድነው?
- ለእግረኞች በመኪና መንገድ ላይ መንዝ ይፈቀዳል?

ቀጥሎ የቀረበውን ስዕል በአትኩሮት ተመልከቺ/ት፡፡

- ከስዕሉ ምን ተረዳሽ/ህ?

### 2 አቅርቦት

መምህርሽ/ህ  የሚያነቡልሽን/ህን ምንባብ በጥሞና አዳምጪ/ጥ፡፡

### 3 መልመጃዎች

፩. በቀረበልሽ/ህ  ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሺ/ስ፡፡

ሀ. ከትራፊክ መብራቶች የቀይ መብራት ትርጉሙ ምንድነው?

ለ. አረንጓዴ መብራት ሲበራ መንቀሳቀስ የተፈቀደላቸው እነማን ናቸው?

ሐ. አሽከርካሪዎች ከተፈቀደላቸው ፍጥነት በላይ ቢያሽከረክሩ ምን ይፈጠራል?

መ. በመኪና መንገድ መሃል የተሰራው ዜብራ አገልግሎት ምንድነው?

፪. ቀጥለው በቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሰረት ዓረፍተ ነገር ስሪ/ሩ፡፡

ለምሳሌ፡- መመሪያ፤ የመንገድ ትራፊክ መመሪያን ማክበር በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

ሀ. ህግ

ለ. ዜብራ

ሐ. ተሽከርካሪ

መ. እግረኛ

፫. በተነበበልሽ/ህ ምንባብ ውስጥ የቀረቡት የትራፊክ መመሪያዎች ምን ምን ናቸው?

፬. የትራፊክ መመሪያን አለማክበር በሰው ልጆች ላይ ምን ጉዳት ያስከትላል?

## ተግባር ሁለት

### 1 የማነቃቂያ ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡ ከማዳመጣችሁ በፊት በቡድን ተወያይታችው መልሱ፡፡

የትራፊክ አደጋ በሰው ልጆች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ተናገሪ/ር፡፡

- ወላጆችሽ/ህ ስለመንገድ አጠቃቀም ምን ይመክሩሻል/ሃል?

### 2 አቅርቦት

መምህሩ የሚያነቡልሽን/ህን ምንባብ በጥሞና አዳምጪ/ጥ፡፡

### 3 መልመጃዎች

፩.. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጥሽው/ከው ምንባብ መሰረት የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ **እውነት** ስህተት ከሆነ **ሀሰት** በማለት በቃል መልሺ/ስ፡፡

ሀ. በሀገራችን በጣም አሳሳቢ እና አስደንጋጭ የሆነ የመኪና አደጋ እየደረሰ ነው፡፡

ለ. እግረኞች የመኪና አደጋ የሚደርስባቸው ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው ነው፡፡

ሐ. ተሽከርካሪዎች በሚበዙባቸው አካባቢዎች እግረኞች መጠንቀቅ የለባቸውም፡፡

መ.እግረኞች የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዘው መጓዝ አለባቸው፡፡

ሠ. እግረኞች በመኪና መንገድ ሲያቋርጡ መጠንቀቅ የለባቸውም፡፡

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጥሺው/ከው ምንባብ መሰረት መልሺ/ስ፡፡

ሀ. ብዙ ሰዎች የአካል ጉዳተኛ የሚሆኑት ለምንድነው?

ለ. እግረኞች የመኪና መንገድ ሲያቋርጡ ምን ማድረግ አለባቸው?

ሐ. ተሽከርካሪዎች በሚበዙባቸው ቦታዎች እግረኞች ምን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው?

መ. በትራፊክ ፖሊስ በመታገዝ መንገድ ማቋረጥ የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?

፫. በ‹‹ሀ›› ስር ያሉትን ቃላት በ ‹‹ለ›› ስር ካለው ተመሳሳይ ፍቺያቸው ጋር አዛምጂ/ድ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ስርዓት | ሀ. ብዙ |
| 2. በንቃት | ለ. በትኩረት |
| 3. ተሽከርካሪ | ሐ. ደንብ |
| 4. አያሌ | መ. መጓጓዣ |

፬. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ስጪ/ጥ፡፡

ሀ. በአካባቢያችሁ የመኪና መንገድ አለ? ካለ እናንተ በየትኛው አቅጣጫ ነው የምትጓዙት? በቡድን ተነጋገሩ፡፡

ለ. ከትምህርት ቤት ስትለቀቂ/ቅ የመኪናውን መንገድ እንዴት ትሻገሪያለሽ/ራለህ?

ሐ. ተሽከርካሪዎች የሚባሉት እነማን ናቸው?

መ. ከላይ የጠቀስሻቸው/ካቸው ተሽከርካሪዎች ምን ጉዳት ያደርሳሉ? በቡድን ተወያዩ፡፡

## ክፍል ሁለት፤ መናገር

- ጭውውትን መሰረት አድርጎ መናገር

### ተግባር አንድ

#### 1 አቅርቦት

የቀረበልሽን/ህን ጭውውት በአትኩሮት ተመልከቺ/ት፡፡

ሀብታሙ የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ ሄኖክ ደግሞ የትራፊክ ፖሊስ ሲሆን የነሀብታሙ ጎረቤት ነው፡፡ እነሀብታሙ ትምህርት ቤት አካባቢ የመንገድ ደህንነት ያስጠብቃል፡፡ አንድ ቀን ሀብታሙ ሄኖክን በሩቅ ተመለከተውና እየሮጠ ሄኖክ ጋር ደረሰ፡፡

ሄኖክ፤ ሀብታሙ ለምንድን ነው? እንደዚህ ሮጠህ መንገድ የምትሻገረው?

ሀብታሙ፤ አንተን ሳይህ ደስ ብሎኝ ነው!

ሄኖክ፤ ድንገት መኪና ቢመጣ ይገጭህ ነበር እኮ!

ሀብታሙ፤ አይደርስብኝም በፍጥነት ነው የተሻገርኩት፡፡

ሄኖክ፤ ሁለተኛ እንደዚህ እንዳታደርግ! በመጀመሪያ መንገድ ከማቋረጥህ በፊት ተሽከርካሪ አለመኖሩን አረጋግጥ፡፡

ሀብታሙ፤ ከዚያስ?

ሄኖክ፤ ቀጥሎ በዜብራ ብቻ ተሻገር!

ሀብታሙ፤ ሌላስ ምን ላድርግ?

ሄኖክ፤ ስትጓዝ ግራህን ብቻ ይዘህ ተጓዝ፡፡

ሀብታሙ፤ እሺ መመሪያዎችን እፈጽማለሁ፡፡

ሄኖክ፤ በል ቻው ሰላም ዋል፡፡

## 2 መልመጃዎች

፩. የቀረበውን ጭውውት መሰረት አድርጋችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተነጋገሩ፡፡

ሀ. ጥንድ ጥንድ በመሆን የቀረበውን ጭውውት አቅርቡ፡፡

ለ. ሀብታሙ ’’አይደርስብንም በፍጥነት ነው የተሻገርኩት’’ ሲል ሄኖክ ምን አለው?

ሐ. ሄኖክ ለሀብታሙ የነገረው ሁለት መመሪያዎች ምንድን ናቸው?

መ. እንደ ሄኖክ መኪና አይደርስብኝም ብሎ ሮጦ መሻገር ተገቢ ነው? ለምን? ለመምህራችሁ ተናገሪ/ር፡፡

፪. ሁልጊዜ ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ስትሄዱ ማድረግ ያለባችሁ ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ በጥንድ ተነጋገሩና ለመምህራችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

## ተግባር ሁለት

### 1 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበውን ጭውውት ተመልከቺ/ት፡፡

አበራ የሶስተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ ሁልጊዜ ክፍል ውስጥ ንግግር ሊያቀርብ ይፈልጋል፤ ጥሩ ንግግር ለማቅረብ ምን ማድረግ አለብኝ? መምህሬን ማናገር አለብኝ በማለት ወሰነ፡፡

**አበራ፤** መምህር አንድ ጥያቄ መጠየቅ ፈልጌ ነው?

**መምህርት፤** ጎበዝ! አበራ ምን መጠየቅ ፈለግህ?

**አበራ፤** የተሰጠንን የቤት ስራ በንግግር ለማቅረብ ምን ማድረግ አለብኝ?

**መምህርት፤** ንግግርህን ስታቀርብ ድምጽህን ከፍ አድርግ፡፡

**አበራ፤** ኦ! እኔም አንድ አውቃለሁ፡፡

**መምህርት፤** ምን?

**አበራ፤** የምናገረውን ነገር በምሳሌ አስደግፌ ማቅረብ፡፡

**መምህርት፤** ጎበዝ በተጨማሪ ንግግርህ አድማጭን በማክበር በትህትና ይሁን

**አበራ፤** ሌላስ መምህርት?

**መምህርት፤** ከአድማጮች የሚነሳውን ሃሳብ በአክብሮት መቀበል እና መልስ መስጠት፡፡

**አበራ፤** እሺ አመሰግናለሁ መምህርት፡፡

**መምህርት፤** እኔም አመሰግናለሁ ሌላ ጥያቄ ሲኖርህ ጠይቀኝ እሺ፡፡

**አበራ፤** እሺ መምህርት፡፡

## ❷ መልመጃዎች

፩. የቀረበውን ጭውውት መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሺ/ስ፡፡

ሀ. ጥንድ ጥንድ በመሆን የቀረበውን ጭውውት በንባብ አቅርቡ፡፡

ለ. አበራ መምህሩን መጠየቅ የፈለገው ለምንድን ነው?

ሐ. አበራ እኔም አንድ ነገር አውቃለሁ ያለው ምንድን ነው?

መ. ከላይ የቀረበውን ጭውውት ጥንድ ጥንድ በመሆን ተለማመዱና በንግግር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ሠ. በተለማመድሽው/ከው የንግግር መመሪያ መሰረት ስለምትወዱት የቤት እንስሳ አጭር ንግግር አቅርቢ/ብ፡፡

፪. ቀጥሎ የቀረቡ የንግግር መልመጃዎችን ተከትለሽ/ህ ተግባራዊ አድርጊ/ግ፡፡

ሀ. መኪና በማይበዛበት አካባቢ ለሰዎች የመጓጓዣ አገልግሎት የሚሰጡት ነገሮችን እየጠቀሳችሁ ስለሚሰጡት አገልግሎት በቡድን ተነጋገሩ፡፡

ለ. የመኪና አደጋ የሚፈጠረው በምን ምክንያት እንደሆነ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተነጋገሩ፡፡

ሐ. የትራፊክ አደጋ የሚቀንሰው የትራፊክ ፖሊሶች በሚያደርጉት ቁጥጥር ብቻ ነው? ጥንድ ጥንድ በመሆን በክፍል ውስጥ ተነጋገሩ፡፡

መ. ለወደፊት የትራፊክ ፖሊስ ብትሆኚ/ን ምን ማድረግ እንዳለብሽ ተናገሪ/ር፡፡

## ክፍል ሦስት፤ ማንበብ

- የግል ንባብ ማንበብ መለማመድ

### የማነቃቂያ ተግባር

ቀጥሎ ያለውን ምንባብ ከማንበብሽ/ህ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሺ/ስ፡፡

- መመሪያ የሚጥስ አሽከርካሪ ምን ያጋጥመዋል ?
- ያለበቂ ስልጠና ማሽከርከር ተገቢ ነው ትያለሽ/ትላለህ?

## ተግባር አንድ

### 2 አቅርቦት

የሚከተለውን ምንባብ መምህርሽ/ህ ካነበቡልሽ/ህ በኋላ ድምፅሽን/ህን ከፍ አድርገሽ/ህ በየተራ አንብቢ/ብ፡፡

**ባለታክሲዋ ጥንቸል**

እንስሳትን ከቦታ ወደ ቦታ የምታዘዋውር አንዲት ጥንቸል ነበረች፡፡ሁልጊዜ እንደምታደርገው በጠዋት ተነስታ የታክሲ ስራዋን ጀመረች፡፡ እንደ አጋጣሚ መንገድ ዳር ሁለት ዝሆኖች ቆመው ታክሲ ሲጠብቁ አገኘቻቸው፡፡ ዝሆኖቹም ታክሲውን እንድታቆም ኩንቢያቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው ምልክት ሰጧት፡፡ጥንቸልም ታክሲዋን አቆመችላቸው ዝሆኖቹም ወደ ጥንቸል ቀረብ ብለው ጥንቸል እባክሽ ከተራራው ጀርባ ወዳለው ጥቅጥቅ ጫካ አድርሽን ሲሉ በትህትና ጠየቋት፡፡

ዝሆኖችዬ እንደምታይዋት የእኔ ታክሲ ለትናንሽ የዱር እንስሳ የተሰራች ናት እናንተን የሚያህል ግዙፍ እንስሳ ጭና መሄድ አትችልም፡፡ ከአቅም በላይ መጫን የትራፊክ ህግ አይፈቅድም፡፡መመሪያውን እንኳን ጥሼ ብጭን ከአቅሟ በላይ ስለሆነ ታክሲዬ ተበላሽታ ትቆማለች ወይም የመገልበጥ አደጋ ያጋጥማታል፡፡ያ ደግሞ የሁላችንንም ህይወት ሊያሳጣን ይችላል እባካችሁ ሌላ አማራጭ ፈልጉ ብላ በትህትና መለሰች፡፡ ዝሆኖቹ ግን በሃሳቧ እንደማይስማሙላት ገልፀው በታክሲዋ ጭና ወደ ሚፈልጉበት ቦታ ቶሎ እንድታደርሳቸው ሊያስገድዷት ሞከሩ፡፡ ጥንቸል በድጋሚ ከአቅም በላይ መጫን ለአደጋ እንደሚያጋልጥ ደጋግማ ብትናገርም ዝሆኖቹ አስፈራርተው ከተራራው ጀርባ ወዳለው ጥቅጥቅ ጫካ እንድትወስዳቸው አስገደዷት፡፡ ዛቻና ቁጣቸውን ፈርታ ጥንቸል ታክሲዋን አስነስታ ተራራውን መውጣት ስትጀምር ታክሲዋ ሚዛኗን መጠበቅ አቅቷት ተከረባብታ ጥቅጥቅ ወዳለው ጫካ ተገለበጠች፡፡ ከብዙ ሰዓት በኋላ ጥንቸል ስትነቃ አንድ እጅዋ ተጎድቷል፡፡ ታክሲዋም ተጨረማምታ እንዳልሆነ ሆናለች ዝሆኖቹ ጋር እየተንፏቀቀች ጠጋ ስትል አንደኛው ዝሆን ሞቷል፡፡የቀረው ዝሆን ደግሞ ጭንቅላቱ ተጎድቶ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ራሱን ስቷል፡፡ ጥንቸል በጣም አዝና ተው! ይቅር አደጋ አለው ስል እንቢ ብላችሁ ነበር አይ! ዝሆን ህይወትህን አጣህ? እኔም ቤተሰቤን የማስተዳድርበትን ንብረቴንና አካሌን አጣሁ፤ ቤተሰቤን በምን ላስተዳደር ነው? በማለት እያለቀሰች ወደ ቤቷ ጉዞ ጀመረች፡፡

ምንጭ፣ ጥበቡ ፈቃዱ (አቅሎስ)፣ባለታክሲው ጥንቸል ሌሎች ተረቶች፣ 2012 ገፅ 14

## ፫ መልመጃዎች

፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጪ/ጥ፡፡

1. ጥንቸል በጠዋት ተነስታ ስራዋን ስትጀምር መንገድ ላይ ምን ገጠማት?
   ሀ. ዝሆኖች ለ. ጅቦች ሐ.ጥንቸሎች መ. ሚዳቆዎች
2. ከአቅም በላይ መጫን የትራፊክ ህጉ አይፈቅድም፤ መመሪያውን እንኳን ብጥስ ታክሲዬ __________::
   ሀ. ትበላሻለች ለ. ትገለበጣለች ሐ. ትፈጥናለች መ. ሀ ና ለ
3. ከብዙ ሰዓታ በኋላ ጥንቸል ስትነቃ ምን ጉዳት ደርሶባታል?
   ሀ. እጅዋ ተጎድቷል ሐ .ዝሆኖቹ ተጎድተዋል
   ለ. ታክሲዋ ተሰባብራለች መ.ሁሉም
4. ጥንቸል ቤተሰቤን የማስተዳድርበት ንብረት አጣሁ ስትል __________::
   ሀ. ሰርቼ ገቢ የማገኝበትን ሐ. ወጪያችንን የምሸፍንበት
   ለ. ትዕዛዝ የምሰጥበትን መ. ሀ ና ሐ

፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጪ/ጥ፡፡

ሀ. ጥንቸሏ የጣሰችው መመሪያ ምንድነው?

ለ. ዝሆኖቹ ሲያስገድዷት ጥንቸሏ ምን ማድረግ ነበረባት? በጥንድ ተወያይታችሁ ፃፉና ለመምህራችሁ አንብቡ፡፡

ሐ. የትራፊክ መመሪያውን እንድትጥስ ባያስገድዷት ኖሮ ምን ይሆኑ ነበር? ተወያዩና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

፫. በአካባቢሽ/ህ በሞተር ሳይክል ከመጠን በላይ ሰዎች ለሚጭኑ ባለሞተር ሳይክሎች ምን ሃሳብ ትሰጫለሽ/ህ ለመምህርሽ/ህ በንባብ አቅርቢ/ብ፡፡

## ተግባር ሁለት

### የማነቃቂያ ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን ከማንበብሽ/ህ በፊት መልስ/ሺ፡፡

- በአካባቢሽ/ህ የምትጠቀሚበት/ምበት ተሽከርካሪ ምን አይነት ነው?
- በጣም በፍጥነት ማሽከርከር የችሎታ መለኪያ ነው?

## 2 አቅርቦት

፩. የቀረበልሽን/ህን ምንባብ መምህር ሲያነቡልሽ/ህ በማዳመጥ ደግመሽ/ህ አንብቢ/ብ፡፡

### ከንቲባው አውራሪስ

የዱር እንስሳት ሀገር በሆነችው ዲምቱ እንስሳት በተለያየ ሙያ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡ የዱር እንስሳት ለማጓጓዝ አገልግሎት የሚጠቀሙት አህዮችን በመጫን ነው፡፡የከተማ ከንቲባ ሆኖ የተመረጠው አውራሪስ ነበር፡፡ ከተማዋ እያደገች ስትመጣ በአህያ ምትክ ጋሪዎችና ብስክሌቶች ገዝተው መጠቀም ጀመሩ፡፡ለመጀመሪያ ጊዜ ሞተር ብስክሌት ገዝታ በከተማ ውስጥ መብረር የጀመረችው ደግሞ ጥንቸል ነበረች፡፡ያንን ሞተር ብስክሌት እያስጮኸች በከተማው መሃል ወደዚህና ወደዚያ ስትበር የዱር እንስሳ በሙሉ አድናቆታቸውን ይገልፁላት ነበር፡፡የሞተር ብስክሌቱን ድምፅ በጣም እያስጓራችና ቀይ መብራት እየጣሰች መብረር አበዛች፡፡

ጥንቸል ገና ለገና እንስሳቶቹ አድናቆታቸውን ገልጸውልኛል ብላ ከልክ በላይ በመቅበጧ ሞተር ብስክሌቱን ለቃ ሁለቱንም እጆቿን በአየር ላይ ዘርግታ ስትሞላቀቅ ሞተሩ ተገለበጠና በአፍንጫዋ መሬት ላይ ወድቃ ተከሰከሰች፡፡ጥንቸል በደረሰባት አደጋ የእጆቿና የእግሮቿ አጥንቶች ተሰበሩና በፋሻ ተጠቅልለው ለብዙ ቀናት ሆስፒታል ተኛች፡፡ ድና ከወጣች ከአንድ ወር በኋላም እንደበፊቱ ፍጥነቷን ሳትቀንስ ስታበር ጨው ለመግዛት የተላከች ጦጣ መንገድ ስታቋርጥ ደረሰችባትና ገጨቻት፡፡የጦጣዋ ቤተሰቦችም በጣም ተበሳጭተው ወደ ከተማው አስተዳዳሪ አውራሪስ ቀረቡና ጥንቸል ስላደረሰችው አደጋ አስታወቁ፡፡አውራሪስ ጥንቸልን አስጠርቶ ለምን ድርጊቱን እንደፈጸመች ሲጠይቃት ጦጢትም የዱር እንስሳቱ በጋሪና በኩርኩር ሲንቱቱ ከሚውሉ ፈጣንና ዘመናዊ ትራንስፖርት እንዲጠቀሙ እያስተማርኩ ነው፡፡ ጥፋተኛዋ ጦጢት ነች፡፡ መንገዱን ስታቋርጥ ግራና ቀኝ ተመልክታ ማቋረጥ ነበረባት፡፡ እንደውም የሞተር ብስክሌቴን ፍሬቻ ሰብራለችና ዋጋዬን ልትከፍለኝ ይገባል አለች፡፡ አውራሪስ ጥቂት ሲያስብ ቆየና አንቺም ተረጋተሽ መንዳት ነበረብሽ፡፡ ጦጢትም ስትሻገሪ ግራ ቀኙን አይተሽ መሻገር አለብሽ፤ ስለዚህ ሁለታችሁም ጥፋተኛ ናችሁ በማለት ፈረደ፡፡

(በትክክል ገና፣የውሻውና የዶሮ ጥል እና ሌሎች ተረቶች፣ 2010፣ ተሻሽሎ የቀረበ ገፅ 63-64)

## 3 መልመጃዎች

፩. ምንባቡን በጥሞና ካነበብሽ/ህ በኋላ የሚከተሉት ጥያቄዎች የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት በቃል መልሺ/ስ፡፡

ሀ. ዲምቱ የዱር እንስሳት ሀገር ናት፡፡

ለ. ለዱር እንስሳቱ ከተማ ከንቲባነት የተመረጠው ዝሆን ነው፡፡

ሐ. በከተማዋ ለመጀመሪያ ጊዜ ሞተር ብስክሌት ገዝታ ማብረር የጀመረችው ጥንቸል ናት፡፡

መ. ጥንቸሏ ሞተር ብስክሌቷን እያስጮኸችና እያበረረች ስትሄድ ሌሎች እንስሳት ተረጋታ እንድትሄድ ይመክሯት ነበር፡፡

ሠ. የሞተር ብስክሌት ባለቤት ተረጋግታ ስለማትነዳ ተገልብጣ የእጅና የእግር አጥንቶቿ ተሰበሩ፡፡

ረ. ጨው ለመግዛት የተላከችው ጦጣ የተገጨችው ግራ ቀኝ ሳታይ በመሻገሯ ነው፡፡

ሰ. ጋሪና ኩርኩር እንደሞተር ሳይክል አደጋ አያደርሱም፡፡

፪. ከዚህ ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ስር ያሉ ከምንባቡ የወጡ ቃላትን በ‹‹ለ›› ስር ካሉት ፍቺያቸው ጋር አዛምጂ/ድ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መብረር | ሀ. ማስጮህ |
| 2. ማስጓራት | ለ. ጉዳት |
| 3. መክስከስ | ሐ. ትራንስፖርት |
| 4. ማቋረጥ | መ. መሻገር |
| 5. መጋጨት | ሠ. መላተም |
| | ረ. መፍጠን |
| | ሰ. መውደቅ |

፫. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ተገቢውን ምላሽ ስጪ/ጥ፡፡

ሀ. የሞተር ብስክሌት ባለቤት የተላለፈችው የትራፊክ መመሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ በቡድን በመሆን ተወያዩና ለክፍል ጓደኞቻሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

ለ. የጦጢት ቤተሰቦች ጥንቸሏን ለምን እንደከሰሷት በጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ ፃፉ፡፡

ሐ. የከተማው ከንቲባ ፍርድ ትክክል ነው ትያለሽ/ትላለህ? ለምን? መልሱን ለመምህርሽ/ህ በንባብ አቅርብ/ቢ፡፡



## ክፍል አራት፤ መፃፍ

- ዓረፍተ ነገር በመገጣጠም አንቀጽ መገንባት

### 1 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበውን አጭር ጽሁፍ ተመልከቺ/ት፡፡

እናቴ በየጠዋቱ የምታዘኝ ነገሮች የተለመዱ ናቸው፡፡ እነሱም ጊዜህን በአግባቡ መጠቀም እንድትችል በጠዋት ተነስ፤ ወደ ሽንት ቤት ሂድና ስትመለስ እጅህንና ፊትህን በሳሙናና በውሃ ታጠብ፤ቁርስህን ብላ፤ የበላህበትን ሳህን በአግባቡ አንስተህ አስቀምጥ፤ ቦርሳህ ውስጥ ሁሉም ደብተሮችህ መኖሩን አረጋግጥ፤ የግራ ጠርዝህን ይዘህ ወደ ትምህርት ቤት ሂድ የሚሉ ናቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ቁም! | አጥና! | አታድርግ! |
| እንካ! | ሥራ! | አትፍራ! |
| ሂድ! | አንብብ! | ተው! |
| አትሂድ! | አድርግ! | ተነስ! |

## መልመጃዎች

፩. ከላይ በሰንጠረዥ የቀረቡ ቃላትን ቀጥሎ ባለው ምሳሌ መሰረት በዓረፍተ ነገር እያስገባሽ/ህ ስሪ/ራ፡፡

ምሳሌ፡- መኪናው በፍጥነት እየመጣ ስለሆነ ሳታቋርጥ ዳር ላይ ቁም!

ፈተናውን ለመስራት እና መልካም እውቀት ለመቅሰም በርትተህ አጥና!

፪. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቀራረቢ ፍቺ ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- በላ---- ተመገበ

ሄደ ---- ተራመደ

ሀ. ጎበዝ

ለ. ተኛች

ሐ. ተቀበለ

መ. ተፋታ

ሠ. ገጠመ

# ምዕራፍ አምስት

## ዘመናዊ ግብርና

- ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች

- መመሪያዎችን አዳምጠህ/ሽ ትተገብራለህ/ሪያለሽ፤
- የተለያዩ ጭውውቶችን ተጠቅመህ/ሽ ሃሳብህ/ሽን በንግግር ትገልጣለህ/ጫለሽ፤
- ዓረፍተ ነገሮችን በመገጣጠም አንቀጽ ትገነባለህ/ቢያለሽ፤
- አያያዦችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን ገጣጥመህ/ሽ ታነባለህ/ሽ፤
- የዓረፍተ ነገር ክፍሎችን ታዛምዳለህ/ጃለሽ፤
- ዘመናዊ የግብርና መገልገያ መሣሪያዎችን ጽፈህ/ሽ አገልግሎታቸውን ትገልፃለህ/ጪያለሽ፤


## ክፍል አንድ፤ ማዳመጥ

- *መመሪያዎችን አዳምጦ መተግበር*

### 1 አቅርቦት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ስዕል ተመልክተህ/ሽ ምን እንደሆነ ገምት/ቺ፡፡





ቀጥሎ መምህር/ሽ ከመምህር መምሪያ ላይ “ዘመናዊ የእንስት መፋቂያ መሣሪያ” በሚለው ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ሲያነቡልህ/ሽ በጥሞና ተከታተል/ዪ፡፡

### 2 መልመጃዎች

፩. ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሠረት ቀጥሎ የቀረቡት ሃሳቦች የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ **እውነት** ስህተት ከሆነ **ሀሰት** በማለት መልስ/ ሺ፡፡

ሀ. የእንሰት መፋቂያ መሣሪያ በእንጨት ይሰራል፡፡

ለ. የብረት ማያያዣው(ክላምፕ) የእንሰት ቅርፊትን ከጣውላው ጋር ለማያያዝ የሚያገለግል ነው፡፡

ሐ. መሣሪያውን በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ማጓጓዝ አይቻልም፡፡

መ. የእንሰት መፋቂያ መሣሪያን የሚሰሩት አናፂዎች ሳይሆኑ ገንበኞች ናቸው፡፡

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያዳመጥከውን/ሽውን ጽሁፍ መሰረት አድርገህ/ሽ መልስ/ሺ፡፡

1. የእንሰት መፋቂያው የተሰራው በ ________ ልክ ሆኖ ወደ ኋላ ዘንበል ብሎ በድጋፍ እንጨት የሚቆም ነው፡፡

ሀ. በእንሰት   ለ. በሰው   ሐ. በጣውላው   መ. በእንጨት

2. የእንሰት መፋቂያ መሣሪያ ለመፋቅ ተግባር የሚውል________ ቁመት ያለው የተሰነጠቀ ቀርከሀን ይጨምራል፡፡

ሀ. አርባ ስምንት ሜትር   ለ. ሃምሳ ሣንቲም ሜትር   ሐ. ስልሣ ሣንቲም ሜትር

3. የመሣሪያው የመፋቅ አቅም በሰዓት ________ ኪ.ግ ይደርሳል፡፡

ሀ. አርባ ስምንት ኪ.ግ   ለ. ሃምሳ ስምንት ኪ.ግ

ሐ. አርባ አምስት ኪ.ግ   መ. ሰላሳ አምስት ኪ.ግ

፫. ቀጥሎ የቀረበውን መመሪያ አዳምጠህ/ሽ ተግብር/ሪ፡፡

**ማስታወሻ**

ሀ. ስታዳምጥ/ጪ ሃሳብህ/ሽን ከሚነበበው ነገር ጋር አድርግ/ጊ፡፡

ለ. እያዳመጥህ/ሽ ፍሬ ፍሬ ነገሮችን ማስታወሻ መያዝ አትርሳ/ሺ፡፡

ሐ. በማዳመጥ ጊዜ ሌላ ነገር መስራት ሃሳብ እንዲበተን ስለሚያደርግ ሌላ ነገር አታድርግ/ጊ፡፡

መ. በተቻለ መጠን የምታዳምጠውን/ጪውን ነገር ስለምን እንደሆነ እያሰላሰልክ/ሽ አድምጥ/ጪ፡፡

፬. የሚከተሉትን የእንሰት አፋፋቅ መመሪያዎች አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አንቀጽ መስርት/ቺ፡፡

| በመጨረሻ | በመቀጠል | ከዚያም |
|---|---|---|

ሀ. የተቆረጠው እንሰት ቅርፊት ተዘጋጅቶ ከመፋቂያው ጣውላ ላይ ይቀመጣል፡፡

ለ. በተሰነጠቀው ቀርከሃ በተሳለው በኩል በተደጋጋሚ ይፋቃል፡፡

ሐ. ፍቅፋቂው ከመፋቂያው ላይ ዝቅ ብሎ በተያያዘው እንጨት ላይ ይከማቻል፡፡

መ. የተከማቸው ፍቅፋቂ በተፈለገው መጠን ሲደርስ ይጨመቃል፡፡

## ክፍል ሁለት፤ መናገር

- በተለያዩ አውዶች ላይ ንግግር ማድረግ

### 1 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበውን ጭውውት አንድ ተማሪና መምህር ሲያቀርቡ በመከታተል ጥንድ ጥንድ በመሆን ተለማመዱ፡፡

መምህር አስፋውና ተማሪ ታዬ በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን አሶሳ አካባቢ ስንዴ በባህላዊ እና በዘመናዊ ዘዴ ሲመረት የሚያስገኘውን ውጤት በተመለከተ በማነፃፀር ያቀረቡትን ጭውውት ነው፡፡

መ/ር አስፋው፤ ታዬ! ዘንድሮ በማሳችሁ ስንዴው በጣም አምሮ አየሁ፡፡

ተማሪ ታዬ፤ አዎን መምህር! ከአምናው የተሻለ ምርት ይገኛል ብለን እናስባለን፡፡

መ/ር አስፋው፤ ግን ዘንድሮ የተለየ ነገር ምን አድርጋችሁ ነው እንዲህ ያፈራው?

ተማሪ ታዬ፤በፊት የሚታረሰው በበሬ ጉልበት በመሆኑና መሬቱ በጣም ሳይነሳ እንዲሁም ሳይለሰለስ ነበር የሚዘራው፡፡ ዘንድሮ ግን በማሽን ነው የታረሰው፤ በተጨማሪም ምርጥ ዘሩንና ማዳበሪያውን በወቅቱ አግኝተን ተጠቅመናል፡፡ የዝናቡ ሁኔታም ዘንድሮ በቂና ተስማሚ ነበር፡፡

መ/ር አስፋው፤ ወላጆችህ የትራክተር ማሽን ገዙ እንዴ?

ተማሪ ታዬ፤ አይ! በኮንትራት ነው ያገኙት፤ አንድ ሄክታርን አርሶ ለማለስለስ እና ለዘር ለማዘጋጀት አንድ ሺህ ብር ኪራይ ይከፈላል፡፡

መ/ር አስፋው፤ አ! በጣም ውድ ነው፤ ነገር ግን ጉልበት ቆጣቢ ዘመናዊ በመሆኑ በትራክተር ሲታረስና በበሬ ሲታረስ በጣም ሠፊ ልዩነት ነው ያለው፡፡

**ተማሪ ታዬ፤** መምህር አምና እኮ በባህላዊ መንገድ በበሬ ታርሶና ተዘርቶ ከአንድ ሄክታር ሠላሳ ኩንታል ስንዴ ብቻ ነው ያገኘነው፡፡

**መ/ር አስፋው፤** ዘንድሮሳ? ምን ያክል ከሄክታር እንደሚገኝ የባለሙያዎችን ሀሳብ ሰምተሃል?

**ተማሪ ታዬ፤** አዎን መምህር!ከአምናው በእጥፍ ማለትም ስልሳ ኩንታል በሄክታር ታገኛላችሁ ብለው ለአባቴ ሲናገሩ ሰምቻለሁ፡፡

**መ/ር አስፋው፤** በጣም ደስ ይላል፤ዘመናዊ የግብርና አስተራረስ ዘዴን መጠቀም እንደዚህ ውጤታማ ያደርጋል፡፡ በል በርታ በትርፍ ጊዜህ ወላጆችህን መርዳት አትርሳ፡፡

**ተማሪ ታዬ፤** እሺ መምህር አመሰግናለሁ!

## 2 መልመጃዎች

፩. ከላይ የቀረበውን ጭውውት መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ጥያቄዎችን መልስ በቃል ተናገር/ሪ፡፡

ሀ. መምህር አስፋው “ከአምናው የተለየ ነገር ምን አድርጋችሁ ነው ዘንድሮ የተለየ ምርት የምትጠብቁት?” ብሎ ሲጠይቀው ተማሪው ምን ብሎ መለሰለት?

ለ. መምህር አስፋው “በጣም ውድ ነው! ነገር ግን የተሻለ ምርት ያስገኛል ያሉት ለምንድን ነው?

ሐ. ተማሪው ከአምናው እጥፍ ምርት እንደምናገኝ ለአባቴ ሲናገር ሰምቻለሁ ሲል መምህሩ ምን ብሎ መለሰለት?

መ. ጭውውቱን ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ከተለማመዳችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

፪. ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎችን በቡድን በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

ሀ.ባህላዊ የግብርና አመራረት ዘዴ ውጤቱ አነስተኛ የሚሆነው ለምን ይመስልሃል/ሻል?

ለ. በዘመናዊ ና በባህላዊው አስተራረስ መካከል ያለውን ልዩነት እያነፃፀርክ/ሽ ሃሳብህን/ሽን በንግግር አቅርብ/ቢ፡፡

ሐ. በአካባቢያችሁ በዘመናዊ የግብርና መሣሪያ የሚጠቀሙ አርሶ አደሮች አሉ? ካሉ ውጤታማነታቸው ምን ያህል ነው? በጥንድ ተነጋገሩ፡፡

መ. ዘመናዊ የቡና ዝርያ አተካከል ዘዴን ተጠቅሞ ማምረት ከባህላዊ አንፃር ሲታይ የትኛው እንደሚሻል በምክንያት እያቀረባችሁ በቡድን ተነጋገሩና የጋራ ሃሳባችሁን በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሦስት፤ ማንበብ

- የግል ንባብን ተጠቅሞ ማንበብ
- አያያዦችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር በመገጣጠም አንቀፅ ማንበብ

### 1 የማነቃቂያ ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ስዕሉን በመመልከት መልስ/ሺ፡፡

- ዘመናዊ የግብርና መሣሪያዎች የሚባሉትን ዘርዝር/ሪ፡፡
- ኢንኩቤተር የሚባለው መሳሪያ አገልግሎቱ ምንድንነው?
- ቀጥሎ የቀረበው ስዕል ምን እንደሆነ ገምት/ቺ፡፡



### 2 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበውን የግል ንባብ ድምፅህ/ሽን ከፍ አድርገህ/ሽ ተራ በተራ አንብብ/ቢ፡፡

## ግብርናን ከበሬ ጫንቃ የማላቀቅ ርብርብ

መንግሥት በእርሻ ሥራ የታወቁ አካባቢዎች ከተለመደው አሠራር ወጥተው በዘመናዊ ግብርና መጠቀም እንዲጀምሩ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ጀምሯል፡፡ መንግሥት ትኩረት ከሠጠባቸው ሠላሳ ሁለት የዘመናዊ ግብርና ማሥፋፊያ አካባቢዎች ውስጥም ማኛ ነጭ ጤፍ አምራቹ ጎጃም ይገኝበታል፡፡ በዚህ አካባቢ ቀደም ሲል በባህላዊ መንገድ ሲያርሱ እና ሲያጭዱ የነበሩ አርሶ አደሮች በዘመናዊ ግብርና አስተራረስ ዘዴ መጠቀም ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡ ለአብነት ያህል በዘመናዊ የእርሻ መሣሪያ ትራክተር ተጠቅመው ከሠሩ በኋላ ምርቱን ለመሰብሰብ የሚጠቀሙበት መሣሪያ "ኮምባይነር" ነው፡፡ የኮምባይነር ማሽን የደረሰውን ጤፍ አጭዶ፣ወቅቶ፣ገለባውን ከፍሬ ለይቶ በተዘጋጀው አውድማ ላይ ፍሬውን ያከማቻል፡፡ ይህ ሂደት በአንድ ጊዜ የሚደረግ መሆኑ የአርሶ አደሮቹን ድካም ከማቃለልም አልፎ ምርቱን ጥራት ባለው መንገድ ለመሰብሰብ አግዟቸዋል፡፡

መንግሥት ከ2008 ዓ.ም እስከ 2012 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲተገበር ያወጣው ሁለተኛው የዕድገትና የለውጥ ዕቅድ በአነስተኛ አርሶ አደር ማሳዎች በተያዥ (ኩታ ገጠም) የአስተራረስ ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ በትንሽ ቦታ ሠፊ ምርት ለማሰባሰብ የምርጥ ዘርና የማዳበሪያ አቅርቦት ሳይቋረጥ እንዲዳረስ ጥረት አድርገዋል፡፡

(ምንጭ፣ኢ.ፌ.ድ.ሪ ግብርና ሚኒስትር የድህረ ምርት ቴክኖሎጂ፣ ሰኔ 1990፣ ኤክስቴንሽን ፓኬጅ)

### 3 መልመጃዎች

፩. ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎችን ባነበብከው/ሽው ምንባብ መሠረት የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

ሀ. መንግሥት አርሶ አደሮች ከባህላዊ የአስተራረስ ዘዴ ወጥተው በዘመናዊ መንገድ እንዲያርሱ ቅስቀሳ ጀምሯል፡፡

ለ. መንግሥት በዘመናዊ ዘዴ እንዲታረስ ትኩረት ከሰጠባቸው አካባቢዎች መካከል አንዱ ጎጃም ነው፡፡

ሐ. ዘመናዊ የግብርና አስተራረስ ማለት በትራክተር በማረስ በኮምባይነር ማሰባሰብ ነው፡፡

መ. የኮምባይነር ማሽን ሥራ የምርት አጨዳ ማከናወን ብቻ ነው፡፡

ሠ. ዘመናዊ የምርት አሰባሰብ ሂደት ከባህላዊ የማይሻል ነው፡፡

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልስ/ሺ/መልሰ/ሽ፡፡

ሀ. መንግሥት ከ2008 እስከ 2012 ዓ.ም ምን አቅዷል?

ለ. ከትንሽ ማሣ ብዙ ምርት ለማግኘት ምን ማድረግ ይገባል?

ሐ. ምርትን ጥራት ባለው መንገድ ለማሰባሰብ የሚያገለግለው የትኛው የግብርና ስልት ነው?

፫. የሚከተሉትን የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮች በአሠራር ቅደም ተከተል አስተካክለህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. አፈሩን አለስልሰህ ማረስ፡፡

ለ. የደረሰውን ምርት መሰብሰብ፡፡

ሐ. በቆሎውን መዝራት፡፡

መ. አረሙን በጊዜው መንቀል፡፡

ሠ. ማዳበሪያውን መጨመር፡፡

ረ. ወደ ጎተራ ምርቱን ማስገባት፡፡

፬. ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አያያዦችን ከሠንጠረዡ ላይ እየወሰድህ/ሽ በማገጣጠም አንቀጽ ፃፍ/ፊ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| በመሆኑም | በተጨማሪ | ይሁን እንጂ |
| | በሌላ በኩል | ስለዚህ |

ሀ. ሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚመረቱ ገቢ ማስገኛ ምርቶች መካከል ቡና ቀዳሚ ነው፡፡

ለ. በየዓመቱ ብዙ የውጪ ምንዛሪ የሚገኘውም ከዚሁ ምርት ውጤት ነው፡፡

ሐ. እንደምርቱ ብዛት ግን ሀገሪቷ ገቢውን አላገኘችም፡፡

መ. ዋጋው እንዲወርድ የሚያደርጉ ሰው ሰራሽ ችግሮችም በርካታ ናቸው፡፡

ረ. ወደፊት ከቡና ምርት ገቢ ለማግኘት መንግሥትና ባለድርሻ አካላት ሁሉ ጠንክረው መሥራት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

## ክፍል አራት፤ መጻፍ

- **የዓረፍተ ነገር ክፍሎችን አዛምዶ መፃፍ**

ጅምር ሀሳቦችን አስፍቶ መፃፍ

### የማነቃቂያ ተግባር

ከምትወደው/ጂው የጓሮ አትክልት አንዱን ጻፍ/ፊ፡፡

### 2 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዳጠያየቃቸው መልስ/ሺ፡፡

### 3 መልመጃዎች

፩. ቀጥሎ የቀረቡ ሃሳቦችን አስፍተህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. የኮምባይነርን አገልግሎት በተመለከተ ፃፍ/ፊ፡፡

ለ. ዘመናዊ የግብርና መሣሪያዎችን በመጥቀስ ከባህላዊ አንፃር ስለሚኖረው ጥቅም በማነፃፀር ሃሳብህን/ሽን ፃፊ/ፍ፡፡

፪. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር ስራ/ሪ፡፡

ምሳሌ፤ አስተራረስ =በዘመናዊ አስተራረስ ተጠቅመው የዘሩ አርሶ አደሮች ምርቶቻቸው በእጅጉ አድጓል፡፡

1. ግብርና
2. ዘመናዊ
3. ምርት
4. ትራክተር

**ማስታወሻ**

ዓረፍተ ነገር ሙሉ መልዕክት የሚያስተላልፉ የቃላት ስብስብ ነው፡፡ አንድ ዓረፍተ ነገር ሶስት ክፍሎች ቢኖሩትም የማይቀሩ ክፍሎቹ ባለቤት እና ማሰሪያ አንቀጽ (ግስ) ናቸው፡፡

፫. የሚከተሉትን ጅምር ሀረጎች አሟልተህ/ሽ ዓረፍተ ነገር ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. በመስኖ ልማት የተሳተፉ ወጣቶች ________________

ለ. አብዛኛው ገበሬ ________________

ሐ. ሌባውን አባርሮ የያዘው ፖሊስ ________________

መ. የአንደኛ መንፈቀ ዓመት ፈተና ________________

ሠ. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና ________________

ረ. የዘንድሮው የግብርና ምርቶች ________________

## ክፍል አምስት፤ ቃላት

- ዘመናዊ የግብርና መሳሪያዎችን አገልግሎት መጻፍ

### የማነቃቂያ ተግባር

. ለሚከተሉት ጥያቄ መልስ ስጥ/ጪ

- ከግብርና ጋር የሚዛመዱ የሙያ ቃላት ለጓደኛህ/ሽ ተናገር/ሪ

### 2 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዳጠያየቃቸው መልስ/ሺ፡፡

### 3 መልመጃዎች

፩. የሚከተሉትን የሙያ ቃላት ከሠንጠረዥ እየወሰድህ/ሽ በየዘርፋቸው መድበህ/ሽ አስቀምጥ/ጭ፡፡

- መድኃኒት ምርጥ ዘር የቡና ተክል ጋቢ
- ትራክተር ማዳበሪያ ቀሚስ
- እንቆቅልሽ አቡካዶ ፓራሲታሞል
- እንካ ሰላንትያ እንሰት

ምሳሌ፤ ከጤና ጋር ግንኙነት ያላቸው የሙያ ቃላት መድኃኒት፤ ፓራሲታሞል

ሀ. ከግብርና ጋር ግንኙነት ያለው የሙያ ቃላት ________________

ለ. የጓሮ አትክልት ፍራፍሬ ስሞች ________________

ሐ. የስነቃል ዘርፎች ______________________

መ. አልባሳት ______________________

፩. ቀጥሎ ለቀረቡት ዘመናዊ የግብርና መገልገያ መሳሪያዎች አገልግሎታቸውን ጻፍ/ፊ፡፡

ሀ. ኮምባይነር

ለ. ትራክተር

ሐ. ኢንኩቤተር

፫. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሰረት መነሻና መድረሻ ቅጥያ ቃላት አውጥተህ/ሽ ለመምህርህ/ሽ አሳይ/ዩ፡፡

ምሳሌ፤ አስገባሪ     አስ፣ መነሻ ቅጥያ ገባሪ፣ ዋና ቃል

ሀ. ወደቤት ____________ መ. በታሪክ____________

ለ. ከአካባቢ ____________ሠ. ጥያቄዎች ____________

ሐ. በሬዎች____________ረ. በምሳሌው ____________

# ምዕራፍ ስድስት

## ስርዓተ ፆታ

● የሚጠበቁ ውጤቶች

- የተለያዩ ታሪኮችን አዳምጠህ/ሽ አስተያየት ትሰጣለህ/ጪያለሽ፤
- ምንባቦችን አዳምጠህ/ሽ የቃል ጥያቄ ትመልሳለህ/ሺያለሽ፤
- ያዳመጥሽውን/ከውን ምንባብ መሰረት አድርገህ/ሽ የፅሁፍ መልመጃ ትሰራለህ/ሪያለሽ፤
- የቀረበልህ/ሽን ጭውውት መሰረት አድርገህ/ሽ ንግግር ታቀርባለህ/ቢያለሽ፤
- የቀረበልህን/ሽን ጥያቄ መሰረት አድርገህ/ሽ በንግግር መልስ ትሰጣለህ/ጪያለሽ፤
- በምንባቡ ያሉ ባለታሪኮችንና መቼታቸውን ታነባለህ/ቢያለሽ፤
- የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮችን በድርጊት ቅደምተከተል አስተካክለህ/ሽ ታነባለህ/ቢያለሽ፤
- ጅምር ሃሳቦችን ጨርሶ መፃፍን ትለማመዳለህ/ጂያለሽ፤
- ያልተሟሉ ሀሳቦችን በተገቢ ቃላት አሟልተህ/ሽ አንቀፅ ትፅፋለህ/ፊያለሽ፡፡

## ክፍል አንድ፤ ማዳመጥ

- የተለያዩ ታሪኮች አዳምጦ አስተያየት መስጠት
- ምንባቦችን አዳምጦ የቃል ጥያቄ መመለስ

### የማነቃቂያ ተግባር

መምህርህ/ሽ "ስርዓተ ፆታ" የሚለውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

- ሰዎች በፆታ ይለያያሉ ሲባል ምን ማለት ነው?
- የሴቶች ተብለው የሚታመኑባቸው ስራ በወንድ ይሰራል ብለህ/ሽ ታስባለህ/ቢያለሽ?

### 2 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበው ስዕል የሚያስተላልፈውን መልዕክት ተናገሪ/ር፡፡







**መልመጃዎች**

፩. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህርህ/ሽ ሲያነቡልህ/ሽ እያዳመጥህ/ሽ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ ምረጥ/ጪ፡፡

1. ሙሳና አስቴር የስንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው?

   ሀ. ሦስት ለ. አራት ሐ. አምስት መ. ስድስት

2. እነሙሳ የስርዓተ ፆታ ክበብ አባል ሆነው የሚያስተምሩት ስለምንድነው?

   ሀ. ስለ ትምህርት ሐ. ስለሰንደቅ ዓላማ

   ለ. ስለሴት ልጅ እኩልነት መ.የፆታ ክበብ

3. በሴትና በወንድ መካከል የሚታዩት የመራቢያ አካላት ልዩነት የሚያሳየው____ ነው፡፡
   ሀ. በፆታ ለ. በስርዓት ፆታ ሐ. በፂም ማብቀል መ. በመውለድ
4. ሴቷ ከወንዱ የምትለይበት ተፈጥሮ __________ ነው፡፡
   ሀ. በማርገዝ ለ. በመውለድ ሐ. በማጥባት መ. ሁሉም
5. አስቴር ያስተማረችው ስለምንድነው?
   ሀ. ስለፆታ ለ.ስለስርዓት ፆታ ሐ. ስለ ክበባት መ. ስለስርዓት ፆታ እና ክበባት

**፪. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት መልስ/ሺ፡፡**

ሀ. እነሙሳ ከትምህርታቸው ጎን ለጎን የሚያከናውኑት ተግባር ምንድነው?

ለ. እነአስቴር ከሰንደቅ ዓላማ ስነስርዓት በኋላ የተያዘላቸው ቀጠሮ ምንድነው?

ሐ. ስርዓተ ፆታ ማለት ምን ማለት ነው?

መ. በተለያዩ ክበባት መሳተፍ ውጤታማ የሚያደርግ ይመስልሃል/ሻል?

ሠ. በቀረበው ምንባብ የግልህ/ሽ አስተያየት ምንድን ነው?

**፫. ያልተሟሉ ዓረፍተ ነገሮችን በምንባቡ መሠረት በቅንፍ ውስጥ ከተሰጡት ቃላት የሚስማማቸውን እየመረጥህ/ሽ አስምር/ሪ፡፡**

ሀ. ሙሳ ገለፃውን እንደሚከተለው __________ /አቀረበ፣ አቀረቡ፣ አቀረብሽ/

ለ. የወንዶች የጾታ መለያ ምሳሌ __________/ፂም ማብቀል፣ ማጥባት፣ ማርገዝ/

ሐ. አሁን __________ ስለስርዓተ ፆታ ምንነት እነግራችኋለሁ/እህት፣ እኔ፣ እኛ/

መ. እግር ኳስ የወንዶች ተግባር አድርጎ መውሰድ ተገቢ __________ /ነው፣ አይደለም፣ ናቸው/

**፬. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት የግል አስተያየትህ/ሽን ለመምህርህ/ሽ ተናገሪ/ር፡፡**

ሀ. ሴቶች የወንዶች የተባሉትን ተግባራት ሁሉ ማከናወን የሚችሉ ይመስልሃል/ሻል?

ለ. በአብዛኛው ወንዶች የሴት የተባሉትን ስራ ለመስራት ፍቃደኛ የሚሆኑ ይመስልሃል/ሻል?

ሐ. በተለያዩ ክበባት መሳተፍ ተገቢ ነው ትያለህ/ሽ?



## ክፍል ሁለት፤ መናገር

- ጭውውትን መነሻ አድርጎ ንግግር ማቅረብ
- የቀረበን ጥያቄ መሰረት አድርጎ በንግግር መልስ መስጠት

## 1 አቅርቦት

**ቀጥሎ የቀረበልህ/ሽን ጭውውት በጥሞና ተመልከት/ቺ፡፡**

ከመምህርህ/ሽ ጋር በመሆን ቀጥሎ የቀረበውን ጭውውት ለጓደኞችህ/ሽ አቅርብ/ቢ፡፡

ሽታዬና ናታን የ12 ዓመት ታዳጊዎች ሲሆኑ አብሮ አደግ ናቸው፡፡ ትምህርት ቤት ሲሄዱና ሲመጡ አብረው ስለሆነ ያጋጠማቸውንና ያዩትን ሁሉ እያወሩ ነው የሚጓዙት፡፡

ሽታዬ፤ ናታን ዛሬ ሚኒሚዲያ ላይ የሰማሁት በጣም የሚገርም ነው፡፡

ናታን፤ በጣም!በተለይ ከስርዓተ ፆታ ማሳያ ምሳሌዎች አዲስ እውቀት አግኝቼበታለሁ፡፡

ሽታዬ፤ እኔማ ምግብ ማዘጋጀት የሴት ተግባር ይመስለኝ ነበር፡፡

ናታን፤ በፍፁም! ወንድ የማገዶ እንጨት መሰብሰብ እንዳለበት አውቀናል፡፡

ሽታዬ፤እረ ሴት እግር ኳስ መጫወትም ትችላለች፡፡

ናታን፤ በተጨማሪም በቢሮ ውስጥ የጽህፈት ስራ ወንዶች ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

ሽታዬ፤ የአመራርነት ስራ ለወንዶች ብለን ማመናችን ስህተት ነበር ለካ!

ናታን፤ የሚገርም ነው!

ሽታዬ፤ ምንድን ነው የሚገርመው?

ናታን፤ የወንድና የሴት የተባለ ስራ ፈፅሞ የለም፤ ሁለቱም ሁሉንም ስራ በጋራ መስራት አለባቸው፡፡

ሽታዬ፤ አዎ! ሴት ከወንድ የምትለየው በማርገዟ፤ መውለዷና በማጥባቷ ነው፡፡

ናታን፤ የተወለደውን ልጅ ግን በጋራ ማሳደግ አለባቸው፡፡

ሽታዬ፤ እውነት ነው፡፡

ምንጭ፡- የስርዓተ ጾታ ክበብ አደረጃጀት አሠራር መመሪያ፡፡ ት/ሚ ሰኔ 2011፡፡ ገጽ 5፡

## 2 መልመጃዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጭውውቱን መሰረት አድርገህ/ሽ መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ናታን ከስርዓተ ፆታ ማሳያ ምሳሌዎች ያገኘው አዲስ ነገር ምንድነው?

ለ. ሽታዬ‹‹ሴት፤ የእግር ኳስ መጫወት አለባት›› ባለችው ሃሳብ ትስማማለህ/ሚያለሽ?

ሐ. ጥንድ ጥንድ በመሆን የቀረበላችሁን ጭውውት ተለማመዱና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ በንግግር አቅርብ/ቢ፡፡

ሀ. በቤት ውስጥ የወላጆችህ/ሽ የስራ ድርሻ ምንድነው? ለክፍል ጓደኞችህ አቅርብ/ቢ፡፡

ለ. በአካባቢሽ/ህ የወንድ ስራ ተብለው የሚታሰቡ ስራዎችን የሚሰሩ ሴቶች ታውቂያለሽ/ህ? ካወቅሽ/ህ ስለሚሰሩት ስራ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ ተናገር/ሪ፡፡

ምሳሌ፤ የመኪና ሹፌር፤የባጃጅ ሹፌር፤ የመኪና ረዳት.....

ሐ. ሴቶች በውትድርና ሙያ ሲሰማሩ ውጤታማ የሚሆኑ ይመስልሃል/ሻል?

መ. ሴቶችን በማንኛውም የስራ መስክ ማብቃት የሚቻል ይመስልሃል/ሻል?

፫. ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መርጠህ/ሽ ቤተሰቦችህን/ሽን በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ በንግግር አቅርብ/ቢ፡፡

ሀ. ወንዶች ምግብ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

ለ. ሴቶች የመስሪያ ቤት ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

ሐ. ሴቶች ወታደር መሆን ይችላሉ፡፡

መ. ወንዶች የሴቶች ፀጉር ቤት መስራት ይችላሉ፡፡

## ክፍል ሦስት፤ ማንበብ


- ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቀውን ዓረፍተ ነገሮች አስተካክሎ ማንበብ

### ተግባር ሁለት

### የማነቃቂያ ተግባር

የቀረበልህን/ሽን ምንባብ ከማንበብህ/ሽ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልስ/ሺ፡፡

- የተለያዩ ሰዎች ታዋቂ የሆኑበትን ሙያ ዘርዝር/ሪ፡፡
- ስዕሉ የሚያሳየው ምንድነው?



## 2 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ተራ በተራ ድምፅህን/ሽን ከፍ አድርገህ/ሽ አንብብ/ቢ፡፡

### ደራሲዋ ጦጣ

በድሮ ጊዜ መጽሐፍ እየፃፈች የምታሳትም ደራሲ ጦጣ ነበረች፡፡ ይህች ደራሲ ጦጣ የዱር አራዊቶችን ሕይወት በአዲስ መልክ እየፃፈች ታሳትም ነበር፡፡ ብዙ የዱር አራዊቶችም ጦጢት የምታሳትመውን መፅሐፍ እያነበቡ አስተያየት እየሰጧት በአስተያየታቸው መሰረት እያስተካከለች ትፅፍ ስለነበር የደራሲዋ ጦጣ መጽሐፍ በዱር አራዊት ዘንድ እየተወደደላት ይሄድ ጀመር፡፡

ደራሲዋ ጦጢትም ከበፊቱ የሚበልጡ ድርሰቶችን ለመፃፍ ስትል የዱር እንስሳትን ህይወት ተራራ ላይ እየወጣች፣ ሸንተረሮችን ሁሉ እየተዘዋወረች የዱር እንስሳትን እየፈለገች አብራቸው እየዋለችና እያደረች እንዴት እንደሚኖሩ አጠናች፡፡ ይህን ሁሉ ከተመለከተች በኋላ ስላየችው፣ ስለሰማችውና ስለተገረመችበት የሚተርክ አንድ መጽሐፍ ፅፋ አሳተመች፡፡ አዲሱ የጦጢት መጽሐፍ ብዙዎቹ የዱር እንስሳት ገዝተው ማንበብ ጀምሩ፤በተፃፈውም ታሪክ ተገርመው እርስ በርስ ሲወያዩ የሰሙትም ሌሎችም ገዝተው ሲያነቡ የታተመው መጽሐፍአለቀ፡፡ የዱር እንስሳቱም ካንቺ መፃፍ ብዙ ትምህርት ወስደናል፤ በዚሁ ቀጥይ ስለምንኖርበት ህይወት የማናውቀውን እንድናውቅ ስላደረግሽን እናደንቅሻለን፤ እናመሰግናለን! በማለት አድናቆታቸውን ይገልፁላት ነበር፡፡ ጦጢትም በበኩሏ ከበፊቱ በበለጠ ተወዳጅ መጽሐፍ ለማሳተም ቆርጣ ተነሳች፡፡

ነገር ግን ከዱር እንስሳት አያ አንበሶ እኔ እያለሁ እንዴት! ጦጢት እንዴት! በመጽሐፎቿ ብቻ ታዋቂ ትሆናለች? እንዴትስ የእኔን ክብርና ዝና ትወስዳለች? በማለት ተንኮል በማሰብ ይከታተላት ጀመረ፡፡ ጦጢትም ቀጣይ ስራዋን ለመስራት የሚመቻትን ጭር ያለቦታ መርጣ መፃፍ ጀመረች፡፡ ሲደክማት ለማረፍ ብላ ዛፍ ላይ ወጥታ እንቅልፍ ወስዷት እያለ አያ አንበሶ የፃፈችውን በሙሉ ሰርቆ ወሰደና ይሄንን ፅፌ ታዋቂ እሆናለሁ በማለት አሰበ፡፡ ጦጢትም ስትነቃ የፃፈችውን አጣችው፤ ማነው የወሰደው? እያለች ስትፈልግ አያ አንበሶ መውሰዱን ሰማች፡፡ሄዳ መጽሐፉን እንዲሰጣት ብትጠይቀውም አላየሁም የራሴ ነው ከፈለግሽ የዱር አራዊትን ሰብስቢና ጠይቂ አላት፡፡ ጦጢትም የዱር እንስሳትን ሰበሰበች፡፡ጉማሬ፣‹‹አያ አንበሶ ምንም መጽሐፍ ፅፈህ ስለማታውቅ ይህ መጽሐፍ የጦጢት ነው›› ብሎ ፈረደላት፡፡

ምንጭ፣ጥበቡ ፍቃዱ አቅሎስ፡፡ (2011)፡፡ <u>መካኒኳ ፍየል</u>፡፡

## 3 መልመጃዎች

፩. ቀጥሎ የቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

ሀ. በድሮ ጊዜ መፅሐፍ እየፃፈች የምታሳትም ጥንቸል ነበረች፡፡

ለ. የደራሲዋ መፅሐፍ በዱር እንስሳት ዘንድ በጣም ተወዳጅ ነበር፡፡

ሐ. አዲስ የታተመው መፅሐፍ በጣም ተወዳጅ ስለነበር በፍጥነት አለቀ፡፡

መ. የደራሲዋ ጦጢት መፅሐፍን በጣም የወደደው አያ አንበሴ ነው፡፡

ሠ. ጦጢት ለመፃፍ እንዲመቻት የምትመርጠው ጭር ያለ ቦታ ነው፡፡

፪. ቀጥሎ ከቀረቡት ጥያቄዎች የጎደለውን ቃል ከምንባቡ በመፈለግ ዓረፍተ ነገሩን አሟላ/ይ፡፡

ሀ. በድሮ ጊዜ መፅሐፍ እየፃፈች ____________ ደራሲ ጦጣ ነበረች፡፡

ለ. የደራሲዋ ጦጣ መፅሐፍ ____________ ዘንድ እየተወደደላት መጣ፡፡

ሐ. የዱር እንስሳትን ህይወት ____________ እየወጣች፣ ሽንተረሮችን እየተዘዋወረች እንዴት እንደሚኖሩ አጠናች፡፡

መ. ጦጢትም በበኩሏ ከበፊቱ የበለጠ ______ መፅሐፍ ለማሳተም ቆርጣ ተነሳች፡፡

ሠ. ሲደክማት ____________ ብላ ዛፍ ላይ ወጥታ እንቅልፍ ወሰዳት፡፡

፫. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቀረበው ምንባብ መሰረት በፅሁፍ መልስ/ሺ፡፡

ሀ. በፅሁፉ ውስጥ ያለችው ዋናዋ ባለታሪክ ማነች?

ለ. ደራሲዋ መፅሀፉን ለመፃፍ ምን ምን ታደርጋለች?

ሐ. አያ አንበሴ የተናደደው ለምንድነው?

መ. ደራሲዋ ለመፃፍ የሚመቻት ምን ዓይነት ቦታ ነው?

፬. በአካባቢህ/ሽ ስለምታውቂያት/ቃት ጎበዝ ሴት በቡድን ተወያዩና የጋራ ሃሳባችሁን ለመምህራችሁ በንባብ አቅርቡ፡፡

፭. ሴቶች በሚሰማሩበት የስራ መስክ ውጤታማ የሚሆኑ ይመስላችኋል? ለምን? በጥንድ ተወያዩና ለክፍል ጓደኞቻሁ በንባብ አሰሙ፡፡

## ተግባር ሁለት

### 1 የማነቃቂያ ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን ከማንበብህ/ሽ በፊት መልስ/ሺ፡፡

- ሴቶች ልጅ ከማሳደግ ውጪ ውጤታማ የሚሆኑበት ስራ ያለ ይመስልሃል/ሻል፡፡
- ወንዶች የሴቶችን ስራ መስራት ይችላሉ?

### 2 አቅርቦት

የቀረበልህን/ሽን ምንባብ ቤትህ/ሽ አንብበህ/ሽ ጥያቄዎችን መልስ/ሺ፡፡

**ብልኋ ዳኛ**

በአንዲት መንደር ውስጥ ይኖር የነበረ ደሃ ገበሬ ቤቱ ጓሮ የሚሸጥ ነጭ ሽንኩርት ተከለ፡፡ ነጭ ሽንኩርቱን በሚገባ ከተንከባከበ በኋላ ለመነቀል ሲደርስ አንዲት የእንጨት አልጋ አስቀምጦ ሌሊቱን እዚያች አልጋ ላይ እያደረ መጠበቅ ጀመረ፡፡ ሲጠብቅም ሌባ ወደ ነጭ ሽንኩርቱ ሲገባ ባለማግኘቱ የነጭ ሽንኩርቱ ደህንነት የተጠበቀ ነው ብሎ በማሰብ የእንጨት አልጋውን ትቶ ቤቱ ገብቶ አደረ፡፡

ጠዋት ሲነሳ ነጭ ሽንኩርቱ በሙሉ ተነቅሎ ተወስዷል፡፡ ሁኔታው በጣም ስላሳሰበው ሲሮጥ ሄዶ ለመንደሩ ዳኛ ሁኔታውን ያስረዳታል፡፡ ሌባውን ለምን አልያዝከውም?‹‹ገበሬው እኔ እዚያ አልነበርኩም›› ሲል ይመልሳል ዳኛዋም ለምን ነጭ ሽንኩርትህ ሲሰረቅ ያየ ምስክር አታመጣም? ገበሬውም ክብርት ዳኛ ነጭ ሽንኩርቱ ጋ ከአልጋው በስተቀር ማንም የለም አለ፡፡ ጥሩ አልጋውን ጠዋት ፍርድ ቤት ይዘህ እንድታመጣ! አልጋው ተከሶ ምርመራ ይደረግበታል አለት፡፡

በመንደሯ ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች ይህን ታይቶ የማይታወቅ አስደናቂ የችሎት ውሎ በመስማታቸው ፍርዱን ለማየት ፍርድ ቤቱን አጨናነቁት፡፡ የእንጨት አልጋውን አምጥተው ወንጀለኞች በሚቆሙበት ስፍራ ሲያስቀምጡት ዳኛዋ ፖሊሶች እንዲደበድቡት አዘዟቸው፡፡ ፖሊሶቹም በያዙት ዱላ አልጋውን በመግረፍ ብትንትን አደረጉት፡፡ ይህንን አስደናቂ ድርጊት ሲመለከቱ የነበሩ ሰዎች ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መንገድ መሳቅ ጀመሩ፡፡ ዳኛዋ በመቆጣት ካስጠነቀቁ በኋላ የፍርድ ቤቱ በር እንዲዘጋና እዚያ የነበረ ሰው ሁሉ አንድ አንድ እፍኝ ነጭ ሽንኩርት እንዲያመጣ አዘዙ፡፡ ሁሉም ሰዎች የታዘዘውን ሲያመጡ ዳኛዋ ለየብቻ እንዲያስቀምጡ አዘዙ፡፡ ከዚያ ገበሬውን ጠርተው ያንተ ነጭ ሽንኩርት የትኛው ነው? ለይ! በማለት ካስለዩት በኋላ ያንን ነጭ ሽንኩርት ያመጣው ሰውዬ የትኛው እንደሆነ

ሲመረመር ነጭ ሽንኩርቱን የሰረቀው እርሱ እንደሆነ ታወቀ፡፡ ዳኛዋም በብልሃቷ ሌባውን ካገኙ በኋላ አርባ እንዲገረፍና ሁለት ዓመት እንዲታሰር ወሰኑ፡፡ ሂደቱን ሲከታተሉ የነበሩ ሰዎች በሙሉ የዳኛዋን ብልሃት በማድነቅ ከዚህ በፊት ከነበሩት ዳኞች ሁሉ በብልሃትና በጉብዝናቸው ይበልጣሉ አሉ፡፡

ምንጭ፡- በዮሐንስ አደም፡፡(2012)፡፡ <u>አጋዘኗ ሞኙ ገበሬ እንዲሁም ሌሎች አስተማሪ ታሪኮች</u>፡፡ ገፅ 6-11 ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡

## ፫ መልመጃዎች

፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ገበሬው ወደ ቤት ገብቶ ማደር የጀመረው ለምንድነው?

ለ. ዳኛዋ ሌባውን ለምን አልያዘከውም? ሲሉት ገበሬው ምን መልስ ሰጠ፡፡

ሐ. የአካባቢው ነዋሪዎች ፍርድ ቤቱን ያጨናነቁት ለምንድነው?

መ. ዳኛዋ ሌባውን ያገኙት እንዴት ነው?

፪. ከምንባቡ የወጡ ተዘበራርቀው የተቀመጡ ዓረፍተ ነገሮችን በድርጊት ቅደም ተከተል አስተካክለህ/ሽፃፍ/ፊ፡፡

1. ሀ. ሌባ እንዳይወስድበት አልጋ ላይ እየተኛ ይጠብቅ ነበር፡፡
   ለ. ቤቱ ጓሮ ነጭ ሽንኩርት ተከለ፡፡
   ሐ. ቤቱ ገብቶ አደረ፡፡
   መ. አንድ ደሃ ገበሬ ነበር፡፡
2. ሀ. ለመንደሯ ዳኛ ሄዶ ነገረ፡፡
   ለ. እርሻ ቦታ ምንም አልነበረም፡፡
   ሐ. ጠዋት ሲነሳ ነጭ ሽንኩርት ተነቅሏል፡፡
   መ. ሌባውን ለምን አልያዝከውም?
3. ሀ. አልጋውን ፖሊሶች ደበደቡት፡፡
   ለ. አልጋው ፍርድ ቤት መጣ፡፡
   ሐ. ፍርዱን ለማየት ፍርድ ቤቱን አጨናነቁት፡፡
   መ. አልጋው ብትንትኑ ወጣ፡፡
4. ሀ. ለየብቻው እንዲያስቀምጡ አዘዙ፡፡
   ለ. አንድ አንድ እፍኝ ነጭ ሽንኩርት አመጡ፡፡
   ሐ. የሰረቀው ሰውዬ ታሰረ፡፡
   መ. የፍርድ ቤቱ በር ተዘጋ፡፡

፫. ባነበብከው/ሽው ምንባብ ውስጥ ያሉ ባለታሪኮች እነማን ናቸው? ጥንድ ጥንድ በመሆን ተነጋገሩና ለመምህራችሁ በንባብ አሰሙ፡፡

፬. በታሪኩ ውስጥ ድርጊቱ የተከናወነው የት እንደሆነ ለመምህርህ/ሽ በንባብ አሰማ/ሚ፡፡



## ክፍል አራት፤ መፃፍ

- ጅምር ሃሳቦችን ጨርሶ መፃፍ

### 1 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበልህን/ሽን ጭውውት በጥሞና አንብበህ/ሽ ቀጥሎ ያልተሟላውን ጭውውት አሟልተህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡

ሳራና ሙላቱ የወንድማማች ልጆች ሲሆኑ ሁለቱም በተመሳሳይ እድሜ ያሉ እኩያሞች ናቸው፡፡ ሳራ የቤቱ ሁለተኛ ልጅ ስትሆን ሙላቱ ደግሞ ለእናቱና ለአባቱ የመጀመሪያ (በኩር) ልጅ ነው፡፡

ሙላቱ፤ ዛሬ በጠዋት ድክም ብሎኛል፡፡

ሳራ፤ ለምን? ምን ሰርተህ ነው የደከመህ?

ሙላቱ፤ ______________________________

ሳራ፤ እኔም ቤት አፅድቼ ነው የመጣሁት፡፡

ሙላቱ፤ ከት/ቤት ስትመለሺ ምን ትስሪያለሽ?

ሳራ፤ ______________________________

ሙላቱ፤ ታናናሾቼንማ እኔም አጫውታለሁ፡፡

ሳራ፤ ከዚያ በተጨማሪ ምን ታደርጋለህ?

ሙላቱ፤ ______________________________

ሳራ፤ ሙላቱ በል ቻው ቻው፡፡

### 2 መልመጃዎች

፩. ቀጥሎ የቀረበውን ጅምር ሃሳብ አሟልተህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. ሴቶችን በማንኛውም የስራ መስክ ማብቃት ይቻላል፡፡ ሴት ልጅ ከተማረች ዶክተር ሆና የታመመውን ህብረተሰብ በማከም ሀገሯን ማገልገል ትችላለች፡፡ እንዲሁም ዳኛ በመሆን ----------------------------

ለ. ወንዶች ሴቶች የሚሰሩትን ስራ በሚገባ ማከናወን ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ________

ሐ. በሀገራችን የፆታ እኩልነት በተወሰነ መልኩ ለውጥ አሳይቷል፤ ለዚህ ማስረጃ በተለያየ አካባቢ የሴት ሹፌሮች፣በተለያየ መስሪያ ቤት የሴት አለቃ መኖር እንዲሁም ________

፪. ቀጥሎ ያሉትን ቃላት በተገቢ ቦታቸውን በማስገባት አንቀፁን አሚላ/ዪ፡፡

ችግሮች ተደራጅተው ክህሎታቸው

እንዲጎበዙ እኩልነት

በትምህርት ቤታችን የተቋቋመው የስርዓተ ፆታ ክበብ በአንድ ትምህርት ቤት የሚማሩ ሴትና ወንድ ተማሪዎች ለአንድ ዓላማ በቡድን ____1____ የሚንቀሳቀሱበት መድረክ ነው፡፡ ይህ መድረክ የፆታ ____2____ ለማስፈንና ለማጠናከር የተቋቋመ ነው፡፡ ተግባሩም ለሴትና ለወንድ ተማሪዎች መረጃ በመስጠት ____3____ በማጎልበት የተዛባውን የስርዓተ ፆታ ተግባር ማስተካከል ሲሆን በተጨማሪም ሴት ተማሪዎች በፆታቸው የሚደርሱባቸውን ____4____ ለማስወገድ የሚደረግ ጥረት ነው፡፡ ተማሪዎች የግል ብቃትን በማሳደግ በትምህርታቸው ____5____ የወደፊት የስራ ዕድል ማስፋት ነው፡፡ ንቁ ዜጎችን ለመፍጠር የሚያስችል ስራ በትምህርት ቤት ደረጃ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ

- ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ባዳመጥከው/ሽው ታሪክ ላይ ተመርኩዘህ/ሽ አስተያየት ትሰጣለህ/ጫለሽ፤
- የተለያዩ ተረቶችን፣ ታሪኮችን ትናገራለህ/ሪያለሽ፤
- ባነበብከው/ሽው ታሪክ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህሪያትን መቼት ትናገራለህ/ሪያለሽ፤
- የዘመናዊ ሙዚቃ አጨዋወትን የሚገልጹ ጽሁፎችን አንብበህ/ሽ የቃላቱን ፍቺ ትገልፃለህ/ያለሽ፤
- አጫጭር ግለታሪኮችን ትፅፋለህ/ፊያለሽ፤
- የጽሁፍ መልመጃዎችን በመስራት የፅሁፍ ክሂልህን/ሽን ታሳድጋለህ/ጊያለሽ፤

## ክፍል አንድ፤ ማዳመጥ

- የተደመጠውን ታሪክ መሰረት አድረጎ አስተያየት መስጠት

### የማነቃቂያ ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች “ዘመናዊ ሙዚቃ” የሚለውን ምንባብ ከማዳመጥህ/ሽ በፊት በቃል መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ሙዚቃ ምንድን ነው?

ለ. ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ የሚባሉትን ተናገር/ሪ?

ሐ. ቀጥሎ የቀረበው የሙዚቃ መሳሪያ ምን ይባላል?



## 2 አቅርቦት

- መምህርህ/ሽ የሚያነቡትን ምንባብ በጥሞና አዳምጥ/ጪ፡፡

### 3 መልመጃዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት፤ ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልስ/ሽ፡፡

ሀ. የድምጽ ቀረፃ ባልነበረበት ጊዜ ሙዚቃን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ አስቸጋሪ ነው፡፡

ለ. ከሩስያ የመጡ ሙዚቀኞች በሀገራችን የሙዚቃ ትምህርት ሰጥተዋል፡፡

ሐ. የሙዚቃ ትምህርት ቤት መከፈት ለዘመናዊ ሙዚቃ አስተዋፅኦ አላደረገም፡፡

መ. የቴክኖሎጂ መስፋፋት ለሙዚቃ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ሠ. ጊታር ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

ረ. አርሞኒካ የትንፋሽ መሳሪያ ነው፡፡

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት በፅሁፍ መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ሙዚቃ የድምፅ ቀረጻ ባልነበረበት ጊዜ አስቸጋሪ የሆነው ለምንድነው?

ለ. በ19ኛ ክፍለ ዘመን በዘመናዊ ሙዚቃ ውስጥ የነበረ ክስተት ምንድን ነው?

ሐ. የሙዚቃ ትምህርት ቤቶች መብዛት ለዘመናዊ ሙዚቃ ያለው አስተዋፅኦ ምን ይመስላል?

መ. ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚባሉት እነማን ናቸው?

፫. ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት በ“ሀ” ስር ያሉትን የሙዚቃ መሳሪያ ስሞች በ በ“ለ” ስር ካሉት የሙዚቃ መሳሪያዎች ጋር አዛምድ/ጂ፡፡

| “ሀ“ | “ለ“ |
| --- | --- |
| 1. ሀርፕ | ሀ.  |
| 2. ጊታር | ለ.  |
| 3. አኮርዲዮን | ሐ.  |
| 4. ኪቦርድ | መ.  |
| 5. ሀርሞኒካ | ሠ.  |

፬. የያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ለዘመናዊ ሙዚቃ ያለው አስተዋፅዖ ምንድነው?



## ክፍል ሁለት፤ መናገር

- የተለያዩ ተረቶች (ታሪኮች) መናገር

### 1 አቅርቦት

የሚከተለውን ታሪክ በጥሞና ተመልከቱ፡፡

ስሜ ደህንነት ፈጠነ ይባላል፡፡ በዲላ ዩኒቨርስቲ የ5ኛ ዓመት የህግ ተማሪ ነኝ፡፡የተወለድኩት ምስራቅ ጎጃም ሲሆን እስከስምንት አመቴ ያደግኩት ገጠር ነበር፡፡ በቆይታዬከፍተኛ የስራ ጫና ነበረብኝ፡፡ልጅም ብሆን ውሃ እቀዳለሁ፤ ኩበት እለቅማለሁ፤ ከብት እጠብቃለሁ፡፡ በዓል ካልሆነ እንደ ልቤ የተጫወትኩበትን ጊዜ አላስታውስም፡፡ ስምንት ዓመት ሲሆነኝ ሁለቱም አይኖቼን ግላኮማ የሚባል የዓይን በሽታ ስለያዘኝ አባቴ ወደ አዲስ አበባ አመጣኝ፤ ነገር ግን ህመሙ ከጀመረኝ የቆየ ስለ ነበር መዳን አልቻልኩም፤ የቀኝ ዓይኔን ብርሃን ወዲያው አጣሁ፡፡ አባቴ በጊዜ እንዳያሳክመኝ አቅመ ደካማና የ10 ልጆች አባት ስለነበር በዚህ ምክንያት አዲስ አበባ ለአጎቴ ሰጥቶኝ ወደ ቤት ተመለሰ፡፡ አጎቴና ባለቤቱ እየረዱኝ እስከ ሶስተኛ ክፍል ከተማርኩኝ በኋላ የምስራች የሚባል እደ ጥበብ ድርጅት ከሌሎች ማየት ከተሳናቸው ጓደኞቼ ጋር ቤት ተከራየልን፡፡ እስከ 12ኛ ክፍል አንደኛ በመውጣት ተምሬ አሁን በዲላ ዩኒቨርስቲ የ5ኛ ዓመት የህግ ተማሪ ስሆን በዩንቨርሲቲው ከፍተኛ ውጤት ያለኝ ሴት ተማሪ ነኝ፡፡

ምንጭ፡- <u>የትምህርት ሴክተር ስኬታማ እንስት ተሞክሮ</u>፡፡ (ግንቦት 2005)፡፡ ገፅ 166፡፡

## መልመጃዎች

፩. ከላይ የቀረበውን ታሪክ መሰረት አድርገህ/ሽ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ከላይ በቀረበው ፅሁፍ ውስጥ ያለችውን ባለታሪክ ስምና በልጅነቷ ምን እንደምትሰራ በንግግር ግለፅ/ጪ፡፡

ለ. ባለታሪኳ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል የት ተማረች ?

ሐ. ባለታሪኳ አሁን የደረሰችበትን ደረጃ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ ተናገር/ሪ፡፡

፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጥ/ጭ፡፡

ሀ. በአካባቢህ/ሽ ስለምታውቀው/ቂው ታዋቂ ሰው ታሪክ ቤተሰቦችን በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ በንግግር አቅርብ/ቢ፡፡

ለ. አንድ የምታውቀውን/ቂውን ተረት በመምረጥ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ ተናገር/ሪ፡፡

ሐ. የምትወደውን/ጂውን የልጅነት መዝሙር ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ አሰማ/ሚ፡፡

## ክፍል ሦስት፤ ማንበብ

- በፅሑፍ ውስጥ ያሉትን ገፀባህሪያትና መቼት መግለፅ

### ተግባር አንድ

#### የማነቃቂያ ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን ከማንበብህ/ሽ በፊት በቃል መልስ/ሺ፡፡

ሀ. የልጅነት ጨዋታ የሚባሉት እነማን ናቸው?

ለ. በጣም የምትወደው/ጂው የልጆች ጨዋታ ምንድነው?



ሐ. ከላይ የቀረበው ስዕል ምን ዓይነት ጨዋታ እየተጫወቱ እንደሆነ ያሳያል?

## 2 አቅርቦት

የቀረበልህን/ሽን ምንባብ በጥሞና አንብብ/ቢ፡፡

*መሃረቤን ያያችሁ*

ልውል ተሻለ እባላለሁ፡፡የ10ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ ድሮ በልጅነቴ በጣም የምወዳቸው ጨዋታዎች አኩኩሉ፣ ወንድሜ ያዕቆብ፣ መሃረቤን ያያችሁ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ጨዋታዎች መካከል መሃረቤን ያያችሁ የሚለውን ጨዋታ በጣም ስለምወደው ሁልጊዜ የመጀመሪያዋን መሀረብ ይዤ የምጠብቃቸው እኔ ነኝ፡፡ በመጀመሪያ ከ7-10 የሚሆኑ ጓደኛማሞች እጅ ለእጅ ተያይዘን ክብ ሰርተን እንቆምና በቆምንበት ትክክል እንቀመጣለን፡፡ እጅ ለእጅ የምንያያዘው በመካከላችን ስፋት እንዲኖረን(እንዳንጋጭ) ሲባል ነው፡፡

ከዚያ መሀረብ ካለኝ መሀረቤን ይዤ መሀረብ ከሌለ ያገኘሁትን ጨርቅ በመያዝ “መሀረቤን ያያችሁ” እያልኩ እዞራለሁ፡፡ ክብ ሰርተው የተቀመጡት ልጆች እያጨበጨቡ “አላየንም እባካችሁ” በማለት ይመልሳሉ፡፡ እኔም የያዝኩትን ጨርቅ (መሃረብ) የምፈልገው ልጅ ላይ እስክጥል ድረስ እየደጋገምኩ እየዞርኩኝ “መሀረቤን ያያችሁ” እላለሁ፡፡ እነሱም “አላየንም እባካችሁ” እያሉ እያጨበጨቡ ያጅቡኛል፡፡

መሃረቤን ያያችሁ ጨዋታ የራሱ ህግ አለው፡፡ መሀረቧ የወደቀችበት (የተሸጎጠችበት) ልጅ መሀረቡን ፈቱን ሳያዞር መፈለግ ይጀምራል፡፡ መሀረቡን ካገኘ ጨዋታውን የሚመራው ልጅ በመሀረቡ ከመታው መሀል ይገባና ይቀመጣል፡፡ ተማርኳል ይባላል ፡፡ ጨዋታው እስኪያልቅ መሀል ይቀመጣል፣ ነገር ግን መሃረቡን ያስቀመጠው ልጅ ሮጦ መሀረቡ የተቀመጠበት ልጅ ቦታ ላይ ከተቀመጠበት ጨዋታው በተነሳው ልጅ ይቀጥላል፡፡

እኔም በጣም ፈጣን ያልሆነ ልጅ በመምረጥ መሀረቡን አስቀምጥና መሮጥ እጀምራለሁ፡፡

ከዚያም ልጁ ያልነቃ ከሆነ "አንድ ልጅ ሞተ" እያሉ በጭብጨባ ያጅቡኛል (ያደምቁታል)፡፡ ሳይነቃ ደርሼ ጀርባውን ከመታሁት መሀል ይገባል በድጋሚ "መሀረቤን ያያችሁ" በማለት እጀምራለሁ፤ "አላየንም እባካችሁ" እያሉ ያደምቁታል እረፍት ሰዓት እስኪያልቅ በድምቀት የምንጫወተው ጨዋታ ነበር፡፡

ምንጭ፡-ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1992)፡፡ <u>የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን</u>፡፡ ገጽ 16፡፡

## ❸ መልመጃዎች

፩. ባነበብከው/ሽው ምንባብ መሰረት የሚከተሉት ጥያቄዎች የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልስህን/ሽ በምክንያት ግለጥ/ጭ፡፡

ሀ. ልዑል አሁን የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡

ለ. ልዑል ከሚወዳቸው ጨዋታዎች አንዱ ወንድሜ ያዕቆብ ነው፡፡

ሐ. መሀረቤን ያያችሁ ጨዋታ ሁለት ሁለት ሆነው የሚጫወቱት ነው፡፡

መ. መሀረቤን ያያችሁ የራሱ ህግ አለው፡፡

ረ. የተማረከው ልጅ መሀረቡን ይዞ ያሯሯጣል፡፡

፪. የሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በፅሁፍ መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ልዑል በልጅነቱ የሚወዳቸው ጨዋታዎች የትኞቹ ናቸው?

ለ. የተለያዩ ጨዋታዎችን መጫወት ለልጆች የሚሰጠው ጥቅም ምንድነው?

ሐ. መሀረቤን ያያችሁ የሚለው ጨዋታ ህጉ ምንድንነው?

መ. መሀረቤን ያያችሁ በሚለው ጨዋታ የሚሠለፉት ምን ሲሆኑ ነው?

ሠ. ልዑል ፈጣን ያልሆነ ልጅ የሚመርጠው ለምንድነው?

፫. በምንባብ መሰረት በ"ሀ" ስር ከተዘረዘሩት ቃላት በ "ለ" ስር ካሉት በፍቺ ተስማሚያቸውን በመፈልግ አዛምድ/ጂ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ማድመቅ | ሀ. ማሰስ |
| 2. ህግ | ለ. ማሞቅ |
| 3. መፈለግ | ሐ. መጨባበጥ |
| 4. ተማርኳል | መ. ተሸንፏል |
| 5. መያያዝ | ሠ. መመሪያ |

፬. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ተገቢውን ምላሽ በፅሁፍ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. በምንባቡ ውስጥ ያለው ዋና ባለታሪክ ስሙ ማነው?

ለ. መሀረቤን ያያችሁ የሚለው ጨዋታ ስንት ልጆች ያስፈልጉታል?

ሐ. መሀረቤን ያያችሁ ጨዋታ የሚከናወንበት ቦታ የት ነው? በንባብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሙ፡፡

## ተግባር ሁለት

- ገጸ-ባህሪያትንና መቼትን መግለጽ

### 1 የማነቃቂያ ተግባር

- ወንድሜ ያዕቆብ የሚለውን መዝሙር ለጓደኞችህ/ሽ ዘምር/ሪ፡፡

## አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር ቤታችሁ አጥንታችሁ በመምጣት ከመምህራችሁ ጋር ዘምሩ፡፡

ኧረ አምሳለ

ኧረ አምሳለ

ኧረ አምሳለ

ኧረ ወይ ኧረ ወይ

ኧረ እንዴት ነሽ

ኧረ እንዴት ነሽ

አለው በመከራ

እንባዬን ሳዘራ

ለምን ታዘሪያለሽ

አገዳ እየበላሽ

አገዳም የለኝ

ምስኪን ደሃ ነኝ

ምስኪን ደሃ ሆነሽ

ምን በልተሽ ታድሪያለሽ?

ባገኝም በልቼ

ባጣም ተደፍቼ

ይክፉኝ ይድፉኝ

ጦም ማደርሽ ከፋኝ

የደጅሽ እንኮይ

አልበሰለም ወይ

ቢበስልም ባይበስልም

ትመጪ ይመስል

መምጣቱንስ መጣሁ

አንድ አጫዋች አጣሁ፡፡

ምንጭ፡- ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1992)፡፡ <u>የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን</u>፡፡

## 3 መልመጃዎች

፩. ባነበብከው/ሽው ግጥም መሰረት የሚከተሉት ጥያቄዎችየያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት፣ ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

ሀ. አምሳል በግጥሙ ውስጥ አንደኛዋ ባለታሪክ ናት፡፡

ለ. ባለታሪኳ ደስተኛ መሆኗን ለጓደኛዋ ትነግራታለች፡፡

ሐ. አምሳል የምትበላው ምግብ ብታጣ ተደፍታ ታድራለች፡፡

፪. በ"ሀ" ስር የተዘረዘሩት ከግጥሙ የወጡ ቃላት ሲሆኑ በ"ለ" ስር ካለው ተመሳሳይ ጋር ፍቺያቸው አዛምድ/ጂ፡፡

| <u>"ሀ"</u> | <u>"ለ"</u> |
|---|---|
| 1. መከራ | ሀ. ችግርተኛ |
| 2. ምስኪን | ለ. ወድቄ |

| | |
|---|---|
| 3. ተደፍቼ | ሐ. በራፍ/ውጪ |
| 4. ደጅ | መ. ችግር |
| 5. በሰለ | ሠ. ደረሰ |

፫. ኧረ አምሳለ በሚለው ሙዚቃ (ጨዋታ) ውስጥ ስንት ባለታሪኮች አሉ፡፡



## ክፍል አራት፤ መፃፍ

- ግለ ታሪክ መፃፍ

### 1 አቅርቦት

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ በግልህ/ሽ ፃፌ/ፍ፡፡

**ማስታወሻ**

**የህይወት ታሪክ አፃፃፍ**

የህይወት ታሪክ በሁለት ዓይነት መንገድ መፃፍ ይቻላል፡፡

1. የራሳችን የህይወት ታሪክ
2. የግለሰብ የህይወትታሪክ

**የግለሰብ የህይወት ታሪክ ለመፃፍ**

- የህይወት ታሪኩን የምንፅፍለት ሰው ቀደም ሲል ተፅፎውለት ከሆነ ታሪኩን ማንበብ
- ግለሰቡን ከሚያውቁ ሰዎች መረጃ መጠየቅ
- የሰበሰብነውን ታሪክ ቅደም ተከተል ማስያዝ

  ሀ. የተወለዱበትን ቦታ እና ዓመተ ምህረት

  ለ. በህይወት ከሌለ የሞተበትን ጊዜ

  ሐ. አስተዳደጉ ምን ይመስል እንደነበር

  መ. የትምህረት አቀባበሉና ደረጃው

  ሠ. ያበረከታቸው አስተዋፆኦ እና ተግባራት

## 2 መልመጃዎች

፩. ቀጥሎ ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ዓረፍተ ነገሮች በድርጊት ቅደም ተከተል አስተካክለህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. ቀና ብሎ ሲያይ የወንዙ ሙላት አልፏል፡፡

ለ. ለመሻገር ሲል ወንዙ ሞላ፡፡

ሐ. አንድ ቀን ኀብዝ ነጋዴ ማር ይዞ ወደ ገበያ ለመሄድ ተነሳ፡፡

መ. ወንዙ አስኪጎድል ዋሽንት ተጫወተ፡፡

፪. ስለ አንድ ታዋቂ ሰው ታሪክ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በመሰብሰብ ፃፍ/ፊ፡፡

- ታሪኩን የፈፀመውን ሰው
- የት እንደተወለደና አሁን ያለበት ደረጃ
- ስትፅፍ/ፊ ታሪኩ የተፈፀመበትን ቦታ መካተት አለበት፡፡

-

# ምዕራፍ ስምንት

## ገበያ እና ግብር

- ከምዕራፍ ክፍለ ትምህርት የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ያዳመጥሽው/ከው ታሪክ ላይ አስተያየት ትሰጪያለሽ/ጣለህ፤
- አዳምጠሽ/ህ የማዳመጥ መልመጃዎችን ትሰሪያለሽ/ራለህ፤
- በቀረበው ጭውውት መሰረት ንግግር ታደረጊያለሽ/ህ
- የቀረበልሽን/ህን ምንባብ በግልሽ/ህ ታነቢያለሽ/ባለህ፤
- አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ትሰሪያለሽ/ራለህ፤
- መጠይቃዊ ቃላትን ተጠቅመህ/ሽ ዓረፍተ ነገርን አሟልተህ/ሽ ታነባለህ/ቢያለሽ፡፡
- ለዘመድ (ጓደኛሽ/ህ) ደብዳቤ ትጽፊያለሽ/ፋለህ፤
- ስርዓተ ነጥብን በተገቢው ቦታ ትጠቀሚያለሽ/ማለህ፤

## ክፍል አንድ፤ ማዳመጥ

- ታሪኮችን አዳምጦ አስተያየት መስጠት

አዳምጦ የመረዳት ጥያቄዎችን መስራት

### ተግባር ሁለት

**1 የማነቃቂያ ተግባር**

ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎች መልሽ/ሺ፡፡

- ግብር የሚከፈለው ለማነው?
- ግብር ማለት ምን ማለት ነው?

## አቅርቦት

ቀጥሎ መምህርሽ/ህ“ግብር ምንድነው?” በሚል ርዕስ ሲያነቡ በፅሞና አዳምጪ/ጥ፡፡

### መልመጃዎች

፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ያዳመጥሽውን/ከውን ጽሁፍ መሰረት አድርገሽ/ህ ትክክለኛውን መልስ ምረጪ/ጥ፡፡

1. ሰዎች በማንኛውም መንገድ ከሚያገኙት ገቢ ላይ በህግ በተቀመጠው መሰረት________ ይከፈላሉ፡፡

   ሀ. ምጽዋት ለ. ብድር ሐ. ግብር መ. ጊዜ

2. ከሚከተሉት ነገሮች መካከል ከግብር ገቢ የሚሰራው________ ነው፡፡

   ሀ. ኢኮኖሚን ማልማት ሐ. ለባህል ዕድገት

   ለ. ማህበራዊ አገልግሎት ማስፋፋት መ. ሁሉም

3. ቀጥሎ ከቀረቡት አማራጮች አንዱ የግብር አስፈላጊነትን ያመለክታል፡፡

   ሀ. ለግል ጥቅም ማዋል ሐ. ለራስ ቪላ ቤት ለመገንባት

   ለ. የሌላን ሀገር ለመውረር መ. ሆስፒታሎችን ለመገንባት

፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጥሽው/ከው ምንባብ መሰረት የግል አስተያየትሽን/ህን ስጪ/ጥ፡፡

ሀ. ለመንግስት ግብር ከህብረተሰቡ የሚሰበሰበው እንዴት ነው?

ለ. ዜጎች የሚጠበቅባቸውን ግብር በታማኝነት ወቅቱን ጠብቀው ካልከፈሉ ምን ይሆናሉ?

ሐ. ግብር ሆስፒታሎችንና ትምህርት ቤቶችን ለማስፋፋት ያለው አስተዋጽኦ ምንድነው?

መ. ግብር ከመንግስት ይልቅ ለህብረተሰቡ የሚሰጠው ጠቀሜታ ምንያህል ነው?

፫. ከሚከተሉት ምንጮች መረጃዎችን አዳምጠሽ/ህ መልዕክቱን ለክፍል ጓደኞችሽ/ህ አቅርቢ/ብ፡፡

ሀ. በሬድዮ የሚተላለፉ ዜናዎች

ለ. በቴሌቪዥን የሚተላለፉ መልዕክቶች

ሐ. ከትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን እና መምህራን የሚያስተላልፏቸው ምክሮች

## ተግባር ሁለት

### የማነቃቂያ ተግባር

መምህርሽ/ህ ምንባቡን ከማስደመጣቸው በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጭ/ጥ፡፡

- ፖሊሶች ለህብረተሰቡ የሚሰጡት ጥቅም ምንድነው?
- ህብረተሰቡ ወንጀልን እንዴት መከላከል ይችላል?

### 1 መልመጃዎች

፩. ባዳመጥሽው/ከው ጽሁፍ መሰረት የሚከተሉት ጥያቄዎች የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት››፣ ስህተት ከሆነ ‹‹ሀሰት›› በማለት መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ሀኪም ቤት የተወሰደችው የላሚሶ ታላቅ ሴት ልጅ ናት፡፡

ለ. መድሀኒት ሻጪው የታሰረው አጭበርባሪ በመሆኑ ነው፡፡

ሐ. አንድ ወንጀል የሰራ ሰው ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ማስረጃ ያስፈልጋል፡፡

መ. ለታመመችው ልጅ የተገዛላት መድሀኒት ሳይሆን አመድ የሞላበት ፕላስቲክ ነው፡፡

ሠ. ትክክለኛ ነጋዴዎች በህጋዊ የንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው ብዙ ሀብት ማፍራት ይችላሉ፡፡

ረ. ላሚሶ የታሰረውን ወንጀለኛውን ለፖሊስ መጠቆም ሲችል ራሱ እርምጃ በመውሰዱ ነው፡፡

፪. ባዳመጥሽው/ከው ምንባብ መሰረት በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ከ "ለ" ረድፍ ተመሳሳይ ፍቺ  የሚሆናቸውን በመፈለግ አዛምጂ/ድ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ______1. ዳነ | ሀ. ስስታም |
| ______2. ባሰ | ለ. ጨመረ |
| ______3. ስግብግብ | ሐ. አጣራ/አወቀ |
| ______4. አረጋገጠ | መ. ጠቆመ |
| ______5. አጋለጠ | ሠ. ተፈወሰ |

፫. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት የግል አስተያየትሽን/ህን ስጪ/ጥ፡፡

ሀ. መድሐኒት ነው ብሎ መጥፎ ነገሮችን መሸጥ ተገቢ ነው ትያለሽ/ትላለህ?

ለ. ህብረተሰቡን የሚጎዳ ነገር እየሸጡ ሀብታም መሆን አስፈላጊ ነውን?

ሐ. መንግስት በአጭበርባሪ ነጋዴዎች ላይ የሚወስደው እርምጃ ተገቢ ነው ትያለሽ ትላለህ?



## ክፍል ሁለት፤ መናገር

- በቀረበው ጭውውት መሰረት ንግግር ማድረግ

### 1 አቅርቦት

የሚከተለውን ጭውውት መምህርሽ/ህ ከአንድ ተማሪ ጋር በመሆን ያቀርብልሻል/ሃል፡፡
በዚህ ምሳሌ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን ተለማምዳችሁ ለክፍሉ አቅርቡ፡፡

ዳፉርሳ እና ምንትዋብ ጓደኞች ናቸው፡፡ ዳፉርሳ ሁልጊዜ ከረሜላ ይዞ ስለምታየው ሁልጊዜ ከረሜላ ለምን እንደሚመጣ ትጠይቀዋለች ፡፡

ምንትዋብ፤ ከየት አምጥተኸው ነው ከረሜላውን የምትመጠው?

ዳፉርሳ፤ እናቴ ሰጥታኝ ነው፡፡

ምንትዋብ፤ እናትህ ለምንድነው ከረሜላ የምትሰጥህ? አግባብ እኮ አይደለም፡፡

ዳፉርሳ፤ እናቴ ሁል ጊዜ ሱቅ ስትልከኝ የምላክበትን ሳንቲም ትሰጠኛለች፡፡

ምንትዋብ፤እሱ አግባብ አይደለም፡፡ እንደሱ ከለመድክ ነገም ጉቦ ትቀበላለህ፡፡

ዳፉርሳ፤ ጉቦ ደግሞ ምንድነው?

ምንትዋብ፤ አንድ ሰው አገልግሎት ለማግኘት ለአለቃ ወይም ለበላይ አዛዥ የሚሰጠው መደለያ ገንዘብ ወይም ዕቃ ነው፡፡

ዳፉርሳ፤ ሽልማት ሊሆን አይችልም?

ምንትዋብ፤ ሽልማት የሚሆነው እንድትሰራ የሚሰጥህ ሳይሆን የሰራኸውን መልካም ነገር ወይም ከፍተኛ ውጤት አይተው ተደስተው የሚሰጥህ ሲሆን ነው፡፡

ዳፉርሳ፤ በትክክል አሁን ተገንዝቤያለሁ፡፡

## 2 መልመጃ

፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በተለማመድሽው/ከው ጭውውት መሰረት መልሶቹን ከነምክንያቱ ተናገሪ/ር፡፡

ሀ. ምንትዋብ ዳፉርሳን እናቱ ወደ ሱቅ ስትልከው የሚላክበትን ሳንቲም እንዳይጠይቅ የመከረችው ለምንድነው?

ለ. ዳፉርሳ ምንትዋብን “ጉቦ ሽልማት ሊሆን አይችልም?” የተባለው ምክንያት ምንድነው?

ሐ. ከዳፉርሳ እና ከምንትዋብ ንግግር ትክክለኛውን ሀሳብ ያስተላለፈው ማነው? ለምን?

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ ስሩ፡፡

ሀ. ግብር በወቅቱ ለማይከፍሉ ሰዎች ምን ትመክራለህ/ሪያለሽ?

ለ. ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚገዙ ነገሮች ላይ ጭማሪ ለሚያደርጉ ነጋዴዎች ያላችሁን ሀሳብ ተናገሩ፡፡

ሐ. እናንተ የገበያ ተቆጣጣሪዎች ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ? በቡድን ሆናችሁ ተነጋገሩ፡፡

መ. ግብርን በአግባቡ ቢከፍሉ ለትምህርት ቤት እና ለተማሪዎች የሚኖረው አስተዋፅኦ ምንድነው? ሃሳባችሁን በንግግር አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሶስት፤ ማንበብ

- የቀረበውን ምንባብ በግል ማንበብ
- አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን መስራት
- መጠይቃዊ ቃላትን ተጠቅሞ ዓረፍተ ነገርን አሟልቶ ማንበብ

## አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በየግልሽ/ህበራስሽ/ህ ፍጥነት አንብቢ/ብ፡፡

### የቡና ግብይት

በቡና ዝግጅትም ሆነ በግብይት ወቅት ተዋናይ በመሆን ምርቱ በገበያ ላይ የተሻለ ዋጋ እንዲያወጣ የሚሰሩ በርካታ የህብረት ስራ ማህበራት ይገኛሉ፡፡ ለዚህም የግብርና ግብዓ ቶችን በማቅረብ ምርት እና ምርታማነትን በማሳደግ እንዲሁም የገበያን ዋጋ ለማረጋጋት አምራቹ የምርቱ ተጠቃሚ እንዲሆን እየሰሩ ይገኛል፡፡ አርሶ አደሩ የገበያ አማራጭ እንዲያገኝና በአለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆን ከማድረጋቸውም በተጨማሪ ገዢዎች በቀጥታ ከአርሶ አደሩ ማህበራት እንዲገዙ ምቹ ሁኔታ ፈጥረዋል፡፡

ከዚህም አንፃር ለገበያ የሚቀርበው ምርት ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል አባላቱ የተፈጥሮ ቡና እንዲያመርቱና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል፡፡

በመንግስት የልማት አቅጣጫዎች በግልፅ እንደተቀመጠው ገጠሩን ማዕከል ያደረገው ልማት ግቡን የሚመታው አርሶ አደሩ በቂ ምርት በማምረት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ ሲችል ነው፡፡ አርሶ አደሩ ቡናን በጥራት እና በበቂ መጠን አምርቶ ለገበያ ማቅረብ የሚችለው ደግሞ ላመረተው ምርት ተገቢውን ዋጋ ሲያገኝ ነው፡፡ ሆኖም ቀደም ሲል የተማከለ የግብይት ስርዓት ባለመኖሩ አምራቹ ከምርቱ ማግኘት የሚገባውን ሳያገኝ ቆይቷል፡፡ ይህ ችግር ይፈታ ዘንድ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ተቋቁሟል፡፡ በዚህ መሰረት መንግስት በሰጠው ትኩረት የግብይት ስርዓቱን ዘመናዊ፣ቀልጣፋ፣ ፍትሀዊና ግልፅ በማድረግ ስራው እየተካሄደ ይገኛል፡፡

## ተማሪዎች ልማት ግቡን የሚመታው ምን ሲሆን ነው ?

መንግስት ለህብረት ስራ ማህበራት ደንብና መመሪያ ከማዘጋጀት ጀምሮ ስልጠናና ትምህርት በመስጠት እንዲሁም የብድር አቅርቦት ድጋፍ በመስጠት ልማቱን በማገዝ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት በቡና ግብይት የተሳተፉ ማህበራት፣ የቦርድ አመራር አባላት፣በዩኒየን ደረጃ ባሉ እና በመሰረታዊ ማህበር ደረጃ ለሚገኙ የህብረት ስራ አመራር፣ በግብይት በንብረት አያያዝና አስተዳደር እንዲሁም በአደረጃጀት ዙሪያ ስልጠና በመስጠት የአቅም ግንባታ ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም ማህበራት ጥራት ያለው የቡና ምርት ለገበያ በማቅረብ የተሻለ ገቢ ለአባሎቻቸው እንዲያስገኙ ገበያ የማፈላለግ፣ የመደገፍ እና ክትትል የማድረግ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የገጠር ፋይናንስ ፈንድ አገልግሎት ጽ/ቤት የማህበራቱን ፈንድ አገልግሎት ጽ/ቤት የማኅበራቱን የፋይናንስ አቅም ከመደገፍና ክፍተቱን ከመሙላት አንፃር እየሰራ ያለ ተቋም ነው፡፡ከዚህ ሌላም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መነጋገር ማህበራቱ በወቅቱ ስራቸውን እንዲጀምሩ ለማድረግ ክልሎች የፋይናንስ ተቋማት ብድር እንዲያገኙ የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል፡፡ በአጠቃላይ ለቡና ንግዱ የሚውል ከባንክና ከተለያዩ ምንጮች ብድር እየተመቻቸ ይገኛል፡፡

የህብረት ስራ ማህበራቱን ለማጠናከር ሌላው እየተሰራ ያለው ንቅናቄ የመፍጠር ስራ ነው፡፡ በክልሉ ያሉ ማህበራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉ የመጡ ቢሆንም በህብረተሰቡ እና በየደረጃው በሚገኙ አካላት የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የህብረት ስራን ጥቅምና አጠቃላይ በኢኮኖሚው ላይ የሚኖራቸውን ድርሻ ከመረዳት አንፃር የሚኖረውን ክፍተት ለመሙላት የህብረት ስራ ማህበር ንቅናቄ ሰነድ ተዘጋጅቶ በየደረጃው ከሚገኙና ከሚመለከታቸው ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ጋር ውይይት አካሄደዋል፡፡

ምንጭ፡- ማህደረ ደቡብ ከጥቅምት - ታህሳስ 2002 ዓ.ም

## ❷ መልመጃዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን በየግል በድጋሚ በማንበብ የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልሺ/ስ፡፡

ሀ. የቡና ምርት ገበያ የተሻለ ዋጋ እንዲያመጣ የሚሰሩ የህብረት ስራ ማህበራት አሉ፡፡

ለ. መንግስታዊ ያልሆኑ የህብረት ስራ ማህበራት የቡና ምርት ግዢዎች በቀጥታ ከአርሶ አደር ማህበራት እንዲገዙ አድርገዋል፡፡

ሐ. የተፈጥሮ ቡናን የተፈጥሮ ማዳበሪያ እየመገቡ ማምረት በአለም ገበያ የተሻለ ዋጋ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

መ. የመንግስት የቡና እቅድ ግቡን የሚመታው አርሶ አደሮች ጥራት ያለውን በቂ ምርት ለሀገር ውስጥ እና ለውጪ ገበያ ማቅረብ ሲችሉ ነው፡፡

፪. በምንባቡ መሰረት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጪ/ጥ፡፡

1. የቡና ገበያ የሚኖረው ____________ ነው፡፡
   ሀ. ሀገር ውስጥ ሐ. ቡና አምራች አርሶ አደሮች አካባቢ
   ለ. ከሀገር ውጪ መ. ሁሉም
2. የገበያ ዋጋን በማረጋጋት አምራቹ የምርቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚሰሩ ________ ናቸው፡፡
   ሀ. መንግስት መ. “ሀ” እና “ለ” ብቻ
   ለ. የህብረት ስራ ማህበራት
   ሐ. የግል ኩባንያ
3. በአሁኑ ጊዜ ህጋዊ የቡና ነጋዴዎች የሚባሉት ____________ ናቸው፡፡
   ሀ. ፍቃድ ያላቸው ባለሀብቶች ሐ. ዩኒየኖች
   ለ. የህብረት ስራ ማህበራት መ. ሁሉም

፫. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሺ/ስ፡፡

ሀ. “የቡና ግብይት” በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የመጀመሪያውን አንቀፅ በቡድን አንብባችሁ በአንቀፁ የቀረበውን ሀሳብ አሳጥራችሁ ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

ለ. የሶስተኛው አንቀፅ የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድነው? ጥንድ ጥንድ በመሆን የተወያያችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ አንብቡ፡፡

፬. የሚከተሉትን መጠይቃዊ ቃላት ተጠቅመህ/ሽ ዓረፍተ ነገሮችን አሟልተሽ/ህ ፃፍ/ፊ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| እንዴት | ለምን | ማን | በምን |
| ምን | ወይ | መቼ | ከየት |

ሀ. ግብር የሚከፍለው ____________ ነው?

ለ. ከገበያ__________ ይገዛል?

ሐ. ሰዎች ምርቶቻቸውን የሚሸጡት __________ ነው?

መ. ግብር __________ ይጠቅማል?

ሠ. መንግስት የህብረተሰቡን ፍላጎት __________ ያሟላል?

ረ. ቡና ወደ ገበያ የሚወስደው __________ ነው?

ሰ. ግብር የሚሰበሰበው __________ ነው?



## ክፍል አራት፤ መፃፍ

- ለወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ መፃፍ

### የማነቃቂያ ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን አጭር ግጥም በየግልሽ/ህ አንብበሽ/ህ የሚያስተላልፈውን መልዕክት በሁለት ዓረፍተ ነገሮች ፃፊ/ፍ፡፡

ገንዘብ

የሰው ልጅ ለራሱ መጠቀሚያ ሰርቶ፤

ሲገበያይበት ገንዘብን አምርቶ፤

ሲገለገልበት ሲጠቀም ቆይቶ፡፡

## 2 አቅርቦት

### ተግባር ሁለት

ቀጥሎ ያለውን ማስታወሻ ጻፍ/ፊ፡፡

ማስታወሻ፡- ደብዳቤ

ደብዳቤን በምንፅፍበት ወቅት ማወቅ የሚያስፈልጉን ነጥቦች

ለወዳጅ የሚጻፍ ደብዳቤ ከሆነ፡-

- ደብዳቤውን የፃፍንበት ቀን፤
- የላኪውና የተቀባዩን አድራሻ በትክክል መስፈሩን፤
- የቋንቋ ስህተት አለመኖሩንና ስርዝ ድልዝ የሌለው መሆኑን መፈተሽ፤

የወዳጅ ደብዳቤ ቅርፅ

ቀን ____________

የላኪው ስም ____________

አድራሻ ____________

የተቀባይ ስም ____________

አድራሻ ____________

________________________________________

____________ ዝርዝር ሃሳብ(ሀተታ) ____________

________________________________________

____________ ፡፡

የመዝጊያ ፊርማ እና ስም

ምንጭ ፡- በመምህር ጉጉ.መቻ. የካቲት 10 2010 ዓ.ም

ዋልታ አማርኛ አጋዥ፡፡ ነጭ ሳር ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

መልመጃ

፩. ከላይ የቀረቡትን የደብዳቤ አፃፃፍ ቅርጾች ተከትለሽ/ህ ለምትወጂው/ደው ዘመድሽ/ህ ደብዳቤ ፃፊ/ፍ፡፡

ተግባር ሁለት

- ስርዓተ ነጥብ

ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ በደብተርሽ/ህ ላይ ጻፊ/ፍ፡፡

**ማስታወሻ፤ ሥርዓተ ነጥቦች**

ስርዓተ ነጥቦች ቃልን ከቃል፣ ሀረግን ከሀረግ፣ ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር ያለያሉ፡፡

ዓረፍተ ነገሩ ሊፈጥር የሚገባውን ስሜት ይጠቁማሉ፡፡ ለዓረፍተ ነገሮች መሳካት በቃላት አመራረጥና አገባብ የምጠነቀቀውን ያህል ለሥርዓተ ነጥቦች ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ብዙ የሥርዓተ ነጥብ አይነቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ለዚህ ክፍል ደረጃ እንዲማሩት ይመጥናል ተብሎ የታሰቡት የሚከተሉት ናቸው፡፡

ድርብ ሰረዝ(፤)

ራሳቸውን የቻሉ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን የሃሳብ ቁርኝት ለማያያዝ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፤ተመልካቾቹ በሰአቱ ትያትር ቤቱን ሞልተውታል፤ ተዋንያኑ ግን እስካሁን አልገቡም፡፡

•ቃል አጋኖ(!)

የቃል አጋኖ ምልክት መገረምን፣ መደሰትን፣ መቆጣትን፣ የመሳሰሉትን ቃላት፣ ሀረጎችን እና ዓረፍተ ነገሮችን ለመግለፅ ይጠቅማል፡፡

ምሳሌ፤ወይ ጉድ! ጆሮ የማይሰማው የለም! እያለች ስትናገር ሰማኋት፡፡

•ጥያቄ ምልክት (?)

ጥያቄ ምልክት መጠይቃዊ ሃሳቦችን ወይም ዓረፍተ ነገሮችን ያመለክታል፡፡

ምሳሌ፤ ወዴት ሄደች?

: የዘንድሮ ኮከብ ተሸላሚ ማን ነው?

ነጠብጣብ (...)

ከአንድ ንግግር ወይም ፅሁፍ ሀሳብ ወስደን በምንጠቀምበት ወቅት የቀረ ሀሳብ መኖሩን የምናሳይበት ነው፡፡

ምሳሌ፤ "...ጠንክራችሁ ከተማራችሁ ጥሩ ቦታ ትደርሳላችሁ...":

፪. ቀጥሎ በ"ሀ" ስር ለቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ ከ"ለ" ስር ወስደሽ/ህ አዛምጂ/ድ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. በለጠች ወደ ገበያ ሄደች _____ | ሀ. (፡፡) |
| 2. __ ቢሆንም ጠንክራችሁ ከሠራችሁ ጥሩ ውጤት ታስመዘግባላችሁ፡፡ | ለ. (፤) |
| | ሐ. (!) |
| 3.. መሠለ በፍጥነት ሄደ _____ ነገር ግን ጓደኛውን ሳያገኝ ተመለሰ፡፡ | መ. (?) |
| | ሠ. (...) |
| 4.. መጽሀፉን ቶሎ አምጣ_____ | |
| 5.. ትላንትና ምን ሆነህ ነበር የቀረኸው _____ | |

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## አካባቢያችን

- ## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ

- ያዳመጥከውን/ሽውን ታሪክ መሰረት አድርገህ/ሽ አዳምጦ የመረዳት ጥያቄዎችን ትሰራለህ/ሪያለሽ፡፡
- የሳምንቱን ቀናት ትናገራለህ/ሪያለሽ፡፡
- የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክለህ/ሽ ታነባለህ/ቢያለሽ፡፡
- አያያዥ በመጠቀም አንቀፅ ትጽፋለህ/ፊያለሽ፡፡
- ተራኪ አንቀጽ ትጽፋለህ/ፊያለሽ፡፡

## ክፍል አንድ፤ ማዳመጥ

- **አዳምጦ የመረዳት ጥያቄዎችን መስራት**


### የማነቃቂያ ተግባር

መምህሩ የሚያነቡትን ምንባብ ከማዳመጥህ/ሽ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልስ/ሽ፡፡

ሀ. የምታውቀውን/ቂውን ብሄራዊ ፓርክ ተናገር/ሪ፡፡

ለ. በአካባቢህ/ሽ ምን አይነት የዱር እንስሳቶች አሉ?

ሐ. በስዕሉ ውስጥ ያሉት የዱር እንስሳት እነማን ናቸው?



## አቅርቦት

ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ሎካ አባያ የሚባለው ብሄራዊ ፓርክ የሚገኘው በደቡብ ክልል ነው፡፡

ለ. የፓርኩ አጠቃላይ ስፋት አምስት መቶ ስኩዌር ነው፡፡

ሐ. የሎካ አባያ አካባቢ የአየር ንብረት ደጋማ ነው፡፡

መ. በሀገራችን ከሚገኙ ብርቅዬ አዕዋፍ መካከል ሀያ ሶስቱ አባያ ፓርክ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ሠ. አንበሳ በሎካ አባያ ብሄራዊ ፓርክ ይገኛል፡፡

## መልመጃዎች

፩. ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት በ "ሀ" ስር የተዘረዘሩት ቃላትን በ"ለ" ስር ካሉት ፍቺያቸው ጋር አዛምድ/ጂ፡፡

| | "ሀ" | "ለ" |
|---|---|---|
| _____ | 1. በረሃ | ሀ. የደምቀ |
| _____ | 2. ጥበቃ | ለ. ምኞት |
| _____ | 3. የጎላ | ሐ. የተከለከለ ጥብቅ ቦታ |
| _____ | 4. ፍላጎት | መ. ሞቃት |
| _____ | 5. ፓርክ | ሠ. ክልከላ |

፪. መምህርህ/ሽ በድጋሚ ሲያነቡ እያዳመጥህ/ሽ በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ሎካ አባያ ፓርክ የሚገኘው የት ነው?

ለ. ሎካ አባያ ፓርክ አጠገብ ያሉት ወንዞች እነማን ናቸው?

ሐ. ፓርኩ ጥቅም እንዲሰጥና በረሃማነቱን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት?

መ. በሎካ አባያ ፓርክ ውስጥ የሚገኙ ብርቅዬ አዕዋፍን ዘርዝሩ፡፡

ሠ. በፓርክ ውስጥ የሚገኙት አጥቢ እንስሳት እነማን ናቸው?

## ክፍል ሁለት፤ መናገር

- የሳምንቱን ቀናት መናገር

### አቅርቦት

**ከዚህ ቀጥሎ የቀረበልህን/ሽን ጭውውት ከመምህርህ/ሽ ጋር በመሆን በንግግር አቅርብ/ቢ፡፡**

ኤልሳ እና ደበላ የጎረቤት ልጆች ሲሆኑ የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ሁለቱም የሚሰጣቸውን ስራ በመተባበር ሰርተው ወደ ጨዋታቸው ይሄዳሉ፡፡

ኤልሳ፤ ዛሬ እኮ ቅዳሜ ነው ቦርሳችንን አናጥብም?

ደበላ፤ እሺ እናጥባለን ግን ትንሽ እንቆይ፡፡

ኤልሳ፤ ለምን እንቆያለን በዛውም የደንብ ልብሳችንን እናጥባለን፡፡

ደበላ፤ ልክ ነሽ! እንዲደርቅልን በጊዜ እንጠብ፡፡

ኤልሳ፤ ካልደከመን ደግሞ የቤት ስራችንንም እንሰራለን፡፡

ደበላ፤አዎ! ዛሬ ስራችንን ከጨረስን ነገ የእረፍት ቀን ይሆንልናል፡፡

ኤልሳ፤ እኔ ግን እሁድ ፀጉሬን እሰራለሁ፡፡

ደበላ፤ አሀ! ለካ ሰኞ ትምህርት ቤት እንሄዳለን፤

ኤልሳ፤ አዎ! ማክሰኞም የወንድሜ ልደት ነው

ደበላ፤ ረቡዕ ፤ ሐሙስና ዓርብም ትምህርት ስላለን መስራትሽ ጥሩ ነው

ኤልሳ፤ ልክ ነህ!

### መልመጃዎች

፩. ከላይ የቀረበውን ጭውውት ጥንድ ጥንድ በመሆን በንግግር አቅርብ/ቢ፡፡

፪. ጭውውቱን መሰረት አድርገህ/ሽ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በንግግር መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ደበላ “እሺ እናጥባለን ትንሽ እንቆይ” ያለው ኤልሳ ምን ስትለው ነው?

ለ. ኤልሳ ካልደከመን ምን እናደርጋለን አለች?

ሐ. እሁድ ኤልሳ ምን የምታደርግበት ቀን ነው?

፫. ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተነጋገሩ፡፡

ሀ. በአንድ ሳምንት ውስጥ የሚገኙትን ቀናት ዘረዝሩ፡፡

ለ. በአካባቢህ/ሽ የስራ ቀናት የሚባሉት ስንት ናቸው? ስማቸውን ለጓደኞችህ/ሽ ህተናገር/ሪ፡፡

ሐ. ከሳምንቱ ቀናት ውስጥ ስንት የእረፍት ቀናት አሉ?

መ. አካባቢያችንን ለማስዋብ በእረፍት ጊዜያችን ምን መስራት አለብን?

፬. የሚከተሉትን ተግባራት መነሻ አድርገህ/ሽ በሳምንቱ ቀናት ውስጥ የምታከናውናቸውን/ ኚያቸውን ተግባራት ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ ተናገር/ሪ፡፡

- ግቢ እጠርጋለሁ
- ውሃ እቀዳለሁ
- ፊልም አያለሁ
- የደንብ ልብሴን አጥባለሁ

## ክፍል ሶስት፤ ማንበብ

- የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክሎ ማንበብ

### ተግባር አንድ

የማነቃቂያ ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች “አባይ” የሚለውን ግጥም ከማንበብህ/ሽ በፊት በቃል መልስ/ሺ፡፡

- በሀገራችን ያሉ ትላልቅ ወንዞች እነማን ናቸው?
- አሁን እየተገነባ ያለው የሀይል ማመንጫ የትኛው ወንዝ ላይ ነው?

### 2 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበውን ግጥም ከመ ምህርህ/ሽ በመቀጠል ተራ በተራ ድምጽህን/ሽን ከፍ አድርገህ/ሽህ አንብብ/ቢ፡፡

## <u>አባይ</u>

አባይ አባይ እያልን ስንት አመት ወቀስንህ፤
እንደ ወንጀለኛ ቅኔ ቋጠርንብህ፤
አንዳንዴ .................... ዘራፍ
ሲመረን ...................... ገፉፊ፤
ሲያምረን ያገር ሲሳይ፤
ስንቆጭ ...........ኮብላይ፤
የውጭ ናፋቂ አገርህን የማታይ፡፡
ማደሪያ የሌለህ ከዱር የምታድር፤
በማለት ስንወቅስህ ቅኔ ስንደረድር፡፡

እኛ ........... ስንሰራልህ፤
ቤት አልባ ............. ስንልህ፤
ሁሉን .............. ተቀብለህ፤
እልፍ ዘመን ............ አልፈህ፤
ይኸው ዛሬ ደግሞ ለምስጋና በቃህ፤
እንዲያው ሲወርድብህ የስድብ መአቱ፤
የኛ ነው ያንተ ነው የማን ነው ጥፋቱ?
አንደበት ቢኖርህ አንተ ብትናገር፤
ላለፉት ዘመናት ስንቱን ባልከን ነበር፡፡
አንተም አትውቀሰን እኛም ተባብረናል፡፡
መጋቢት ሃያ አራት ሁለት ሺ ስድስት፤
ላንተ ቃል ገብተናል፡፡
እንግዲህ ጉልበትህ ኮረንቲ ይረጫል፤

ኢትዮጵያን ሊያለማ ሀይል ያመነጫል፡፡

የምትጠራርገው ለም አፈር ደለሉ፣

ማዕድኑ ውሃው ግሳንግሱ ሁሉ፣

ለሰብል ማምረቻ ለእርሻ ይውላሉ፡፡

ምንጭ ፡- ይርጋ ወሰን የማሪያም ወርቅ፡፡(2011)፡፡ ተናጋሪው

## መልመጃዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ግጥሙን መሰረት አድርገህ/ሽ የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

ሀ. አባይ እንደ ወንጀለኛ ብዙ ዓመት ሲወቀስ ኖሯል፡፡

ለ. አባይ ኮብላይ የተባለው የሀገራችንን ሀብት ይዞ ስለሚሄድ ነው፡፡

ሐ. ማደሪያ የሌለው የተባለው የተከዜ ወንዝ ነው፡፡

መ. አንደበት ቢኖረው አባይ እኛንም ይወቅሰን ነበር፡፡

ሠ. ከአባይ ጋር ለመተባበር ቃል የገባነው ሰኔ 24 ነው፡፡

፪. ለሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሰረት ትክክለኛ ሀሳብ የያዘውን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡

1. አባይ ለብዙ ዘመን ________ ኖሯል፡፡

   ሀ. ሲወቀስ ለ. ሲወደስ ሐ. ሲገነባ መ. ሲመሰገን

2. አባይ ሁልጊዜ ይዞ የሚዞረው ምንድነው?

   ሀ. ግንድ ለ. ቤት ሐ. ሰብል መ. ድንጋይ

3. በግጥሙ “ማደሪያ የሌለው” የተባለው ለምንድነው?

   ሀ. አንድ ቦታ ስለማይረጋ ሐ. ቤት ስለሌለው
   ለ. ሁል ጊዜ ተጓዥ ስለሆነ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

4. በግጥሙ “አንተም አትውቀሰን እኛም ተባብረናል” ያሉት ምን ለማለት ነው?

   ሀ. ግድብ እየሰራን ነው ሐ. ስድብ በዝቶበታል
   ለ. በአንተ መጠቀም ልንጀምር ነው መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

5. አባይ የተወቀሰው ምን አድርጎ ነው?

ሀ. ሀገሩን አስርቦ

ለ. ለም አፈር ጠርጎ ወስዶ

ሐ. ለመብራት ሀይል ሆኖ

መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

፫. ከዚህ በታች የቀረበው ግጥም በማንበብ ተዘበራርቀው የተቀመጡትን አስተካክለህ/ሽ ለክፍል ጓደኞችህ/ አንብብ/ቢ ፡፡

እንዲያው ሲወርድብህ የስድብ መአቱ

ይኸው ዛሬ ደግሞ ለምስጋና በቃህ

የኛ ነው ያንተ ነው የማንነው ጥፋቱ?

ላለፉት ዘመናት ስንቱን ባልከን ነበር፡፡

አንደበት ቢኖርህ አንተ ብትናገር

## ተግባር ሁለት

### የማነቃቂያ ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች “የአርቤጎና ወረዳ መስህቦች” የሚለውን ምንባብ ከማንበብህ/ሽ በፊት በቃል መልስ/ሺ፡፡

- የምታውቀው/ቂው ፏፏቴ የት ይገኛል?
- በአካባቢህ/ሽ የምታውቀው/ቂው ተራራ አለ? ካለ ተናገር/ሪ፡፡

## 2 አቅርቦት

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ቤትህ/ አንብበህ/ሽ የመረዳት ጥያቄዎችን ስራ/ሪ፡፡

### የአርቤጎና ወረዳ መስህቦች

በአርቤጎና ወረዳ ከሚገኙ መስህቦች አንዱ በሲዳማ ባህላዊ ቤቶችና የተለያዩ ዝርያ ያላቸው የሀገር በቀል እና የውጭ ዝርያ ችግኞች የተተከሉበት ከመሆኑም ባሻገር በውስጡ የተለያዩ የሲዳማን ብሄር ማንነት የሚያሳዩ ባህላዊ ዕቃዎች ማለትም ጦር፣ ጋሻ፣ሻቆ፣ሻፌታ፣ጎንፋ፣ቱባና እንዲሁም የተለያዩ ቁሳቁሶች ይገኙበታል፡፡ ለዚህ መንደር ለየት ያለው ውበትና ድምቀት ከሰጡት ነገሮች ውስጥ አንዱ ከጎኑ የሚገኘው የጎረንቲ ወንዝ ፏፏቴ ተጠቃሽ ነው፡፡ በመሆኑም ቦታው ለጉብኝት፣ ለሰርግና ለተለያዩ ዝግጅቶች እጅግ ተመራጭ ሲሆን ይህ መንደር በወረዳው ባህልና ቱሪዝም የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ስር የሚተዳደር ነው፡፡

ሌላኛው መስህብ የሀፉርሳ ተራራና ደን ሲሆን ይህ ተራራ ከወረዳው ዋና ከተማ ከሆነችው ያዬ ከተማ በስተሰሜን አቅጣጫ የሚገኝ ነው፡፡ ተራራው በአረንጓዴ ቀለም ያሸበረቀና ሙሉ በሙሉ በደን የተሸፈነ ሲሆን በውስጡም የተለያዩ የዱር እንስሳትና አዕዋፍን የያዘ ነው፡፡ በተጨማሪም ለአካባቢው ውበት መጠበቅ ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ ከመሆኑም ባሻገር ለቱሪዝም ልማት ቢውል ለአካባቢው ህብረተሰብ ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይሰጣል፡፡

በተጨማሪ መስህብነቱ የሚነሳው ጎረንቲ ፏፏቴ ወንዝ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከያዬ ከተማ በስተምስራቅ አቅጣጫ በግማሽ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ከፏፏቴው አጠገብ በጎን በኩል የሚገኘው ዋሻ ለአካባቢው ትልቅ ውበት ሰጥቶታል በመሆኑም ወደዚህ ስፍራ ለጉብኝት የሚመጡ ጎብኚዎች በአንድ ጊዜ ሁለት መስህብ ማለትም ፏፏቴና የተፈጥሮ ዋሻ ከመመልከታቸው ባሻገር የተለያዩ ቀለማት ያላቸው አዕዋፍ ዝርያዎች መመልከት ይችላሉ፡፡ በወረዳው ውስጥ ተጠቃሽ የሆኑ በርካታ የቱሪስት መስህብ ስፍራዎች ይገኛሉ፡፡ከነዚህም ውስጥ ምሳሌ የሚሆነው የተፈጥሮ ድልድይ፣ የቦሮዶ ሀይቅ፣ የጎሌደን፣ የወርባ ዱሌ ደን እና የመሳሰሉት የሚገኙ ሲሆን እነዚህ እምቅ የሆኑ ቱሪዝም ሀብቶቻችንን ሙሉ ለሙሉ ጥቅም ላይ ቢውል ለበርካታ ወገኖቻችን የስራ እድል ከመፍጠሩም ባሻገር ለሀገራችን የቱሪዝም ዕድገት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

ምንጭ፡- የጎረንቴ ፏፏቴ ዋሻ፡፡ (ነሐሴ 29/2003)፡፡ገረንባ፡፡

## መልመጃዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባብ መሰረት በማድረግ የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ፡፡

ሀ. የጎረንቲ ወንዝና ፏፏቴ የሚገኘው በአርቤጎና ወረዳ ነው፡፡

ለ. የአፋርሳ ተራራ በአረንጓዴ ቀለም ያሸበረቀና ሙሉ በሙሉ በደን የተሸፈነ ነው፡፡

ሐ. የአፋርሳ ተራራ ከያዬ ከተማ በስተምስራቅ አቅጣጫ ይገኛል፡፡

መ. ከጎረንቲ ፏፏቴ አጠገብ ትልቅ ዋሻ አለ፡፡

ሠ. የቦሮዶ ሀይቅ የሚገኘው በበንሳ ወረዳ ነው፡፡

፪. በ"ሀ" ስር ለተዘረዘሩት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት በ"ለ" ስር ከሚገኙት በፍቺ ተስማሚውን በመፈለግ አዛምድ/ጂ

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| _______ 1. ደመቀ | ሀ. ተጋረደ |
| _______ 2. ተመራጭ | ለ. አስተዋፅኦ |
| _______ 3. ተሸፈነ | ሐ. ተመልካች |
| _______ 4. ጎብኚ | መ. አማረ |
| _______ 5. ሚና | ሠ. ተፈላጊ |

፫. የሚከተሉትን ቃላት በምንባቡ መሰረት በመጠቀም የተጓደለውን አንቀፅ አሟልተህ/ሽ ለክፍሉ በንባብ አቅርብ/ቢ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ፏፏቴ | ዋሻ | ጎብኚዎች |
| መስህብ | | ውበት |

በተጨማሪነት መስህብነት የሚነሳው የጎረንቲ ፏፏቴ ወንዝ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከያዬ ከተማ በስተምሰራቅ አቅጣጫ በግማሽ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ከ ______________ አጠገብ በጎን በኩል የሚገኘው ______________ ለአካባቢው ትልቅ ______________ ሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ወደዚህ ስፍራ ለጉብኝት የሚመጡት ______________ በአንድ ጊዜ ሁለት ______________ ማለትም ፏፏቴና የተፈጥሮ ዋሻ ከመመልከታቸው ባሻገር የተለያዩ ቀለማት ያላቸው አዕዋፍ ዝርያዎች መመልከት ይችላሉ፡፡



## ክፍል አራት፤ መፃፍ

- አያያዥ በመጠቀም አንቀፅ መፃፍ
- ተራኪ አንቀፅ መፃፍ

## አቅርቦት

የሚከተለውን ማስታወሻ በደብተርህ/ሽ ፃፊ/ፍ፡፡

አንቀፅ አንድ ፍሬ ሀሳብ የሚብራራበት አውራ ነጥብን መሰረት አድርጎ በሚደጋገፍና ለአንድ ተልዕኮ በተሰለፉ ልዩ ልዩ ዓረፍተ ነገሮች አማካኝነት የሚገነባ የምንባብ አነስተኛ ክፍል ነው፡፡ ሀይለ ቃል በአንድ አንቀፅ ውስጥ የሚገኘውን ሀሳብ አጠቃሎ የያዘ በሱ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ሌሎች ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮች ያሰለፈ ዓረፍተ ነገር ማለት ነው፡፡ ዝርዝር ዓረፍተ ነገር የሚባለው በሀይለ ቃሉ ተጠቃሎ የቀረበውን ሀሳብ የሚያብራራ፣ የሚተነትን የሚዘረዝር ነው፡፡

ምሳሌ፣ አካባቢያችን ለምለም ነው፡፡ ያለሁበት አካባቢ የአየር ንብረት ወይና ደጋ ስለሆነ በየጊዜው ችግኝ ይተክላሉ፤ በየተራ አካባቢውን በማፅዳት ቆሻሻ ያቃጥላሉ፡፡ ማንም ሰው ያለ አግባቡ አንድ ዛፍ እንኳን ቢቆርጥ በህግ ይቀጣል፡፡ ሁሉም በየደጁ የተለያዩ ዕፅዋትን ይንከባከባል፡፡

## 2 መልመጃዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች ቀጥሎ በቀረቡት አያያዦች በማያያዝ የተሟላ አንቀፅ አድርገህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡

| | |
|---|---|
| ነገር ግን | በተጨማሪ |
| ከዚያም | በመጨረሻም |

ሀ. ትምህርት ቤት ስሄድ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛዬን(ጭምብሌን) አደርጋለሁ፡፡

ለ. ክፍል ውስጥ ርቀቴን ጠብቄ እቀመጣለሁ፡፡

ሐ. ትምህርት ቤት ሆኜ ጭምብሌን በፍፁም አላወልቅም፡፡

መ. ከትምህርት ቤት ስመለስ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛዬን አውልቄ በጥንቃቄ አስቀምጣለሁ፡፡

ሠ. እጄን በውሃና በሳሙና በደንብ እታጠባለሁ፡፡

፪. ቀጥሎ በጅምር ከቀረቡት ሀሳቦች መካከል አንዱን በመምረጥ አሟልተህ/ሽ አንቀፅ ፃፊ/ፍ፡፡

1. አቶ ዳንኤል ግቢ ብዙ የዘይቶኒ ፍሬ የሚያፈራ ዛፍ ነበር፡፡እኔና ጓደኛዬም ያንን ዘይቶኒ ለማውረድ ግቢው ጭር እስኪል ድረስ እንጠብቃለን፡፡ ከዚያም__________

____________________________________________

2. የመኖሪያ ቤታችን ፊት ለፊት ትልቅ የዝግባ ዛፍ አለ፡፡ በዝግባው ላይ ብዙ የአዕዋፍ ዝርያዎች ይገኛሉ፡፡ ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት ስንነሳ__________________________

______________________________

3. ጠዋት ከእንቅልፌ እንደተነሳው ወደ መፀዳጃ ቤት እሄዳለሁ፡፡ ስመለስ እጄንና ፊቴን በውሃና ሳሙና በደንብ እታጠባለሁ፡፡ ከዚያ የተኛሁበትን አልጋ አነጥፋ ለሁ________________________________________________________

# ምዕራፍ አስር

## አህጉራት፣ ባህሮችና ሐይቆች

- ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች


- ባዳመጥሽው/ከው ነገር መረጃ ትሰጣለህ/ጪያለሽ፤
- ዋና ዋና ነጥቦችን ለይተሽ/ለይተህ ትናገራለህ/ሪያለሽ፤
- ምንባቡን አንብበሽ/ህ የመረዳት ጥያቄዎችን ትመልሻለሽ/ሳለህ፤
- የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክለሽ/ህ ትፅፊያለሽ/ለህ፤
- የራስሽን/ህን ታሪክ ትፅፊያለሽ/ህ፤

## ክፍል አንድ፤ ማዳመጥ

- ባዳመጡት ፅሁፍ መሰረት መረጃ መስጠት

### የማነቃቂያ ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን ካርታ በማየት የአህጉራት ስሞችን ተናገሪ/ር፡፡



## 2 አቅርቦት

መምህራችሁ የሚያቀርቡልሽን/ህን ምንባብ በፅሞና አዳምጪ/ጥ፡፡

### መልመጃዎች

፩. ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎችን መምህርሽ/ህ ሲያነቡልሽ/ህ ባዳመጥሽው/ከው መሰረት በቃል መልሺ/ስ፡፡

ሀ. አለማችን በስንት አህጉራት የተገነባች ነች?

ለ. ትልቁ አህጉር ማን ይባላል?

ሐ. አንድን አህጉር ከሌላው የሚለያየው ውቅያኖስማነው?

መ. አፍሪካንና አውሮፓን የሚለየው ምንድን ነው?

፪. ቀጥሎ ባዳመጣችሁት ፅሁፍ መሰረት ለቀረቡ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጭ/ጪ፡፡

1. አህጉራት የሚባሉት ________ ናቸው፡፡

   ሀ. ኢስያና አፍሪካ ለ. አውሮፓና አንታርቲካ

   ሐ. አውስትራሊያ፣ሰሜን አሜሪካና ደቡብ አሜሪካ መ. ሁሉም

2. ሰፋፊዎቹ የውሃ አካላት ________ናቸው፡፡

   ሀ. አትላንቲክ ውቅያኖስ ሐ. ህንድ ውቅያኖስ

   ለ. ሰላማዊ ውቂያኖስ መ. ሁሉም

፫. ባዳመጥሽው/ከው ምንባብ መሰረት በ"ሀ" ስር የተሰጡትን ቃላት ከ"ለ" ስር ካለው ፍቺ ጋር አዛምጂ/ድ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አህጉራት | ሀ. ከውቅያኖስ በስፋት የሚያንስ ከሀይቅ የሚሰፋ የውሃ አካል ነው |
| 2. ባህር | ለ. የምንኖርበት ምድር |
| 3. ውቅያኖስ | ሐ. በውስጧ የብዙ ሀገራት ካርታዎች የያዘች |
| 4.መሬት (የብስ) | መ. ከባህር የሚበልጥ ሰፊ የውሃ አካል |



## ክፍልሁለት፣ መናገር

- ዋና ዋና ነጥቦችን ለይቶ መናገር

### 1 አቅርቦት

፩. ከዚህ ቀጥሎ የቀረበልሽን/የቀረበልህን ማስታወሻ ለክፍል ጓደኞችሽ/ህ ተናገሪ/ር፡፡

**ማስታወሻ**

ካርታ ማለት አንድን መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ለመግለፅ በወረቀት የሚቀመጥ መረጃ ነው፡፡ ካርታ በውስጡ የአንድን ቦታ መገኛ ህጋዊ ወሰኖችን፣ድንበሮችን፣ወዘተ ይይዛል፡፡ የዓለም

ካርታና የከተማ ካርታ በሰፊው የሚታወቁ የካርታ ዓይነቶች ናቸው፡፡ በሀገራችን ደግሞ የክልል፣የዞን፣የወረዳና የከተሞች ካርታዎች ይገኛሉ፡፡ የአንድን ከተማ ካርታ በመያዝ ወደምንፈልግበት ቦታ መድረስ እንችላለን፡፡ካርታ በእጅ በወረቀት ሊሳል ይችላል፡፡

**ቀጥሎ የቀረበውን ምልልስ ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ ተነጋገሩ፡፡**

ተማሪ ሰናይትና ደረጀ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ሰናይት ካርታ መሳል ትችላለች፤ ደረጀ ደግሞ በካርታው ላይ የተመለከቱ ቦታዎችን የማንበብ ችሎታ አለው፡፡

**ደረጀ፤** ሰናይት! ከአህጉራት መካከል የትኛውን ነው መስራት የምትችዪው?

**ሰናይት፤** አይ! እኔማ የዓለም ካርታዎችን ሁሉ መሳል እችላለሁ ነገር ግን በቀላሉ እያየሁ መሳል የምችለው የአፍሪካ ካርታን ነው፡፡

**ደረጀ፤** የአፍሪካ አህጉር ስንት ሀገራትን ያካትታል?

**ሰናይት፤** አባቴ የጂኦግራፊ መምህር በመሆኑ እርሱ ሲናገር እንደሰማሁት ሃምሳ አራት ሀገራትን ያካትታል፤

**ደረጀ፤** ኢትዮጵያ የምትገኘው በአፍሪካ አህጉር ላይ መሆኑን ታውቂያለ ሰናይት?

**ሰናይት፤** አይ! እኔ ካርታዎችን መሳል እችላለሁ እንጂ ሀገራችን የት እንደምትገኝ አላጠናሁም፡፡

**ደረጀ፤** የአፍሪካ ካርታ ስናይ ኢትዮጵያ የምትገኝበትን ቦታ ላሳይሽ እችላለሁ፡፡

**ሰናይት፤** የአፍሪካ ካርታ ቀንዳም ስለሆነ እሱን መሳል እወዳለው፡፡

**ደረጀ፤** ታድያ ኢትዮጵያ የምትገኘው በአህጉሩ ቀንድ ላይ ነው?

ሰናይት፤ ሌሎችንም በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያሉ ሀገራትን ታሳየኛለህ፡፡

**ደረጀ፤** በደንብ ነው የማሳይሽ፤እኔ እኮ ካርታውን መሳል ነው የሚያቅተኝ እንጂ ካርታ ማንበብ ጎበዝ ነኝ፡፡

**ሰናይት፤** እንደዛ ከሆነ እኔ ካርታ መሳል አለማምድሃለሁ አንተ ግን እንዴት እንደሚነበብ ታሳየኛለህ፡፡

**ደረጀ፤** በሃሳብሽ እስማማለሁ፡፡

**ሰናይት፤** አመሰግናለሁ፤ አሁን እንስራ፡፡

## 2 መልመጃዎች


፩. ከላይ የቀረበውን ጭውውት መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎች መልሺ/ስ፡፡

ሀ. ተማሪ ደረጀ ሰናይትን ‹‹ኢትዮጵያ የምትገኘው በአፍሪካ አህጉር ላይ መሆኑን ታውቂያለሽ?›› ብሎ ሲጠይቃት ምን ብላ መለሰችለት?

ለ. ተማሪ ሰናይት የአፍሪካ ካርታን መሳል የምትወደው ለምንድን ነው?

ሐ. ሰናይት ለደረጀ ያቀረበችው ሃሳብ ‹‹እኔ ካርታ መሳል አለማምድሃለሁ አንተ ግን እንዴት እንደሚነበብ ታሳየኛለህ›› ስትለው ተባብረው እየሰሩ ልምድ ልውውጥ ማድረግ ጥሩ ነው ትላላችሁ? ለምን? በቡድን ተነጋገሩ፡፡

፪. ቀጥሎ የቀረበውን የአፍሪካ ካርታን በማየት የተጠቀሱ ሀገራትን በተገቢ ቦታቸው በመፃፍ ተናገሪ/ር፤ ሱዳን፣ ኬንያ፣ ሶማሊያ፣ ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ እና ኤርትራ



## ክፍል ሦስት፤ ማንበብ

- አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን መመለስ

**1 የማነቃቂያ ተግባር**

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን ከማንበበሽ/ህ በፊት በቃል መልስ/ሽ፡፡

- በአካባቢሽ/ህየምታውቂው/ቀውን ሀይቅ ተናገሪ/ር፡፡
- በሀይቅ ውስጥ ምን ምን ይገኛል?

**2 አቅርቦት**

፪. ቀጥሎ ‹‹የኢትዮጵያ ኃይቆች›› በሚል ርዕስ የቀረበላችሁን ምንባብ በቅድሚያ ጥንድ ጥንድ በመሆን በጋራ አንብቡ፡፡በመቀጠልም በየግልሽ/ህ በጥሞና አንብቢ/ብ፡፡

### የኢትዮጵያ ኃይቆች

የሃይቅ ውሃ እንደወንዝ ውሃ የሚፈስ ሳይሆን በአንድ ቦታ ረግቶ የተቀመጠ መሆኑ ከወንዝ ይለያል፡፡ኢትዮጵያ የበርካታ ሐይቆች መገኛ አገር ናት፡፡የኢትዮጵያ ሐይቆች በሶስት ከፍፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡እነዚህም ከፍተኛ ቦታ የሚገኙ ኃይቆች፣በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኙ ሐይቆች እና ሰው ሰራሽ ሐይቆች ናቸው፡፡

ከፍተኛቦታየሚገኙኃይቆችየሚገኙትመሃልጣና፣አሸንጌ፣ሐይቅጉዳ፣ቢሾፍቱ፣ሆራ፣ወንጪና ኢንጺ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ጣና በኢትዮጵያ ከሚገኙ ሐይቆች ሁሉ በስፋት ትልቁ ሲሆን ስፋቱ ሶስት ሺ ስድስት ኪሎ ሜትር ነው፡፡

የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የበርካታ ሐይቆች መገኛ ነው፡፡ ከነዚህም መሀል ዝዋይ፣ላንጋኖ ፣አቢጃታ፣ሻላ፣ሀዋ፣ጫሞ፣አባያ፣ቱርክና(ሩዶልፍ) ይገኙበታል፡፡ በስምጥ ሸለቆ ከሚገኙ ሐይቆች ትልቁ የአባያ ሐይቅ ነው፡፡ የሻላ ሐይቅ ደግሞ በኢትዮጵያ ከሚገኙ ሐይቆች ሁሉ በጥልቀቱ የሚታወቅ ነው፡፡

ሌላው የወንዝ ውሃ በመገደብ የሚፈጠሩ ሐይቆች ሰው ሰራሽ ሐይቆች በመባል ይታወቃሉ፡፡አገልግሎታቸው የኤሌክትክ ኃይል ማመንጨትና ለመስኖ ማዋል ነው፡፡ በዚህ ዓይነት

ከተፈጠሩ ሐይቆች መካከል የቆቃ፣መልካዋከና፣አባሳሙኤል፣ፊንጫ፣ግልገል ጊቤ ይገኙበታል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአባይ ወንዝ ላይ የሚገነባውን ሰው ሰራሽ ሐይቅ ከአፍሪካ ትልቁ እንደሆነ ይገመታል፡፡

የኢትዮጵያ ሐይቆች ጠቀሜታ የሚከተሉት ናቸው፡፡ለመጓጓዣ የምንጠቀምባቸው የጣና ሀይቅ፣ባህርዳር ሐይቅ ላይ ወዳሉ ደሴቶች ወደ ጎርጎራ ለመጓጓዝ ያገለግላል፡፡ሌላው በተጨማሪ ለዓሳ ማጥመጃ ሲሆን ለቱሪዝም መስህብ ሆኗል፡፡ እንደ ቆቃ ሐይቅ ያሉት ደግሞ ለኤሌክትሪክ ኃይል ምንጭነት ያገለግላል፡፡

ምንጭ፡- www.absinica.search

## መልመጃ

፩. ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎችን አንብበሽ/ህ በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጭ/ጥ፡፡

1. የኢትዮጵያ ኃይቆች ከአቀማመጣቸው አንፃር በ _________ ይከፈላሉ፡፡
   ሀ. በሁለት ለ. በአራት ሐ. በሦስት መ. በአምስት
2. ኢትዮጵያ _________ ሐይቆች መገኛ ሀገር ናት፡፡
   ሀ. የጥቂት ለ.የብዙ ሐ. የአራት መ. የስምንት
3. ከሚከተሉት መካከል የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ፊንጫ ለ. ላንጋኖ ሐ. ጣና መ.ቆቃ
4. የወንዞችን ውሃ በመገደብ የሚፈጠሩ ሐይቆች _________ ይባላሉ፡፡
   ሀ. የተፈጥሮ ሐይቆች ሐ. የከፍተኛ ቦታ ሐይቆች
   ለ. ሰው ሰራሽ ሐይቆች መ. የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች
5. የኢትዮጵያ ሐይቆች ለ _________ ይጠቅማሉ፡፡
   ሀ. ለዓሳ ማጥመድ ሐ. ለመጓጓዣ አገልግሎት
   ለ. ለቱሪዝም መስህብነት መ. ሁሉም

፪. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምሳሌው መሰረት ተቃራኒ ፍቺ ስጭ/ጥ፡፡

| ምሳሌ፡- ቃላት | ተቃራኒ ፍቺያቸው |
|---|---|
| ሐይቅ | መሬት |
| ሀ. መርጋት | ________ |
| ለ. ሰው ሰራሽ | ________ |
| ሐ. መገደብ | ________ |
| መ. ጠቀሜታ | ________ |

፫. በ"ሀ" ስር ለቀረቡ ጥያቄዎች ከ"ለ" ስር ለቀረቡት መልሶች ጋር አዛምድ/ጂ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ______ 1. ሰው ሰራሽ ሐይቆች | ሀ. ጣና |
| ______ 2. የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች | ለ. አባያ፣ሻላ |
| ______ 3. ከፍተኛ ቦታ የሚገኙ ሐይቆች የሚያገለግሉ ሐይቆች | ሐ. ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ |
| ______ 4. ከኢትዮጵያ ሐይቆች ትልቁ ኃይቅ | መ. ጣና፣ቢሾፍቱ |
| | ሠ. የአባያ ሐይቅ |
| | ረ. ቪክቶሪያ ሐይቅ |

## ክፍል አራት፤ መፃፍ

- የተዘበራረቁ ቃላትን አስተካክሎ ዓረፍተ ነገሮችን መፃፍ
- ግለ ታሪክ መፃፍ

### 2 አቅርቦት

ተዘበራርቀው የተቀመጡ ሃሳቦችን አስተካክለሽ/ህ ዓረፍተ ነገር ስሪ/ራ፡፡

ምሳሌ፣ ደኖች እንዲኖር ወቅታዊ ዝናብ ያግዛሉ፡፡

ደኖች ወቅታዊ ዝናብ እንዲኖር ያግዛሉ፡፡

ሀ. ሱዳን ነች ከምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች አንደኛ በስፋት፡፡

ለ. በጥልቀት አንደኛው ሐይቅ በኢትዮጵያ ነው ሻላ፡፡

ሐ. አባያ ሐይቅ በሎካ ወረዳ በኩል ያዋስናል የሲዳማን ክልል፡፡

መ. የአፍሪካ አህጉር ነው ከሰባቱ አህጉራት መካከል በስፋት ሁለተኛው፡፡

ሠ. ሀገራችን ኢትዮጵያን እወዳለሁ በጣም፡፡

ረ. ከውቅያኖስ በስፋት የሚያንስ ነው የውሃ አካል ከሐይቅ የሚሰፋ፡፡

ሰ. ሐይቅ ማለት የረጋ ውሃ የሚያንስ በስፋት ከባህር ነው፡፡

፪. ቀጥሎ የቀረበልሽን/ህን ሀሳብ መሰረት በማድረግ የተሟላ ዓረፍተነገሮችን ፃፊ/ፍ፡፡

ምሳሌ፡- <u>ሀዋሳ ሐይቅ</u>- የሀዋሳ ሐይቅ የፍቅር ሐይቅ በመባል ይታወቃል፡፡

ሀ. የኢትዮጵያ መልክዓምድር አቀማመጥ

ለ. የአውስትራሊያ አህጉር

ሐ. የባህር ውሃ

መ. ወንዝ

ሠ. አህጉራት

ረ. ትልቁ አህጉር

፫. የግል ታሪክሽን/ህን ፅፈሽ/ህ ለመምህር አሳይ/ዪ፡፡ ስትፅፊ/ፍ የሚከተሉትን ነጥቦች ተከተይ/ል፡፡

ሀ. የተወለድሽበትን /የተወለድክበትን ቀን ዓመት ምህረት ቦታ ይጠቀስ፡፡

ለ. አሁን እስካለሽበት/ለህበት የክፍል ደረጃ የት እንደተማርሽ/ክበቅደም ተከተል ጥቀሺ/ስ፡፡